# እስላም እና ክርስትና

## (ንጽጽራዊ ኣቀራረብ)

ዶ/ር ሙሓመድ ዓሊ ኣልኹሊ

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر و أم الحمام
هاتف : 96614884496 فاكس : 96614827489
رقم الحساب : 17777/8 فرع 251
mather-dawa@hotmail.com

ዶ/ር ሙሐመድ ዐሊ አልኹሊ

# ኢስላም እና ክርስትና

## (ንጽጽራዊ አቀራረብ)

አሳታሚ - ሁዳ ኘሬስ ሊሚትድ
የመጀመሪያ እትም
1989

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

Copyright HUDA PRESS Ltd. 1417 A.H. /1997

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise, without the prior permission of the copyright owner.

# ማውጫ

## ምዕራፍ 1 ትክክለኛነት

የወንጌል ጸሐፊዎች 1፣ ብሉይና ሐዲስ ኪዳኖች 3፣ ይዘት 3፣ ሳይንሳዊ እውነቶች 4፣ 50,000 ስሕተቶች 5፣ ትክክለኛነት 5፣ ተቃርኖዎች 6፣ ምርጫውን ማን አካሄደው? 7፣ ኦሪጂናል ቋንቋ 8፣ ብዙ የተለያዩ ቅጂዎች ወይስ አንድ ብቸኛ ቅጂ? 8፣ ሐዋርያ ወይስ ነቢይ? 9፣ ውስጣዊ አለመጣጣሞች 10፣ ጳውሎሳዊነት ወይስ ክርስትና? 11፣ የሠላምታና የመልካም ምኞት መግለጫ ደብዳቤዎች 12፣ የታረመውና የተከለሰው መጽሐፍ ቅዱስ 13፣ የትኛው መጽሐፍ ቅዱስ? 14፣ የመጽሐፉ መጠሪያ ስም 15፣ የሃይማኖቱ መጠሪያ ስም 16፣ እውነተኛው መፈታተኛ 17፣ መነሻና መድረሻ 19፣ ቅዱስ ነው? ወይስ አይደለም? 19

## ምዕራፍ 2 አምላክ በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

ሥላሴ 21፣ የአንድ አምላክ እምነት ወይስ የአምላክ–ብዙነት እምነት? 22፣ አብ ወይስ ወልድ? 22፣ ተለዋዋጭ አምላክ 23፣ አብ 24፣ እንቆቅልሹ 25፣ የእግዚአብሔር አንድነት 26፣ ሦስት ወይስ አንድ? 26፣ ልጅ ያለው ወይስ የሌለው? 26፣ ብሉይ ኪዳን 27፣ ያህዌህ ወይስ ምን? 28፣ ለምን ያህዌህ? 29፣ ይደክማል ወይስ አይደክምም? 31

## ምዕራፍ 3 ኢየሱስ በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

ለመሆኑ እሱ ማነው? 32፣ አባቱ ማነው? 32፣ ልጁ ማነው? 33፣ ፀሎት 34፣ ቅድመ አያቶቻቸው 35፣ ኢየሱስና አዳም 35፣ ነቢይ ወይስ አምላክ? 36፣ አምላክ በሹመት ዕድገት 37፣ አናጺ ወይስ አምላክ? 37፣ ተፈጥሮአቸው 39፣ እንቆቅልሽ ወይስ ግልጽ? 40፣ ምክንያታዊው ምርጫ 40፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት 41፣ አስገራሚ የሹመት ዕድገቶች 42፣ ተሰቅለዋል? አልተሰቀሉም? 43፣ በፈቃደቸው ወይስ ከፈቃዳቸው ውጭ? 44፣ ተዋረዱ ወይስ ከውርደት ዳኑ? 45፣ ውድቀት ወይስ ስኬት? 46፣ ኢየሱስና ክርስትና 46

## ምዕራፍ 4 የሁለቱ ሃይማኖቶች የእምነት መሠረቶች

መሠረታዊ እምነቶች 48፣ ልጆችና ውሾች 50፣ ኢየሱስ ወደነማን ተላኩ? 51፣ ከፊሉን እውነት ብቻ ወይስ ሁሉንም? 51፣ አጠቃላይነት 52፣ በውርስ የሚተላለፍ ኃጢአት 53፣ አባብ ወይስ ሰይጣን? 54፣ ተግባርና ፍርድ 54 መዳን የት አለ? 55፣ ጥምቀት 56፣ ቤዛነት በተተኪነት 56፣ የፍርድ ቀን 57፣ ስቅለት ወይስ ሰናይ ተግባራት? 58፣ ያለ መጽሐፍ ወይስ ከመጽሐፍ ጋር? 58 ቤተክርስቲያንና ሳይንስ 58፣ ሥጋ ወደሙ 59

## ምዕራፍ 5 የሥርዓተ አምልኮ አፈጻጸም በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

ምልጃ 61፣ ንስሐ መግባት 61፣ ምሕረትና ይቀርታ ልመና ለምን? 62፣ ለእግዚአብሔር መታዘዝ 63፣ ማንበብ የማይፈቀድላቸው 63

## ምዕራፍ 6 ሥነ ምግባር በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

እጅ መስጠት ወይስ አፀፋ መመለስ? 65፣ ከፉን መቃወም 66፣ ዐሥርቱ ትዕዛዛት 66፣ አርአያነት 67፣ ባሕታዊነትና ምናኔ 67፣ ባለፀጋ 68፣ የዋስትና ውጤት 69፣ የሰበካ ዐቢይ ርዕስ 70፣ ካሕናትና ጀሌ ማይማን 73፣ አጠቃላይነትና ሁለገብነት 74፣ ዛፍና ፍሬዎቹ 75

## ምዕራፍ 7 ሕግ በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

ውኃ ወይስ የወይን ጠጅ?80፣ ውርስ 80፣ ኢየሱስና የአሳማ ሥጋ 81፣ ብዙ ሚስት ማግባት 82፣ የመቅጫ ሕግ የለም 83፣ ምንኩስና ወይስ ጋብቻ? 84፣ የሴት ልጅ ሚና 84፣ የሕልም ኃይል 85፣ የሙሴ ሕግ 86፣ ተለዋዋጭነት ያለው ሃይማኖት 87፣ ተለዋዋጭ ሕጐች 88፣ ያልተሟላ መመሪያ 89

# መቅድም

እስላምና ክርስትና ዛሬ በዓለማችን ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፉ ሃይማኖቶች ናቸው። የያንዳንዳቸው ተከታዮች ቁጥር ከአንድ ቢሊዮን ይልቃል። ሁለቱም ተጨማሪ ተከታዮችን ለማፍራት ይጥራሉ።

ሁለቱ ሐይማኖቶች ለረዥም ምእተ ዓመታት በተለያዩ መስኮችና በተለያዩ መድረኮች ሲፎካከሩ ኖረዋል። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን የያንዳንዱ ሐይማኖት ተከታዮች ስለሌላኛው ሐይማኖት የሚያውቁት በጣም ጥቂቱን ብቻ ነው። ሁለቱን ሐይማኖች አንድ ላይ በአንድ መጽሐፍ ለማቅረብ መሞከር አንባቢ በሁለቱ እምነቶች ላይ ንጽጽራዊ ምልከታ እንዲኖረው ለማድረግ ጠቃሚ ይሆናል የሚል ሐሳብ አእምሮዬ ውስጥ የተጫረውም ለዚህ ነው።

ይህ መጽሐፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል:-

1. እስላምና ክርስትና ተአማኒነትን (Authenticity) በተመለከተ እንዴት ይመዘናሉ?
2. ከክርስትና እምነት አንጻር እግዚአብሔር ምንድነው? ከእስላም እምነት አኳያስ?
3. ሁለቱ ሐይማኖቶች በየፊናቸው ኢየሱስን እንዴት ይመለከታሉ?
4. የያንዳንዱ ሐይማኖቶች መሠረታዊ የእምነት መርሆዎች ምንድናቸው?
5. አምልኮት በሁለቱ ሐይማኖቶች ውስጥ እንዴት ይለያያል?
6. በእስላምና በክርስትና መካከል ያሉት ሥነምግባራዊ (ሞራላዊ) ልዩነቶች ምንድናቸው?
7. ሕግ በሁለቱ ሐይማኖቶች ውስጥ ምንድነው?

በአጭሩ ይህ መጽሐፍ በሰባት ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ተአማኒነት፣ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ፣ የእምነት መሠረቶች፣ አምልኮት፣ ሥነምግባርና ሕግ የሚሉ ጽንሰ–ሐሳቦች ላይ ያላቸውን አቋም በተመለከተ እስላምና ክርስትናን በንጽጽራዊ መንገድ ለመመልከት የታለመ ነው። ሁሌም እንደሚባለው ዕውቀት ኃይለ ነው። ማወቅ ካለማወቅ የተሻለ ነው። ይህ ንጽጽራዊ ዕውቀትም አንባቢውን ለራሱ ተስማሚ ሆኖ ሊያገኘው በሚችል መንገድ ሊጠቀመው ይችላል። መጽሐፉ በጥንቃቄና ነባራዊ በሆነ ሁኔታ፣ አእምሮን ነጻ፣ ልብን ክፍት አድርገው ካነበቡት መላ ሕይወትዎን ሊለውጥ ይችላል።

ዶክተር ሙሐመድ ዐሊ ዐብዱልከሪም አልኹሊ
አማን፣ ጆርዳን
22/10/1410 ዓ.ሁ. 17/5/1990 ዓ.ክ.

# ምዕራፍ 1

# ትክክለኛነት

## የወንጌል ጸሐፊዎች

ማቴዎስ የኢየሱስ ደቀመዝሙር ወይም ሐዋርያ ነው። ወንጌሉን የጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን እሱ የጻፈው የመጀመሪያው ኦሪጂናል ቅጂ ጭራሹኑ ጠፍቷል። ዛሬ ያለው ቅጂ የዚያ የጠፋው ቅጂ ትርጉም ብቻ ነው። በመሆኑም ዛሬ የሚገኘው የማቴዎስ ወንጌል ኦሪጂናል ቅጂው የጠፋ በመሆኑ ምክንያት ያን ጊዜ ማቴዎስ ከጻፈው ጋር ተመሳሳይ ስለመሆኑ ማንም ማረጋገጥ አይችልም።

ማርቆስ የኢየሱስ ሐዋርያ አይደለም። የጴጥሮስ ደቀመዝሙር ነው። ስለሆነም የማርቆስ ወንጌል ከኢየሱስ የተላለፈ የመጀመሪያው ቀጥተኛ ትረካ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም።ማርቆስ ኢየሱስ የሠሩትን አላየም፤የተና ገሩትንም በጆሮው አልሰማም። ስለዚህም ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ያቀረበውን ዘገባ እውነተኛነት ማንም ሰው ማረጋገጥ አይችልም። ስለ ኢየሱስ በመዘገብ ረገድ ከሐዋርያቱ ተማሪዎች ይልቅ የኢየሱስ ቀጥተኛ ተማሪዎች የነበሩት ሐዋርያት አስተማማኝ ዘጋቢዎች ናቸው። ማርቆስ ግን የኢየሱስ ደቀመዝሙር ደቀመዝሙር ነው።

በተመሳሳይ መልኩ ሉቃስም የኢየሱስ ሐዋርያ አይደለም። ኢየሱስን ፈጽሞ አላየም፤ ሲናገሩም አዳምጧቸው አያውቅም። ሉቃስ የኢየሱስ ደቀመዝ ሙር ደቀመዝሙር እንኳ አይደለም። ሉቃስ በተራው ጭራሽ የኢየሱስ ሐዋርያ ያልነበረው የጳውሎስ ደቀመዝሙር ነው። ኢየሱስን ፈጽሞ ያላየና ጭራሽ ከሳቸው ያልሰማ እስከሆነ ድረስ የሉቃስን ዘገባ እንዴት መቀበል እንችላለን? የሦስተኛ ደረጃ ዘገባዎች እስከሆኑ ድረስ የርሱ ዘገባዎች ምን ዓይነት የትክክለኛነት ዋጋ ይኖራቸዋል?

ወንጌላዊውን ዮሐንስ በተመለከተ፣ ምሑራን ወንጌልን የጻፈው ዮሐንስ የኢየሱስ ደቀመዝሙር የነበረው ዮሐንስ አይደለም ይላሉ። ተንታኞች እንደሚ ናገሩት የዮሐንስ ወንጌል ይዘትና የቃላት አጠቃቀሙ ሲታይ በኢየሱስ ሐዋር ያው ዮሐንስ የተጻፈ ሊሆን አይችልም። የሆነ ሰው ጽፎት የበለጠ ተአማኒነት ለማስጠት ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር አያይዞታል። ወንጌሉ የተጻፈው በ97 ዓ.ክ አካባቢ ማለትም ከኢየሱስ መሰወር ስልሳ አራት ዓመታት በኋላ መሆኑን ምሑራን ያረጋግጣሉ። ኢየሱስ ሲሰወር ዮሐንስ ዕድሜው ሃያ ዓመት ብቻ ነበር ቢባል ወንጌሉ በተጻፈበት ጊዜ ዕድሜው በትንሹ ሰማኒያ አራት ዓመት ነው።

ታዲያ ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን ለመጻፍ ዕድሜው 84 ዓመት እስኪሆን ድረስ መቆየት ለምን አስፈለገው? ሥራውን ለመጀመር 64 ዓመት ሙሉ ምን አስጠበቀው? ይህ የዮሐንስ ወንጌል በሐዋርያው ዮሐንስ አልተ ጻፈም የሚለውን ማጠቃለያ ያረጋግጣል።

አጠር ባለ አነጋገር ያሉን በእጅጉ አጠራጣሪ የሆኑ አራት ወንጌሎች ናቸው። የማቴዎስ ኦሪጂናል ቅጂ ለዘላለሙ የጠፋ ስለሆነ ዛሬ ያለውን የትርጉም ቅጂ ትክክለኛነት ማንም ማረጋገጥ አይችልም።ማርቆስ የኢየሱስ ቀጥተኛ ደቀመዝሙር ባለመሆኑና የኢየሱስ ቀጥተኛ ዘጋቢ ባለመሆኑ የማርቆስ ወንጌል ብዙ የሚታመን አይደለም። ተመሳሳይ የሆነ ጉድለት በሉቃስ ላይም ይስተ ዋላል። ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ሉቃስ የጳውሎስ ተማሪ ሲሆን ጳውሎስ ደግሞ የኢየሱስ ቀጥተኛ ሐዋርያ የነበረው የበርናባስ ደቀመዝሙር ነውና። የሉቃስ ወንጌል የሦስተኛ ደረጃ ዘገባ ነው። የዮሐንስ ወንጌል በስመ ሞክሼ ጸሐፊ እንጂ በሐዋርያው ዮሐንስ የተጻፈ አይደለም። ስሙ ያገለገለው ለሽፋንነት ብቻ ነው።

በተቃራኒው ቁርአን አንድ ወጥ ቅጂ ብቻ ነው ያለው። የተለያዩ የቁርአን ቅጂዎች የሉም።

የአላህ የጠራ ቃል ነው ብለው የትኛውን ይመርጣሉ? አራት ተጻራሪ ቅጂዎች ያሉትን፣ ኦሪጂናል ቅጂው የጠፋውንና የሁለተኛ ደረጃ ዘገባና የሦስተኛ ደረጃ ዘገባ የሆነውን ወንጌል? ወይስ አንድ ብቸኛ ቅጂ ያለውን ቁርአን?

## ብሉይና ሐዲስ ኪዳኖች

ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አንድ ነው፣ ልጅም የለውም ይላል።ሐዲስ ኪዳን ግን ለእግዚአብሔር ልጅ ይሰጣል፤ ክርስትናም እግዚአብሔርን ሦስት በአንድ ያደርጋል። በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን የፍርዱን ቀን ወይም መጪውን ሕይወት የማይቀበል ሲሆን ሐዲስ ኪዳን ግን ሁለቱንም ይቀበላል።

ሁለቱም ኪዳኖች በአንድ መጽሐፍ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ (Bible) ውስጥ ቢሆኑም እንኳ በአስገራሚ ሁኔታ በሁለት አበይት የእምነት መርሆዎች ማለትም በእግዚአብሔርና በዳግም ሕይወት ላይ ስምምነት የላቸውም። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንደሚባልላቸው ሁለት ከእግዚአብሔር የተገለጹ መጽሐፎች፣ እግዚአብሔር አንድ ነው ወይም ሦስት በአንድ ነው? ዳግም ሕይ ወት አለ የለም? የፍርድ ቀን አለ የለም? ትንሣኤ አለ የለም? በሚሉት ላይ እንዴት ልዩነት ይኖራቸዋል? እነኚህ ሁለት ኪዳኖች እውነት የእግዚአብሔር ቃል ቢሆኑ ኖሮ በነኛ መሠረታዊ የእምነት መርሆዎች ላይ ልዩነት ባልኖራቸው ነበር።

በተቃራኒው፣ የእስላም መጽሐፍ የሆነው ቁርአን በጣም ግልጽና ፍጹም ወጥነት ያለው መጸሐፍ ነው። እግዚአብሔር አንድ ነው። ልጅም ሆነ አባት የለውም። የትንሣኤ ቀን ይመጣል። የፍርድ ቀንም ይመጣል። ከዚህ ሕይወት በኋላ ሌላ ሕይወት አለ ይላል።

እርስ በርሱ የሚፋለሰውን መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ እርስ በርሱ የተጣጣመ፣ ግልጽና ብሩሕ የሆነውን ቁርአን ነው ንጹህ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው የሚመርጡት?

## ይዘት

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል + የነቢያት ቃል + የተራኪዎች ቃል +የተንታኞች ቃል +የሐዋርያት ቃል ያካተተ መጽፍሐፍ ነው። ይህ

የመጽ ሐፍ ቅዱስ ምሑራን የሚሉትና ማንኛውም አንባቢ ለገዛ ራሱ በቀላሉ ማየት የሚችለው እውነታ ነው።

ቁርአን ግን የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ቁርአን የነቢዩ ሙሐመድን ቃል ወይም የታሪክ ጸሐፊዎችን ማብራሪያም ሆነ የተንታኞችን ትንታኔ አላካተተም። የሙሐመድ ቃሎች ከቁርአን ውጭ በሌሎች መጻሕፍት ውስጥ ታቅፈዋል። ተንታኞች፣ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተርጓሚዎች ከቁርአን የተለዩና የየራሳቸውን መለያ የያዙ መጻሕፍት አሏቸው።

ከቅይጥ ጸሐፊዎቹና ከብርዝ ይዘቶቹ ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ነው? ወይስ አንድ ወጥን ቁርአን ነው የጠራ የእግዚአብሔር ቃል አድርገው ለመቀበል የሚዳዳዎት?

## ሳይንሳዊ እውነቶች

የክርስትና መጽሐፍ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በአያሌ ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ እውነታን ይጻረራል። ለምሣሌ ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ገጽ (ዘፍጥረት 1፥5) ላይ እግዚአብሔር ብርሃንን፣ ጧትንና ሌሊትን በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን እንደፈጠረ ተጠቅሷል። በመቀጠልም ጨረቃን፣ ፀሐይንና ከዋክብትን በአራተኛው ቀን ፈጠረ (ዘፍጥረት 1፥14) እያለ ይቀጥላል። የብርሃን ምንጮች የሆኑት ዘግየት ብለው ከሦስት ቀናት በኋላ የተፈጠሩ ከሆኑ ብርሃን፣ ጧትና ማታ በመጀመሪያው ቀን እንዴት ሊኖሩ ይችላሉ?

ሌላው ምሣሌ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ መሠረት ውኃ (ዘፍጥረት 1፥2) በመጀሪመያው ቀን የተፈጠረ ሲሆን ሳይንስ የሚያረጋግጠው ግን ዩኒቨርስ የጀመረው በጋስ ደመና ዓይነት መሆኑን ነው። ታድያ ጋስ የውቅያኖሶችን ውኃ እንዴት ሊሸከም ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋር የመጋጨቱ ሁኔታ፣ ዛሬ ባለ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አለመሆኑን ያረጋግጣል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለፈጠረው ዩኒቨርስ እውነታ ዐዋቂ ነውና።

የእስላም መጽሐፍ የሆነው ቁርአን ግን ከሳይንሳዊ እውነታዎች ጋር ፈጽሞ አይቃረንም። ይልቅዬ ከቅርብ ዘመን ወዲህ እንኳ በሰው ልጅ ዘንድ ያልታወቁ ሳይንሳዊ እውነታዎችን አጠቃሎ ይዟል።

በርስዎ አመለካከት የትኛው ነው የእግዚአብሔር ቃል? ከሳይንሳዊ እውነታዎች ጋር የሚጻረረው መጽሐፍ ወይስ ሳይንሳዊ እውነታዎችን የሚያረጋግጠው መጽሐፍ? እባክዎን አስተውለው ይምረጡ።

## 50,000 ስሕተቶች

ክርስቲያን ምሁራን መጽሐፍ ቅዱስ ከ30,000 እስከ 50,000 የሚደርሱ በጣም ብዙ ስሕተቶች እንዳሉት አምነው ይቀበላሉ። ስሕተቶቹ በዘመን አቆጣጠር፣ በሳይንሳዊ እውነታዎች፣ በጂዮግራፊ፣ በታሪክ እና በውስጣዊ አለመጣጣሞች እንደሚገለጹም ይናገራሉ።

ሙስሊም ምሁራን ግን መጽሐፋቸው ቁርአን አንዲት ስሕተት እንደሌለበት ያረጋግጣሉ።

የሁለቱንም ወገኖች አባባል ባሉት መሠረት እንቀበልና የትኛውን ነው በእግዚአብሔር ቃልነት የሚመርጡት? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቁርአንን? እራስዎ ይወስኑ? 50,000 ስሕተቶች ያሉበትን መጽሐፍ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው ብለው ይቀበላሉ? እራስዎ ወስነው ይምረጡ።

## ትክክለኛነት

ኢየሱስ ይናገሩት የነበረው ቋንቋ «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?» (ማቴ.27፥46) ውስጥ እንደተረጋገጠው አራማይክ (የሶሪያ ቋንቋ) ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ዐረፍተ ነገር ስለ ኢየሱስ የተዘገበ ብቸኛው የአራማይክ ዐረፍተ ነገር ነው። በአራማይክ የተጻፈ አንድም ወንጌል አይገኝም። በኢዬሱስ ቋንቋ

በአራማይክ (በሶሪያ ቋንቋ) የተነገሩ ትክክለኛና ቀጥተኛ የኢየሱስ ንግግሮች ጠፍተዋል።

የሙሐመድ ቋንቋ ዐረብኛ ነው። ሙሐመድ የተናገሩት ሁሉ ይናገሩት በነበረው ቋንቋቸው በዐረብኛ ኦሪጂናል ቅጂው እንደነበረ ዛሬም ይገኛል።

እዚህ ላይ ሁለት ሰዎች ከፊታችን አሉ። በአንድ በኩል በአራማይክ (የሶሪያ ቋንቋ) ተናጋሪ የነበሩና ስለሳቸው አንድም ነገር በአራማይክ ያልተዘገበ ኢየሱስ ሲሆኑ፣ እሳቸውን አስመልክቶ ዛሬ በእጃችን ያለው መረጃ የጠፉ ኦሪጂናሎች የትርጉም ቅጂ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዐረብኛ ተናጋሪ የነበሩና ስለሳቸው የቀረቡ ዘገባዎች በሙሉ ነቢዩ ይናገሩ በነበረው ዐረብኛ ቋንቋቸው ተጠናቅረው የምናገኛቸው ሙሐመድ ናቸው።

በርስዎ ግምት ከነኚህ ሁለቱ ሰዎች ስለየትኛው የቀረበ ዘገባ ነው ትክክለ ኛውና ሰነዳዊነቱ አስተማማኝ የሆነው? ኢየሱስን የሚመለከቱ ዘገባዎች ወይስ ሙሐመድን የሚመለከቱ ዘገባዎች? እስኪ አንዴ በተመሳሳይ መመዘኛ ይመዝኑ። የትኞቹ ዘገባዎች ናቸው ይበልጥ ተአማኒነት ያላቸው? ሕልውናቸው ካከተመ ኦሪጂናሎች የተተረጐሙ ዘገባዎች ምን መሆን ይችላሉ?

## ተቃርኖዎች

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ብትላቸውም፣ አራቱ የሐዲስ ኪዳን ወንጌሎች በተመሳሳይ ሁነቶች ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ልዩነቶች ያሳያሉ።

በእስላም ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቁርአን ግን አንዳች ውስጣዊ አለመጣጣምም ሆነ ተቃርኖ የለበትም።

ለክርክርና አንድን ጉዳይ አንዴ ለመያዝ ሲባል እያንዳንዱ ወገን «ነው» የሚለውን ነገር እንደ እውነት እንቀበልና የተኛው ነው ለርስዎ ይበልጥ መለኮታዊ ሆኖ የሚታየው? በመቶዎች የሚቆጠሩ የወንጌሎችን የርስበርስ ቅራኔዎች ያካተተው ሐዲስ ኪዳን ወይስ አንዳች ውስጣዊ ቅራኔ የሌለው ቁርአን? የቤተ

ክርስቲያን ሰዎች የወንጌሎች የርስበርስ አለመጣጣምና ተቃርኖ መንሥኤው የሰብዓዊ ፍጡር የዘገባ አቀራረብ ልዩነቶች ናቸው ይላሉ። በነርሱ እምነት መሠረት ግን ወንጌሎች የሰብዓዊ ፍጡራን ዘገባዎች አለመሆናቸውን እናስ ታውስ። በቤተክርስቲያን እምነት መሠረት ወንጌሎች የእግዚአብሔር ቃልና ራእይ ናቸውና። ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል ከሆኑ ወንጌሎች እንዴት እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ? በአንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃልና የሰብዓዊ ፍጡራን ትረካዎች ሊሆኑ አይችሉም።

እንደ የእግዚአብሔር የጠራ ቃል የትኛውን ነው የሚቀበሉት? ከአራቱ ተጻራሪ ወንጌሎች ጋር ሐዲስ ኪዳንን ወይስ ከማይናጋ ቋሚ ወጥነቱና የተሟላ ፍጹማዊ መጣጣሙ ጋር ቁርአንን?

## ምርጫውን ማን አካሄደው?

በአንድ ወቅት ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ወንጌሎች እንደነበሩና ከነኚህ ውስጥ ቤተክርስቲያን አራቱን ማለትም የማቴዎስን፣ የማርቆስን፣ የሉቃስንና የዮሐ ንስን ወንጌሎች ብቻ እንደመረጠች ክርስትና ይናገራል። ቀሪዎቹ ወንጌሎች እንዲቃጠሉ ወይም እንዲጠፉና እንዲወድሙ ተደርገዋል።

እስላም ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን አንድ ነጠላ የቅዱስ ቁርአን ቅጂ ብቻ መኖሩንና ተመሳሳይ የማማረጥ ሂደት አለመደረጉን ወይም አለማስፈለጉን ይናገራል።

ለመሆኑ ቤተክርስቲያን ምርጫውን በምን መሠረት ላይ ተመርኩዛ ነው ያካሄደችው? ለምንስ እነኛ አራት ወንጌሎች ብቻ በተለይ ተመረጡ? ለምን ሦስት ወይም አምስት ወይም ደግሞ አሥር ወንጌሎች አልተመረጡም? የተቀ ሩት ወንጌሎችስ ለምን አልተመረጡም? ወንጌሎችን የመምረጥና የማስወገድ መብት ያለው ማነው? ያን መብትስ ማን ሰጠው? ወንጌሎች የእግዚአብሔር ቃል ከሆኑ ዘንዳ ሌሎቻቸው መወገድ የሚኖርባቸው ለምን ይሆን?

የትኛው ሃይማኖት ነው ይበልጥ ተአማኒና ይበልጥ አስተማማኝ ሆኖ የሚሰማዎት? መጽሐፎቹ በድምፅ ብልጫ የተመረጡለት ሃይማኖት ወይስ አንድ ብቸኛ መጽሐፉ ከእግዚአብሔር የተላለፈለት ሃይማኖት? እያንዳንዱ ሃይማኖት ስለራሱ ያለውን ነገር እንደ እውነት እንቀበልለትና ሁለቱንም በዚሁ መሠረት እንመዝናቸው። ሐቀኛ የሆነ ገለልተኛ ፈራጅ ወይም ዳኛ አድርገን ራሳችንን እናቅርብ። ለአፍታ ያህል የራሳችንን ማንነትና ወገናዊነት እንርሳና ፍትሐዊ ብይን እንስጥ።

## ኦሪጂናል ቋንቋ

የማቴዎስ ወንጌል መጀመሪያ የተጻፈበት ኦሪጂናል ቋንቋ የዕብራይስጥ ቋንቋ መሆኑን ክርስትና ይናገራል። ግና የዕብራይስጥ ኦሪጂናል ቅጂው የትም የለም፤ ፈጽሞ ጠፍቷል። ዛሬ የሚገኘው ከዚህ ከጠፋው ቅጂ በሌላ ቋንቋ የተተረጎመ የትርጉም ቅጂ ብቻ ነው።

የእስላም መጽሐፍ የሆነው የቁርአን ቋንቋ ዐረብኛ መሆኑን እስላም ይናገራል። በኦሪጂናል ቋንቋው በዐረብኛ የተጻፈው ቁርአን ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ በዚያ ኦሪጂናል ቋንቋው ነበረ፤ ዛሬም እንደነበረ አለ።

ከትክክለኛነት መመዘኛ አኳያ የትኛው መጽሐፍ ነው ይበልጥ አስተማማኙ? ኦርጂናሉ የጠፋ መጽሐፍ ወይስ ኦሪጂናሉ ዛሬም የሚገኝ መጽሐፍ? ለትክክለኛነቱና ለተአማኒነቱ የትኛውን የበለጠ ይመርጣሉ?

## ብዙ የተለያዩ ቅጂዎች ወይስ አንድ ብቸኛ ወጥ ቅጂ?

የክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ አያሌ የተለያዩ ቅጂዎች ያሉት ከመሆኑም ባሻገር በማያቋርጥ የመለዋወጥ ሂደት ውስጥ ያለና ከጊዜ ወደ ጊዜ ክለሳና ማሻሻያ የሚካሄድበት መጽሐፍ ነው።

የእስላም ቁርአን ግን ከነቢዩ ሙሐመድ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ላለፉት አሥራ አራት ምዕተ ዓመታት አንድ ብቸኛ ኦሪጂናል ቅጂ ብቻ ነው ያለው። የቁርአን ቅጂዎች በሙሉ አንድና ተመሳሳይ ናቸው። በዓለም ላይ የሚገኙ የቁርአን ቅጂዎች በሙሉ በአንዲት ቃል አይበላለጡም ወይም አይተናነሱም።

የትኛው መጽሐፍ ነው ይበልጥ መለኮታዊ? ብዙ የተለያዩ ቅጂዎች ያሉትና ቀጣይነት ላለው ለውጥና ክለሳ የተዳረገው መጽሐፍ ወይስ የማይለወጥና ቋሚ የሆነ አንድ ብቸኛ ቅጂ ያለው መጽሐፍ? የበለጠ ቅድስናና ብጽእና ያለው የትኛው ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ቅዱስ ቁርአን? ሁለቱንም የማናውቅ ነን እንበልና በመጽሐፍ ቅዱስ ተለዋዋጭነትና ቅጂ–ብዙነት አንጻር በቁርአን የማይናጋ ቋሚነትና አንድ ብቸኛ ቅጂነት መሠረት ላይ በመመርኮዝ እስኪ ገለልተኛ ዳኝነት እንስጥ። የትኛው ነው የእግዚአብሔር መጽሐፍ? ለዘመናት በማያቋርጥ ሁኔታ የሚለዋወጠው መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ከእግዚአብሔር እንደተገለጸ እሱነቱን ጠብቆ የቆየው ቅዱስ ቁርአን?

## ሐዋርያ ወይስ ነቢይ?

ዮሐንስ፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ወንጌሎቻቸውን ለመጻፍ ከእግዚአብሔር ራእይ የተገለጸላቸው ሲሆን፣ የክርስትና እምብርት የሆኑት ኢየሱስ ራሳቸው ግን ከእግዚአብሔር ምንም ራእይ እንዳልተገለጸላቸው ክርስትና ይናገራል።

እስላም ግን ራእይ (ወሕይ) ከእግዚአብሔር ወደ እያንዳንዱ ነቢይ መምጣት ያለበት ሲሆን ነቢዩ በተራው መልዕክቱን ለሕዝብ የሚያስተላልፍ መሆኑን ይናገራል።ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ደቀመዛሙርት ከእግዚአብሔር ራእይ ተገለጸላቸው፣ ነቢዩ ራሳቸው ማለትም ኢየሱስ ግን ምንም ራእይ ከእግዚአብሔር አልተቀበሉም ማለቱ ለግንዛቤ የሚቸግርና የማይዋጥ ነገር መሆኑን እስላም ይናገራል። የእስላም ነቢይ የሆኑት ሙሐመድ ከእግዚአብሔር

ራእይ (ወሕይ) የተላለፈላቸው ሲሆን እሱም ቅዱስ ቁርአን ነው። ሌላው ቀርቶ የነቢዩ ንግግሮችም በራእይ የተላለፉላቸው ናቸው።

ለርስዎ ይበልጥ ተቀባይነት ያለው የትኛው ነው? መሥራቹ ነቢይ አንዳች ራእይ ያልተቀበለበት ሃይማኖት ወይስ ነቢዩ ራእይ የተቀበለበት ሃይማኖት? የትኛውን ነው የሚመርጡት? መከተል የሚመርጡት የነቢዩን ደቀመዛሙርት ወይስ ራሱን ነቢዩን ነው?

## ውስጣዊ አለመጣጣሞች

የሐዲስ ኪዳን ወንጌሎች ተመሳሳይ የሆነ አንድ ሁነት አስመልክተው እርስ በርሳቸው የሚፋለሱ ተጻራሪ ትረካዎች ያቀርባሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንዱ ወንጌል ራሱን በራሱ ሲቃረን ይታያል። በአንዱ ወንጌል ውስጥና በተለያዩ ወንጌሎች መካከል በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ቅራኔዎች ይስተዋላሉ። ይህም የሚያረጋግጠው እነኚህ ወንጌሎች የሰብዓዊ ፍጡራን ዘገባዎች እንጂ መለኮታዊ ራእዮች አለመሆናቸውን ነው። እግዚአብሔር እውነቱን ሁሉ ስለሚያውቅ እርስ በርሳቸው የሚፋለሱ ተጻራሪ ዘገባዎችን ሊሰጥ አይችልም። ይህ ማለት ደግሞ ሐዲስ ኪዳን ከእግዚአብሔር በራእይ (ወሕይ) የተላለፈ መጽሐፍ አይደለም ማለት ነው። አይቀሬው ማጠቃለያም ክርስትና በመለኮታዊ ራእይ የተገለጸ መጽሐፍ የለውም የሚል ይሆናል። ሰባኪው ቤተክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን በመያዝ «የእግዚአብሔር ቃል» በማለት ሲገልጸው እውነቱን እየተናገረ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ቢሆን ኖሮ በብዙ መቶዎችና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ውስጣዊ ቅራኔዎች ባላካተተ ነበር።

በተቃራኒው ግን ቁርአን ስለአንድ ሁነት ወጥ የሆነ አንድ ትረካ ይሰጣል። ምንም ዓይነት ውስጣዊ አለመጣጣም ፈጽሞ አይታይበትም።

ታድያ የትኛው ነው የእግዚአብሔር ቃል? በሺዎች የሚቆጠሩ ውስጣዊ ቅራኔዎችን ያቀፈው መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ፍጹም ወጥነት ያለውና ትክክለኛ የሆነው ቁርአን?

# ጳውሎሳዊነት ወይስ ክርስትና?

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ሦስት በአንድ ውስጥ ነው አላሉም፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝም አላሉ፤ መድህን የሚገኘው በስቅለት ነው ብለውም አያውቁም። የሰው ልጅም በተፈጥሮው ኃጢአ ሆኖ ተፈጠረ ብለው አልተናገሩም። እግዚአብሔር ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብለውም አያውቁም። ዛሬ ክርስትና የሚያስተምረው ኢየሱስ ያስተማሩትን በቀጥታ የሚጻረር ነው።

ክርስትና ዛሬ ባለው መልኩ በአብዛኛው የጳውሎስ የፈጠራ ውጤት ነው። ቤተክርስቲያን ለጳውሎስ ሚዛናዊ አመለካከት ቢኖራት ኖሮ ሃይማኖታቸውን ጳውሎሳዊነት ብላ እንጂ ክርስትና ብላ ባልጠራች ነበር። ሃይማኖቱ በስማቸው የተሰየመው ኢየሱስ ክርስቶስ በሃይማኖቱ መሠረታዊ እምነቶች ላይ ጭራሽ አይስማሙምና። ስለዚህም ክርስትና አላግባብ ነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተሳሰረው። ጳውሎሳዊነት ይበልጥ ታማኝና ፍትሐዊ መጠሪያ ስሙ ነው።

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሁሉ እግዚአብሔር የኢየሱስን ትምሕርቶች «ክርስትና» ብሎ ፈጽሞ አልሰየመም። «ክርስትና» የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይ ኪዳንም ይሁን በሐዲስ ኪዳን የትም ቦታ ላይ አልተጻፈም። እግዚአብሔር ክርስትናን የማጠቃለያው ሃይማኖት ቢያደርገው ኖሮ ስም በሰጠው ነበር።

የክርስትና እምነቶች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። «ክርስትና» የሚለው ቃል ራሱ የተፈጠረው በቤተክርስቲያን ሰዎች ነው። ክርስትና ከእምነቶቹና ከመጠሪያ ስሙ ጭምር የተፈጠረው በኢየሱስ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ሰዎች ነው።

በተቃራኒው እስላማዊ እምነቶች፣ ሕግጋት፣ የአምልኮ ተግባራትና የሥነ ምግባር ሕጉ ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር የተላለፉ መለኮታዊ ራእዮች ናቸው። ክርስትና በቤተክርስቲያን ሰዎች እንደተሠራው ዓይነት፣እስላም በምሁራን (ዓሊሞች) የተሠራ አይደለም። እስላም በመሠረታዊ የእምነት መርሆ

ዎቹም ሆነ በአጠቃላይ ሕግጋቱ፣ ቁርአን ውስጥ የሠፈረ የአላህ ቃልና የነቢዩ ሙሐመድ ሱንና ነው።

በመለኮታዊነቱ የትኛውን ይመርጣሉ? በጳውሎስና በቤተክርስቲያን ሰዎች ተፈጥሮ የተሠራውን ክርስትና ወይስ ከእግዚአብሔር የተላለፈውን እስላም?

## የሠላምታና የመልካም ምኞት መግለጫ ደብዳቤዎች

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በጳውሎስ መልእክቶች መጨረሻ ላይ፣ ጳውሎስ ሁልጊዜ በሌሎች ከተሞችና አገሮች ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች የግል ሠላምታውንና የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክቱን ሲልክላቸው እናነባለን። እውነቱን ለመናገር ማሕበራዊ ተግባቢና ዐመለ ሸጋ ትሑት መሆን ምንም ስሕተት የለበትም።

ችግሩ ከፊታችን የሚደቀነው የሚከተለው ጥያቄ ሲነሳ ነው:- በጳውሎስ መልእክቶች መጨረሻ ላይ የግል ሠላምታዎቹንና የመልካም ምኞት መግለጫ ዎቹን ሲያነቡ እነኛ ሠላምታዎች ከእግዚአብሔር የተላለፉ መለኮታዊ ራእይ ሆነው ይሰማዎታል? ቤተክርስቲያን ግን የጳውሎስ መልእክቶች የእግዚአብ ሔር ራእይ ናቸው ትለናለች። እግዚአብሔር በመለኮታዊ ራእዩ ውስጥ ጳውሎስ ለወዳጆቹ የላካቸውን ሠላምታዎች ያካትታል?

እኒያ የጳውሎስ የሠላምታ ደብዳቤዎች በአስረጅነታቸው ጳውሎስን የሚደግፉ አይደሉም። የጳውሎስ መልእክቶች ቅንጣት መለኮታዊ ራእይ የሌለባቸው የራሱ የግል ሥራ ውጤት መሆናቸውን ያረጋግጣሉና።

ማንም ሰው እውነትን ለዘላለም መደበቅ አይችለም። ተደጋግሞ እንደ ሚባለው ሁሉ የተወሰኑ ሰዎችን ለተወሰነ ጊዜ ማታለል ይቻላል፣ መላውን ሕዝብ ሁልጊዜ ማታለል ግን አይቻልም። የጳውሎስ ደብዳቤዎች የጳውሎስ ደብዳቤ ዎች ናቸው። ስለ ደብዳቤዎቹ ማለት የሚቻለው እውነትም ይኸው ብቻ ነው። ጳውሎስ መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) ተቀብሎ አያውቅም።የኢየሱስን ትም ሕርቶች ያቃለለ፣ የሙሴን ሕግ የሰረዘና አዲስ ሃይማኖት የመሠረተ ሰው ነው—ጳውሎስ።

እስላም ደግሞ ከኢየሱስ በኋላ ከሙሐመድ በስተቀር ሌላ ነቢይ አልተነሳም ይላል።በኢየሱስና በሙሐመድ መካከል የተላከ ነቢይ በጭራሽ የለም። ከሙሐመድ በኋላም ምንም ነቢይ አልመጣም፣አይመጣምም። አላህ ቁርአን ውስጥ ይህን ግልጽና ቁልጭ ባለ ሁኔታ ተናግሯል። የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ወይም ሐዋርያት ሐዋርያት ብቻ ናቸው። መለኮታዊ ራእይ ፈጽሞ አልተላለፈ ላቸውም። የኢየሱስ ሳይሆን የኢየሱስ ደቀመዝሙር ተግሪ የነበረው ጳውሎስም ምንም ዓይነት መለኮታዊ ራእይ አልተላለፈለትም። ለዚህ ማስረጃው የመልእ ክቶቹ ይዘት፣ ግላዊ ሠላምታዎቹና የልባዊ ምኞት መግለጫ ደብዳቤዎቹ፣ በኢየሱስና በትምሕርቶቻቸው ላይ የፈጸመው ድርጊቱ፣በሙሴ ሕግ ላይ የሠ ራው ሥራና ግልጥልጥ ባለ ሁኔታ እርሱ ራሱ የተናገረው ቃሉ ነው። ጳውሎስ በሕልሙ ኢየሱስን ማየቱንና ቃሉን መስማቱን አምኗል (የሐዋ.ሥራ 26፥19)። ታዲያ ሕልምን እንደ መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) መቀበል እንች ላለን? ይህ ከሆነ ደግሞ ሕልመኞች ሁሉ የመለኮታዊ ራእይ ተቀባዮች ናቸው ማለት ነው! ይህ ማለት ደግሞ በተራው ሕልመኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል አስተላላፊዎች ናቸው ማለት ይሆናል!ይህ ከሆነ ሕልመኞች ሁሉ ነቢያት ናቸው ማለት ነው! ከዚህ በመነሳትም ሰዎች ሁሉ ነቢዮች ናቸው ማለት ይመጣል!

ታዲያ እርስዎ የጳውሎስን ሠላምታና ለተወሰኑ ወዳጆቹ ያስተላለፋቸውን የመልካም ምኞት መግለጫ ደብዳቤዎች መለኮታዊ ራእይ ነው ብለው መቀበል ይችላሉን? የጳውሎስን ሕልም እንደ መለኮታዊ ራእይ መቁጠር ይቻላል?

## የታረመውና የተከለሰው መጽሐፍ ቅዱስ

«የታረመው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም» (The Revised Version of the Bible) የተሰኘ የመጽሐፍ ቅዱስ እትም አለ። «የታረመው» ማለት የ«ተስተካከለው፣ የተቃናው ...» ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፣ ቃሉን የማቃናት የማረምና የመከለስ መብት ያለው ማንም ፍጡር የለም። የእግዚአብሔርን ቃል የማሻሻል፣ የመቀነስ፣ የመጨመርም ሆነ የመሰ ረዝ ሥልጣን ማንም የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ ከለሳና እርማት የሚያሻው

እስከ ሆነ ድረስም የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን አይችልም። በተጨባጭ እንዴ ከተሻሻለና ከታረመም መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ያህል የእግዚአብሔር ቃል አይደለም።

በተቃራኒው ግን የእስላም ቅዱስ መጽሐፍ የሆነው ቁርአን የታረሙና የተሻሻሉ እትሞች የሉትም። ታርሞ ተሻሽሎ ወይም በአሕጽሮት (Abridged) ተጽፎም ፈጽሞ አያውቅም። ዛሬ በሰው ልጆች እጅ የሚገኝ የጠራና የነጠረ የእግዚአብሔር ቃል ያቀፈ ብቸኛው መጽሐፍ ነው።

የእግዚአብሔር ንጥር ቃል አድርገው የትኛውን ይመርጣሉ? የታረመ ውንና የተከለሰውን መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ያልተለወጠውንና ያልተከለሰውን ወጥ የእግዚአብሔር ቃል ቁርአን?

## የትኛው መጽሐፍ ቅዱስ?

መጽሐፍ ቅዱስ ብለን ስንናገር አንድ የተለየ ነጠላ ጥራዝ እየጠቀስን አይደለም። በይዘት ረገድ ሰፊ ልዩነቶች ያሏቸው ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች ይገኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ከእትም እትም ይለያያል። የለንደን እትሞች፣ የሮማ እትሞች፣ የበይሩት እትሞችና ሌሎችም እትሞች በአንድ ተመሳሳይ ቋንቋ የሚታተሙ እንኳ ብዙ ልዩነቶች አሏቸው።

ፕሮቴስታንቶች በባለ 39–መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን ያምናሉ። ካቶሊኮች በባለ 46–መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን ያምናሉ። የካቶሊኮች መጽሐፍ ቅዱስ በፕሮ ቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጨማሪ ሰባት መጽሐፎች አሉት። የሰማር ያውን ብሉይ ኪዳን ደግሞ በሰላሳ ዘጠኝ ወይም አርባ ስድስት ፈንታ አምስት መጽሐፎች ብቻ ያካትታል[1]። ታድያ ከነኚህ ውስጥ የትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው መጽሐፍ ቅዱስ? ማንም አያውቅም።

1 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደግሞ ከብሉይ ኪዳን 46 መጽሐፎች ከሐዲስ ኪዳን 35 መጽሐፎች በድምሩ 81 መጽሐፎች ያሉትን መጽሐፍስ ቅዱስ ትቀበላለች–ተርጓሚው

በተቀራኒው የእስላም ቅዱስ ቁርአን ደግሞ አንድና አንድ ብቻ ነው። የተለያዩ እትሞች የሉትም። ቅጂዎቹ በሙሉ ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ይዘት ነው ያላቸውና የነበራቸው። ቃል በቃል፣ ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽ በአንቀጽና ምዕራፍ በምዕራፍ የፊደል ልዩነት እንኳ የላቸውም።

ታድያ የትኛው መጽሐፍ ነው ቅዱስ እና እውን የአላህ ቃል የሆነው? የተለያዩ በርካታ እትሞችና አወዛጋቢ ይዘቶች ያሉት መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ አንድ ብቸኛ እትም ያለው ቁርአን?

## የመጽሐፉ መጠሪያ ስም

የክርስትና መጽሐፍ ስሙ መጽሐፍ ቅዱስ (The Bible) ነው። ይሁን እንጂ «መጽሐፍ ቅዱስ» (Bible) የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ሥፍራ አልተጠቀሰም። በጣም የሚገርመው የመጽሐፉ መጠሪያ ስም ወይም ርዕስ መጽሐፉን በገለጸው ወገን ያልተሰጠ መሆኑ ነው። በዚህ ስም የጠሩት ምሁራን ናቸው። እግዚአብሔር አንድን መጽሐፍ ካስተላለፈ እሱ ራሱ የመጽሐፉን መጠሪያ ስም በዚያው መጽሐፍ ውስጥ የሚሰጥ መሆኑ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር መጠሪያ ስም ወይም ርዕስ ሳይሰጠው እንዴት መጽሐፍ ያስተላልፋል? ሌላው ቀርቶ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን የተሰኙት ስሞች እንኳ በራእይ የተገለጡ ስሞች አይደሉም።

የእስላም መጽሐፍ እንደምናውቀው ሁሉ ቁርአን ነው። «ቁርአን» የሚለው ቃል በራሱ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል። ቁርአን የተሰየመው ቁርአንን ባስተላለፈው እግዚአብሔር ነው።

የትኛው መጽሐፍ ነው ይበልጥ መለኮታዊ የሚመስልዎት? መጽሐፍ ቅዱስ (Bible) ተብሎ በእግዚአብሔር ያልተሰየመው ወይስ ቁርአን ተብሎ በእግዚአብሔር ስም የተሰጠው መጽሐፍ? በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ውስጥ «መጽሐፍ ቅዱስ» (Bible) የሚል ቃል ያልተካተተ ሲሆን፣ ቁርአናዊ አንቀጾች ውስጥ ግን «ቁርአን» የሚለው ቃል ተካቷል። በሌላ አባባል መጽሐፍ

ቅዱስ በዚህ ስም የተሰየመው በቤተክርስቲያን አማካይነት ሲሆን፣ ቁርአን ግን «ቁርአን» ተብሎ የተሰየመው በእግዜአብሔር ነው። ታድያ የትኛው ነው የእግዚአብሔር ትክክለኛ መጽሐፍ? በሰዎች የተሰየመው ወይስ በእግዚአብሔር የተሰየመው? በጉዳዩ ላይ ራስዎ ያስቡበትና የራስዎን ውሳኔ ይስጡ።

## የሃይማኖቱ መጠሪያ ስም

ክርስትና እንደሚለው ሃይማኖቱ ለመድህን በእግዚአብሔር የተመደበ ሃይማኖት ነው። ይህ እውነት ከሆነ እግዚአብሔር «ክርስትና» የሚለውን ስም የክርስትና መጽሐፍ በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይ ይጠቅሰው ነበር። በእጅጉ የሚደንቀው ግን «ክርስትና» የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ቦታ ፈጽሞ ያልታየና ያልተጠቀሰ መሆኑ ነው። ሃይማኖቱን እግዚአብሔር ስም አልሰጠውም። ኢየሱስም ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው አልጠሩም። ደቀመዛሙርቱን ሐዋርያትም ክርስቲያኖች ብለው በጭራሽ አልጠሯቸውም።

እስላም ለሰው ልጆች መድህን የሚያስገኝ የአላህ ሃይማኖት መሆኑን ይናገራል። «እስላም» የሚለው ይህ መጠሪያ ስም በመለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) በተላለፈው የእስላም መጽሐፍ –ቁርአን– ውስጥ በተለይ ተጠቅሶ ይገኛል። ሙሐመድም ተከታዮቻቸውን «ሙስሊሞች» ብለው ጠርተዋል። ቁርአንም ምእመናንን «ሙስሊሞች» ብሎ ይጠራቸዋል።

ታድያ የትኛው ሃይማኖት ነው የበለጠ መለኮታዊ መስሎ የሚታየው? በራሱ መጽሐፍ ውስጥ ስሙ ጭራሽ ያልተጠቀሰው ክርስትና ወይስ በመጽሐፉ ውስጥ ስሙ በግልጽ የተቀመጠው እስላም? የትኛው ሃይማኖት ነው በእግዚአብሔር መንገድ ላይ ያለው? በተከታዮቹ አማካይነት መጠሪያ ስም የተሰጠው ወይስ ስያሜውን ቁርአን ውስጥ ከእግዚአብሔር ያገኘው? እግዚአብሔር ክርስትናን ሃይማኖት እንዲሆን ቢሻው ኖሮ ክርስትና ብሎ በሰየመው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር «እስላም»ን ቁርአን ውስጥ የሰየመው ሲሆን «ክርስትና»ን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልሰየመም። «እስላም» በእስላም መጽሐፍ ውስጥ

በእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ነው። «ክርስትና» ግን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልሰፈረና በቤተክርስቲያን ሰዎች የተፈጠረ ስያሜ ነው።

## እውነተኛው መፈታተኛ

ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚደረግ የፀሎት ሥነ ሥርዓት ላይ ሰባኪው ለታዳሚው የሚያነበው ቀደም ብሎ ተመርጠው የተዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን ነው። የቤተክርስቲያን ሰባኪያን ለማንበብ ፈጽሞ የማይደፍሯቸው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ። ለምን? አንዳንዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የቤተክርስቲያኗን ትምሕርቶች ይቃረናሉ፤ አንዳንዶቹ ጥቅሶች ደግሞ በተመሳሳይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሌሎች ጥቅሶችን ይጻረራሉ፤ አንዳንዶቹ ጥቅሶች ጭራሹኑ የመለኮታዊ ራእይ ርዕስ ጉዳይ ሊሆኑ የማይችሉ ሌጣ የታሪክ ዘገባዎች ናቸው። አንዳንዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ደግሞ ተጨባጭና ቋሚ የሆኑ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ይጻረራሉ። ሌሎቹ ከተራ ሎጂክና ከጤነኛ አእምሮ ግንዛቤ ጋር ይጻረራሉ። አንዳንዶቹ ጥቅሶች ነቢዮችን ኃጢአንና ተራ ወንጀለኞች አድርገው ያሳያሉ። ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን የማይችል ወራዳ የወሲብና የብልግና ቋንቋ ይጠቀማሉ።

በሌላ አገላለጽ የቤተክርሲያን ሰባኪው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ማንበብ እንዳለበት አስቀድሞ የሚመርጠው ይህን ማድረግ ስለሚኖርበት ነው። እንዳው ዝም ብሎ መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ ዐይኑ ያረፈበትን መስመር ማንበብ አይችልም።ያን ማድረግ ውጤቱ የከፋ ይሆናል።መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰባኪው ቢያነባቸው የመጽሐፉን ‹ቅድስና› የሚያረክሱና የሚያንቋሽሹ አንዳንድ ጥቅሶች ስለሚገኙ ሰባኪው ሊያነባቸው አይችልም።

በተቃራኒው ግን ሙስሊሙ ሰባኪ ከቁርአን ውስጥ የሚደብቀው አንዳች ቃል የለም። ማንኛውንም ምዕራፍ ወይም አንቀጽ ማንበብ ይችላል። ቁርአን ባካተታቸው ይዘቶች በሙሉ ኩራት ይሰማዋል። ማንበቡ የሚያሳፍረውና የሚያሸማቅቀው አንዳች ነገር ቁርአን ውስጥ የለም። አብዛኞቹ ሙስሊሞች በየዕለቱ

ከቁርአን ብዙ ክፍሎች ያነባሉ፣ ያነበንባሉ። ቁርአንን በቃላቸው ሙሉ በሙሉ አጥንተው የያዙ አያሌ ሙስሊሞች ይገኛሉ። በፍቺው፣ በይዘቱ፣ በጭብጦቹ፣ በመለኮታዊ ትእዛዛቱ፣ በሕግጋቱ፣ በመርሆዎቹ፣ በሥነምግባርና በግብረገብነት ደንቦቹ፣ በሥርዓተ አምልኮ መመሪያዎቹና በቋንቋ ውበቱ ልዩና ድንቅ የሆነ መጽሐፍ ነው።

ታድያ የትኛውን ነው የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው የሚመርጡት? የመጀመሪያውን ወይስ ሁለተኛውን መጽሐፍ? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቅዱስ ቁርአንን? ምርጫውም ኃላፊነቱም የራስዎ ነው።

## መነሻና መድረሻ

መጽሐፍ ቅዱስ መነሻውን ወይም ግቆሚያውን የሚለይ በመለኮታዊ ራእይ የተላለፈ አንቀጽ የለውም። ቁርአን ግን በፍቺውና በይዘቱ ብቻ ራእዩ ከየት ተጀምሮ የት ላይ እንዳለቀ ሚያሳይ መለያ አንቀጽ አለው። ለምሳሌ ያህል እንዲህ ይላል:-

«አንብብ፥ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም።» (ቁርአን 96:1) የመለኮታዊውን ራእይ ማጠቃለያና መጨረሻ የሚያመለክት አንቀጽም አለው:-

«..ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤»(ቁርአን 5:3)

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የሰው ልጅ ሃይማኖት ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር የመረጠው ስለመሆኑ ጭራሽ የሚለው ነገር የለም። ሌላው ቀርቶ መጽሐፍ ቅዱስ «ክርስትና» የሚለውን ቃል እንኳ አላነሳም። ቁርአን ግን የእስላምን ሃይ ማኖት መጠሪያ ስም ራሱ ተናግሮ የመለኮታዊው ራእይ (ወሕይ) የተጀመ ረበትንና ሲጠቃለልም የተደመደመበትን ለይቶ በማስቀመጥ ከእግዚአብሔር

ሲተላለፍ የቆየው መለኮታዊ ሃይማኖት ተሟልቶ ከፍጻሜው የደረሰበትን አንቀጽ ያመለክታል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ቢሆን ኖሮ ቃሉ የተጀመረበትና የቆመበትን የሚያሳዩ መለያ ምልክቶች እውስጡ በተመለከቱ ነበር።

ታድያ የትኛው መጽሐፍ ነው የጠራ የእግዚአብሔር ቃል መስሎ የሚታይዎ? መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ቁርአን?

## የዘመን ጉዳይ

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ከሙሴ ዘመን ማለትም ከ1213 ቅ.ክ. ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ማለትም እስከ 100 ዘ.ክ. አካባቢ ባሉት ዘመናት ውስጥ ነው። ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ያበቃው በአንድ ሺህ ሦስት መቶ ዓመታት ያህል ውስጥ ሲሆን የተጻፈውም በሚታወቁና ማንነታቸው በውል በማይታወቅ ብዙ ቁጥር ባላቸው ጸሐፊዎች አማካይነት ነው ማለት ነው።

ቁርአን ግን ከእግዚአብሔር በመለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) ተላልፎ የተጠናቀቀው በሃያ ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህም የነቢዩ ሙሐመድ ተልእኮ የአርባ ዓመት ጉልማሳ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ነቢዩ በስልሳ ሦስት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ባረፉበት ጊዜ መከከል የነበረው ዘመን ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ሕሊናዎ በእርካታ የሚቀበለው የትኛውን መጽሐፍ ነው? በአንድ ሺ ሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ በሃያ ሦስት ዓመታት ውስጥ ብቻ ተላልፎ ያበቃውን ቁርአን?

## ቅዱስ ነው ወይስ አይደለም?

ክርስቲያን ምሁራን አምነው በሚቀበሉት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ስሕተቶች አካቷል። እኒያን ስሕተቶች በዝርዝር የሚያቀርቡ

ብዙ መጽሐፎች ተጽፈዋል። የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ራሱ በዚህ ርዕስ ላይ በዐረብኛ ሁለት መጽሐፎች ጽፎአል። አንደኛው የብሉይ ኪዳንን ስሕተቶች ሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው የሐዲስ ኪዳን ስሕተቶችን የሚያሳይ ነው።

መጸሐፍ ቅዱስ ከ30,000 እስከ 50,000 የሚደርሱ ስሕተቶች ያሉበት ከሆነ የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን አይችልም። ተአማኒነት ያለው መጽሐፍ መሆ ንም አይችልም። አስተማማኝ ምንጭና ዋቢም መሆን አይችልም። «ቅዱስ» ሊሆንም አይችልም።

በአጭሩ የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ስለማይችል ክርስትና መጽሐፍ ቅዱ ስን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ አይጠቅሰውም። እግዚአብሔርም 50,000 ስሕተቶች ያሉበት መጽሐፍ አይልክም!! ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ጸሐፊ እንኳ ይህ ሁሉ ስሕተት ያለበት መጽሐፍ አይደርስም።

«መጽሐፍ ቅዱስ» የተባለው በተጨባጭ «ቅዱስ» አይደለም። ትክክለኛ አእምሮ ያለው ማንም ሰው 50,000 ወይም 30,000 ስሕተቶች ያካተተውን መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ወይም «ቅዱስ» ብሎ ሊጠራ አይችልም።

በተቃራኒው ግን ቁርአን አንዳች ስሕተት የለበትም። ያለውም በአንድ ነጠላ ቅጂው ወይም እትሙ ነው። ተከልሶ ወይም ተሻሽሎና ታርሞም አውያቅም፤ ወደፊትም አይሆንም።

ታድያ አስተማማኝ ለሆነ መለኮታዊ መመሪያነት የትኛውን መጽሐፍ ይመ ርጣሉ? 50,000 ስሕተቶችን ያቀፈው መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ስሕተት አልባ ውን ቁርአን?

# ምዕራፍ 2

# አምላክ

# በሁለቱ ሃይማኖቶች ዘንድ

## ሥላሴ

ክርስትና በሥላሴ ማለትም እግዚአብሔር ሦስትም አንድም ነው ብሎ ያምናል። ይሁን እንጂ ይህ የሥላሴ እምነት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ፈጽሞ አልተጠቀሰም። ሌላው ቀርቶ «አንድም ሦስትም» የሚለው ሐረግ እንኳ አልተመለከተም። ይህ ማለት የሥላሴ እምነት በቤተክርስቲያን የተሠራ አዲስ ፈጠራ ነው ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የእግዚ አብሔር ቃል አድርጋ ከምትወስደው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

እስላም እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው ብሎ ነው የሚያምነው። የእስላም መጽሐፍ የሆነው ቅዱስ ቁርአንም እንደዚሁ ይላል።

የትኛው ሃይማኖት ነው የራሴ ነው ለሚለው መጽሐፉ የሚገዛው? ክርስትና ወይስ እስላም? ቤተክርስቲያን የምታስተምረውን የሥላሴ እምነት መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም። እስላም ቁርአን የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ፍጹማዊ አንድነት አጥብቆ ይከተላል። ታድያ የትኛው ሃይማኖት ነው የገዛ ራሱን መጽሐፍ የሚያከብረው? ክርስትና ወይስ እስላም? ከገዛ ራሱ ጋር የበለጠ የሚጣጣመው የትኛው ሃይማኖት ነው?

## የአንድ አምላክ እምነት ወይስ የአምላክ—ብዙነት እምነት?

ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ሦስትም አንድም ነው ትላለች። በዚህ እምነ ቷም ሰዎችን እንቆቅልሽ ውስጥ ትጥላቸዋለች። ኢየሱስ እንደተባለው በተሰ ቀሉ ጊዜ ሦስቱም አንድ ላይ ተሰቅለው ነበር ወይ? አባት ከልጁ ጋር ተሰቀለ ወይስ ልጁ ብቻውን ተሰቀለ? ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ ብቻቸውን ሞቱ ወይስ ሦስ ቱም አንድ ላይ ሞቱ? ማርያም ኢየሱስን ሲወልዱ እግዚአብሔር አባትም ከኢየሱስ ጋር ተዋሕዶ ነበር? ይህ ካልሆነ ግን አባት የራሱ የሆነ የተለየ ሕል ውና፣ ልጅም እንደዚሁ የራሱ የተለየ ሰብእና አለው ማለት ነው። የተለያዩ ከሆኑ ዘንዳ ደግሞ ለምን አንድ ይሆናሉ?

እስላም በዚህ ላይ በጣም ግልጽና ቀላል የሆነ እምነት አለው። እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆኑ ሰብዓዊ ፍጡር ናቸው።

ታድያ የትኛውን ነው የሚመርጡት? ሰውም እግዚአብሔርም የተባሉትን ኢየሱስ ወይስ ሰውና ነቢይ የሆኑትን ኢየሱስ?

## አብ ወይስ ወልድ?

ክርስትና፣ እግዚአብሔር ቁጥር 1 አባት ነው፤ እግዚአብሔር ቁጥር 2 ልጅ ወይም ወልድ ነው፤ እግዚአብሔር ቁጥር 3 ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው ይላል። አንድ ሰው የሚገምተው አባት በደረጃ ከፍ ብሎ ከልጅ በላይ መሆኑን ነው። ቤተክርስቲያን ግን ልጅን ከአባት በላይ ነው ያደረገችው። ክርስቲያኖች ምሕረትና ይቅርታ ሲለምኑ ልመናቸውን የሚያቀርቡት ወይም የሚያስተ ላልፉት ለኢየሱስ ?ዲ ለ?ባት አይደለም። በአጭሩ አባትን ጡረታ አስወጥ ተውታል። ቤተክርስቲያን በፍርዱ ቀን በሰዎች መካከል የመፍረዱን ሥራ ለወልድ ሰጥታለች። እናም አብ ወልድ ዓለምን እንዴት እንደሚመራ ቁጭ ብሎ ከመመልከት በስተቀር ሌላ ሥራ የለውም ማለት ነው፤ ክርስትና ለእግዚ

አብሔር ልጅ ፈጥሮ በመስጠት ቀስበቀስ ልጅን ጣዖት በማድረግ እግዚአብሔር ቁጥር 2 አድርጐ ማቅረቡ፣ ወልድን ከእግዚአብሔር ቁጥር 1 ከአብ የበላይና ይበልጥ ተፈላጊ ማድረጉ በጣም የሚገርም ነው።

እስላም ልንታዘዘውና ልንገዛው የሚገባን አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው በሚለው እውነታ ላይ አቋሙ በጣም ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን ነው የምና መልከው።የምንታዘዘውም እግዚአብሔርን ነው። የምንማጸነውም አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ነው። በመከከ ላችን የሚፈርደውም እግዚአብሔር ብቻ ነው። ብቸኛው እውነተኛ አምላክ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ምንድነው ምርጫዎ? ባለ ሦስት አምላኩ እምነት ወይስ ባለ አንድ ብቸኛ አምላኩ እምነት?

## ተለዋዋጭ አምላክ

ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር በማርያም ማሕጸን ውስጥ የሰው ልጅ ተፈ ጥሮ ተላበሰ ትላለች። ውጤቱም እግዚአብሔርም ሰብዓዊ ፍጡርም ነው የምት ለው ኢየሱስ ነው ብላ ትናገራለች። ይህም የእግዚአብሔር በኢየሱስ ውስጥ መስረጽ ወይም የኢየሱስ ሥጋ ለባሽ አምላክነት እምነት ነው። ኢየሱስ ሰው–አምላክ ወይም አምላክ–ሰው ቅልቅል ነው። እሱም ሁለት ባሕርያት ወይም ተፈጥሮዎች አሉት ማለት ነው።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጉዳይ የሚከተለው ነው:- እግዚአብሔር እንዴት ጽንስ ወይም ሽል ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር አምላክ እንደምን በማርያም ማሕጸን ውስጥ ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር ሊያድግና ቅርጽ ሊለዋውጥ እን ዴት ይችላል? እግዚአብሔር እንዴት ሊበላና ሊሸና ይችላል? እግዚአብሔር እንዴት ይተኛል? እግዚአብሔር ሊጸዳዳና ወደ መጸዳጃ ቦታ እንዴት ይሄዳል? እግዚአብሔር የማርያምን ጡት እንዴት ሊጠባ ይችላል? እንዲህ ዓይነቱ ምን ዓይነት አምላክ ነው?! የክርስቲያን አምላክ በእውነቱ ከአማልክት ሁሉ ልዩ ነው!!!

እስላም በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው አቋም በጣም ግልጽ ነው። እውነተኛውና አንድየው አምላክ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፍጡርና አገልጋዩ ናቸው። ማንም ቢሆን በአንድ ጊዜ አምላክም ሰውም ሊሆን አይችልም።

ታድያ የርስዎ ምርጫ የቱ ነው? በማርያም ማሕጸን ውስጥ የቆየው አምላክ ወይስ ሰብዓዊ ፍጡር የሆነው ኢየሱስ? ማመን የሚፈልጉትን እራስዎ ይምረጡ።

## አብ

እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድን ወልዷል ይላል ክርስትና። ይህ ከሆነ በመለኮታዊ ሥልጣን ወልድ የሆነው ኢየሱስ ከአብ ጋር እንዴት እኩል ሊሆን ይችላል? አብ ወልድን ፈጠረ ተብሏል። አንደኛው ፈጣሪ ሁለተኛው ፍጡር ከሆነ ዘንዳ ሁለቱ እንደምን በደረጃ እኩል ሊሆኑ ይችላሉ? አብ እግዚ አብሔር ከሆነ በርሱ የተፈጠረው ልጅ ወይም ወልድ እንዴት እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል? ኢየሱስ ለመፈጠር የግድ በ«ኔብ» ላይ ተመርኩዟል። ኢየሱስ ራሱን በራሱ የተብቃቃ አይደለም። ስለዚህ ራሱን በራሱ ያልፈጠረና ከምንም ያልተብቃቃ ፍጡር እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል? የኢየሱስ ሕልውና ከመሠረቱ በአባቱ ላይ የተመረከዘ ነውና።

እስላም የሚለው ኢየሱስ በተአምራዊ መንገድ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ሰብዓዊ ፍጡር ናቸው። ከዚህ የአስተናነጽ ሁኔታ በስተቀር ከሌላው የሰው ልጅ በምንም አይለዩም። ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። እሱም አንድ ነው። የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ አምላክ ነው። አልወለደም፣ አልተወለደምም።

ታድያ የርስዎ ምርጫ የትኛው ነው? የሦስትዮሽ–አምላክ ኮሚቴ ወይስ አንድ ብቸኛ አምላክ? ልጅ ያለው አምላክ ወይስ ልጅ የሌለው አንድ እግዚአብሔር?

# እንቆቅልሹ

ክርስትና እግዚአብሔር ሦስት አማልክት በአንድ አምላክ ነው ይላል። እነሱም እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ታድያ እግዚአብሔር አንድ ነው ወይስ ሦስት? ቤተክርስቲያን የምትለው እግዚአብሔር ሦስትም አንድም ነው፤ ወይም አንድ በሦስት ውስጥ ወይም ሦስት በአንድ ውስጥ ነው።

እስላም ግን እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው ይላል። ይህ የእስላም እምነት በጣም ቀላል፣በጣም ግልጽ፣ ሎጂካዊና ጤነኛ አእምሮ ያለው ማንም ሰው በቀላሉ የሚረዳው እምነት ነው።

ክርስትና አማልክት ሦስት ናቸው የሚለውን ብቻ ቢይዝ ኖሮ አንድም ሦስትም ነው ከሚለው ይልቅ የበለጠ ትርጉም ያለው ግንዛቤ ማስተላለፍ በቻለና ነገሮችን ቀላል ባደረገ ነበር። «ሦስትም አንድም» የሚለው እምነቱ የሰው ልጆችን አእምሮና ግንዛቤ በእጅጉ የሚፈታተን እውነተኛው እንቆቅልሽ ነው። ኢሎጂካዊ የሆነውን ይህን እምነት በምክንያታዊነት ላይ የተመረኮዘ አንድም ሰብዓዊ ሕሊና ፈጽሞ ሊገነዘብ አይችልም። ሦስቱ አማልክት የተነጣጠሉ ናቸው ወይስ የተዋሐዱ? የተዋሐዱ ከሆኑ አንድ ናቸው እንጂ ሦስት አይደሉም። የተነጣጠሉ ከሆኑ ግን ሦስት እንጂ አንድ አይደሉም። ወይ አንድ ነው ወይ ደግሞ ሦስት ነው። ከዚህ ውጪ ሁለቱም መሆን የማይታሰብና የማይሆን ነው።

ታድያ የትኛው ነው የርስዎ ምርጫ? አንድም ሦስትም የሆነው አምላክ ወይስ አንድ ብቸኛ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር? ወንድሜ ምርጫው የርስዎ ነው።

## የእግዚአብሔር አንድነት

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አንድ ነው። ክርስትና ግን እግዚአብሔር ሦስትም አንድም ነው የሚለውን እምነት ያራምዳል።

እስላም ግን የማይናወጽና ለግንዛቤ በጣም ቀላል የሆነ እምነት አለው። እግዚአብሔር አንድ ነው የሚል።

አምላክን በተመለከተ ወጥና የተጣጣመ አቋም የሚሹ ከሆኑ የትኛውን እምነት ነው የሚመርጡት? ከተጭበረበረ አምላክ–ብዙነቱና ጣዖታዊነቱ (ሽርኩ) ጋር ክርስትናን ወይስ ከማይናወጸው ግልጽና ጥርት ያለ አንድ አምላክ አምልኮ (ተውሒዱ) ጋር እስላምን?

## ሦስት ወይስ አንድ?

ክርስትና እግዚአብሔር ሦስት በአንድ ውስጥ ማለትም እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው ይላል። ሦስት አማልክት በአንድ አምላክ ውስጥ አሉ ይላል።

እስላም ግን እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው። ከርሱ የሚስተካከል ወይም ሥልጣኑን የሚጋራው ምንምና ማንም ተጋሪ የሌለው አንድ አምላክ ነው።

በርስዎ አመለካከት የትኛው እምነት ነው ይበልጥ ሎጂካዊና ለሰው ልጅ ግንዛቤ ይበልጥ ቀላል የሆነው? የክርስትና እሳቤ ወይስ የእስላም እሳቤ? ለግን ዛቤ ቀላልና ገሩ የትኛው ነው? መምረጥ ቢኖርብዎት የቱን ነው የሚመርጡት?

## ልጅ ያለው ወይስ የሌለው?

ክርስትና እግዚአብሔር ልጅ አለው፤ ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላል። እስላም ደግሞ እግዚአብሔር ምንም ወንድም ሆነ ሴት ልጅ የለውም። ሚስትም

ሆነች ወዳጅ የለችውም። እግዚአብሔር ልዩና ምንምና ማንም የማይመስለው፣ አቻና አምሳያ የሌለው አንድ አምላክ ነው።

ታድያ የትኛው አመለካከት ነው በጣም ቀላል ሎጂካዊ፣ ከሰው ልጅ አእምሮና ስለ አግዚአብሔር ካለው ግንዛቤው አኳያ ይበልጥ የሚጣጣም? የትኛውን አመለካከት ነው የሚመርጡት? እግዚአብሔር ልጅ አለው የሚለውን ወይስ እግዚአብሔር ልጅ የለውም የሚለውን?

## ብሉይ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን ስለ አንድ እግዚአብሔር ነው የሚናገረው። ኢየሱስ የሚባል የእግዚአብሔር ልጅ የሚባል ነገር የለበትም። ስለሁለቱ ካላነሳ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ይላል? አሁንም በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚባል ነገር የለም።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ለምን እግዚአብሔር አልተባለም? የሚለው ነው። ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ቁጥር 2 ኢየሱስን ከራሷ ፈጥራ መድባለች። እግዚአብሔር ቁጥር 3 መንፈስ ቅዱስንም እንደዚሁ ከራሷ ፈጥራለች። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን ነች ከራሷ ኪስ ሁለት ተጨማሪ አማልክት አክላ አንድ እግዚአብሔርን ሦስት ነው ያለችው።

እስላም ግን በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽና የማይለወጥ ጽኑ እምነት አለው። እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው የሚል።ተጋሪ አኩዮች ወይም ሸሪኮች የሉትም።

ታድያ የርስዎ ምርጫ ምን ይሆን? ባለ ሦስት–አምላክ ሃይማኖት ወይስ ባለ አንድ–አምላክ ሃይማኖት?

## ያህዌህ ወይስ ምን?

በቤተክርስቲያን እምነት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስትና የእግዚአብሔር ቃል ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል ማለትም ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ያህዌህ መሆኑን ይዘግባል። ይሁን እንጂ ይህ ስም በሐዲስ ኪዳን ፈጽሞ አልተጠቀሰም። እግዚአብሔር ስሙን ያልለወጠ እንደመሆኑ ለዚህ ሊሰጥ የሚችለው ብቸኛ ትንተና ወይ ያህዌህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ስም አይደለም፤ ቢሆን ኖሮ ሐዲስ ኪዳን ውስጥም በተጠቀሰ ነበር፤ አለበለዚያ ሐዲስ ኪዳን ያን እውነተኛ ስም ሆን ብሎ ተዘናግቶታል ማለት ነው የሚል ነው። በሁለቱም ሁኔታ ነገሩ መጽሐፍ ቅዱስ የጠራ የእግዚ አብሔር ቃል አለመሆኑን ያረጋግጣል።

በእስላም ዘንድ የእግዚአብሔር ስም **አላህ** ነው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በቁርአን ምዕራፎችና በነቢዩ ሙሐመድ ቃል ውስጥ የተነገረው የእግ ዚአብሔር ስም አላህ ነው። አላህ የአዳም፣ የአብርሃም፣ የሙሴ፣ የኢየሱስና የሙሐመድ የመላው ሰው ዘር ፈጣሪ አምላክ ነው። ይህ ስም ማለትም አላህ አዲስ ስም አይደለም። አላህ ብቸኛው እውነተኛ የእግዚአብሔር ስም ነው። ሌላው ቀርቶ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳ ብቸኛው እውነተኛ የእግዚአብሔር ስም ነው። ለዚህ መስረጃው «ሃሌ ሉያ» እና «አሌ ሉያ» ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመዝሙረ ዳዊት በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ነው። ፍቺው «ምሥጋና ለእግዚአብሔር ይሁን» ማለት ነው። ቃሉ በእስላምና በቁርአን የተመለከተውን የእግዚአብሔር ስም «አላህ»ን በግልጽ እውስጡ ይዟል።

እስላም፣በጣም ግልጽና ወጥ በሆነ ሁኔታ አጽንኦት በመስጠት ነው እግዚአብሔርን በተጸውኦ ስሙ ያላንዳች ማመንታት ወይም ትርጉም በቀጥታ የሚጠቀሰው።

«ሃሌሉያ» ማለት ምሥጋና ለእግዚአብሔር ይሁን ማለት ከሆነ አላህ ማለት እግዚአብሔር አምላክ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተመለከተው አላህ የእግዚአብሔር ስም ከሆነ ዘንዳ ይህ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም

በሐዲስ ኪዳን አገልግሎት ላይ ያልዋለው ለምንድነው? ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ አያስነሳምን?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን አምላክ፣ ያህዌህ ወይም ጌታ ብሎ ነው ሚጠራው። ቁርአን ግን እግዚአብሔርን የሚጠራው እርሱ ራሱ ራሱን በጠራበት ስም ማለት አላህ እያለ ነው። ለየትኛው ነው በትክክለኛነቱ የበለጠ አመኔታ የሚሰጡት? ለመጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ለቁርአን?

## ለምን ያህዌህ?

ብሉይ ኪደን ያህዌህ የሚለውን ስም በብዙ አጋጣሚዎች ላይ የእግዚ አብሔር የተጸውኦ ስም አድርጐ ይጠቅሳል።ሳይታሰብ ግን ይህ ስም ይሰወርና ሐዲስ ኪዳን ውስጥ ፈጽሞ አይጠቀስም። ከዚህ ቁልጭ ብሎ እንደሚታየው መጽሐፍ ቅዱስ ሌላው ቀርቶ በእግዚአብሔር ስም ላይ እንኳ ፈጽሞ ወጥነትና መጣጣም የሌለው መጽሐፍ ነው።

ክርስቲያን ምሑራን እንደሚሉት ያህዌህ የእግዚአብሔር ስም ሳይሆን፣ አይሁዶች እውነተኛው ስም ለመጥቀስ እጅግ ቅዱስ በመሆኑ የተነሳ በርሱ ምትክ እንዲለውጥ የተጠቀሙበት ቃል ነው።

እነኚህ ምሑራን እንደ ማብራሪያ ያቀረቡትን ሃሳብ በመቀበል የሚከተሉትን ሦስት ጥያቄዎች እናነሳለን:-

(1) ያህዌህ የሚለው የእግዚአብሔር እውነተኛ ስም ካልሆነ፣ አይሁድ ማለቱን እጅግ ቅዱስ ሆኖ ያገኙት ያ እውነተኛ ስም ምንድነው? ቤተክርስቲያን ይህን ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ምላሽ ለመስጠት ፈጽሞ ግድ ኖሯት አያውቅም!

(2) የእግዚአብሔር እውነተኛ ስም ለምን ይደበቃል? ይህን የማድረግ መብት የማነው? ስሙ መጠቀስ የሌለበት ከሆነ እግዚአብሔር ለራሱ ለምን መጠሪያ ስም ሰጠ?

(3) ያህዌህ የሚለው ለእውነተኛው የእግዚአብሔር ስም ተለዋጭ ስም ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ለለውጥ የተጋለጡ መሆናቸውን ያረጋግጣል። በዚህ የመለዋወጥና የመቀያየር ሂደት ነው በእውነተኛው የእግዚአብሔር ስም ፈንታ «ያህዌህ» የሚለውን ያስቀመጡት ማለት ነው።

እስላም ለነኚህ ጥያቄዎ የሚሰጠው ምላሽ ግን ምንጊዜም ዝግጁና ቀላል ነበሩ፤ ናቸውም:-

(1) እውነተኛ የእግዚአብሔር ስም አላህ ነው። ይህም ዘላለማዊው የእግዚ አብሔር መጠሪያ ስም ነው። ይህ ስም በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ሃሌሉያ» ወይም «አሌሉያ» በሚል አገላለጽ በተደጋጋሚ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ ተመልክቷል። እውነተኛው የእግዚአብሔር ስም ለብዙ ሺ ጊዜያት ቁርአን ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል።

(2) የእግዚአብሔርን እውነተኛ ስም በሌላ የመተካት ወይም የመሰወር መብት ማንም ፍጡር የለውም። እግዚአብሔር ለራሱ የመጠሪያ ስም ከሰጠ በኋላ ማንም ቢሆን ስሙን መደበቅ ወይም በሌላ መተካት የለበትም። የማንንም ተራ ፍጡር ስም መደበቅ ወይም መተካት የማንም መብት እስካልሆነ ድረስ፣ የእግዚአብሔርን ስም በሌላ የመተካት ወይም የመደበቅ መብት አንድ ሰው ምን ብሎ ለራሱ ይሰጣል?

(3) መጽሐፍ ቅዱስ መጠነ ሰፊ ለሆነ የማበላሸት፣ የማዛባት፣ የማብራራት፣ የመደለዝና የመቀያየር ሂደቶች ተጋልጧል። የማበላሸቱ ተግባር እጅግ የገዘፈ ከመሆኑ የተነሳ ጠቅላላ ይዘቱና ሕልውናው የተጋና የተበጠበጠ ሆኗል።

ታዲያ ይበልጥ መለኮታዊና ይበልጥ ተአማኒ አድርገው የሚመርጡት የትኛውን መጽሐፍ ነው? የእግዚአብሔርን ስም የሚደብቀውንና በሌላ የሚተካ ውን መጽሐፍ ወይስ ስሙን እንዳለ ወጥና ቋሚ በሆነ ሁኔታ የሚጠቀመውን መጽሐፍ?

# ይደክማል ወይስ አይደክምም?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረና ደክሞት በሰባተኛው ቀን ላይ አረፈ ይላል (ዘፍ 2፥2)።

ቁርአን ግን እግዚአብሔር ዓለምን ወይም ፍጠረተ ዓለምን (ዩኒቨርስን) በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረ ግን አልደከመውም ነበር ይላል።

ታድያ የእግዚአብሔር ቃል አድርገው የትኛውን ይቀበላሉ? እግዚአ ብሔር ደክሞት ዕረፍት አስፈለገው የሚለውን ወይስ አልደከመውም የሚለ ውን? ከተገቢው የእግዚአብሔር ባህሪያት ጋር የሚጣጣመውስ የትኛው ነው? የሚደከመው መሆኑ ወይስ ፈጽሞ የማይደከመው መሆኑ? እግዚአብሔር ሊደ ክም ይችላል? ይህ ከሆነ ሊደከመውና ዕረፍት ሊያስፈልገው በሚችል ሰብዓዊ ፍጡርና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

# ምዕራፍ 3

# ኢየሱስ

# በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

## ለመሆኑ እሱ ማነው?

በኢየሱስ ማንነት ላይ ሐዲስ ኪዳን ግልጽ የሆነ የጠራ አቋም የለውም። አራቱ ወንጌሎች ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የማርያም ልጅና የዮሴፍ ልጅ ብለው ይጠቅሳሉ።

የእስላም ቁርአን ግን ወጥነት ባለውና በማይናወጽ አቋም «ኢየሱስ (ዒሳ) የማርያም ልጅ» ብሎ ነው የሚጠቅሰው።

አንድን ግለሰብ ከተለያዩ አባቶች ጋር ማያያዝ ስሜት ይሰጣል? ታድያ በየትኛው ነው ከወጥነቱና ከጽናቱ አኳያ ይበልጥ የሚተማመኑበት? ለኢየሱስ የተለያዩ አባቶችን በሚሰጠው ሐዲስ ኪዳን ወይስ ኢየሱስን ሁልጊዜ የማርያም ልጅ ብሎ በሚጠራቸው ቅዱስ ቁርአን? በዚህ ነጥብ ላይ የርስዎን ታማኝነት እቀበላለሁ።

## አባቱ ማነው?

ክርስትና ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድ ብቸኛ ልጅ ነው ይላል።

እስላም ደግሞ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ናቸው፤ የተወለዱትም ያለ አባት ተአምራዊ በሆነ መንገድ ነው ይላል። እግዚአብሔር ያሻውን ሰውና ፍጥረት ባስፈለገው መንገድ ለመፍጠር ቻይ አምላክ ነው። አዳምን ከምንም ያለ አባትና

ያለ እናት ለመፍጠር የቻለው አምላክ ኢየሱስን ያለ አባት ለመፍጠር ቻይ መሆኑ አንዳች ጥርጣሬ የለውም። ሔዋንን ያለ እናት ከአዳም ጉድን ፈጥሯል። ስለዚህም የአዳም አፈጣጠር ከኢየሱስ አፈጣጠር ይበልጥ ተአምራዊ ነው።

ታዲያ የትኛው ነው ይበልጥ ሎጂካዊ ወይም ምክንያታዊው? እግዚ አብሔር ልጅ አለው የሚለው ወይስ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ናቸው፣ እግዚ አብ ሔር ልጅ ወይም ልጆች የሉትም የሚለው? የአምላክን ጽንሰ ሐሳብ ለመግ ለጽ ይበልጥ ተስማሚው የትኛው ነው? አስተውለው ይወስኑ።

## ልጁ ማነው?

ክርስትና እና ቤተክርስቲያን ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድ ብቸኛ ልጅ መሆኑንና እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሰው ልጆች መድህን ብሎ የሰዋ መሆኑን በአጽንኦት ይናገራሉ። ለመሆኑ ኢየሱስ እውነት የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ ናቸው?

ሉቃስ በወንጌሉ ውስጥ ለእግዚአብሔር ሌላ ተጨማሪ ልጅ ይሰጣል። እው ነቱን ለመናገር በሉቃስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ አይደለም። በሉቃስ ዘንድ ኢየሱስ የአናጺው የዮሴፍ ልጅ ነው። ሉቃስ በሚለው መሠረት እውነ ተኛው የእግዚአብሔር ልጅ አዳም ነው (ሉቃስ 3፥7)። ስለዚህም በወንጌሉቹ መሠረት እግዚአብሔር አንድ ብቸኛ ልጅ ሳይሆን ሁለት ልጆች–አዳምና ኢየሱስ–አሉት።

ማንኛቸውን እንመን? ኢየሱስ አንድ ብቸኛ የእግዚአብሔር ልጅ የም ትለውን ቤተክርስቲያን ወይስ አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ሉቃስን?

በእስላም ዘንድ እንደተለመደው ጉዳዩ ምንጊዜም ቢሆን በጣም ግልጽና የማያሻማ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አይደሉም። አዳምም። እግዚ አብሔር ፈጽሞ ልጆች የሉትም።

ኢየሱስንና እግዚአብሔርን በተመለከተ ይበልጥ ወጥነት ያለው ሆኖ የሚያገኙት የትኛውን ነው? ክርስትናን ወይስ እስላምን? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቅዱስ ቁርአንን?

## ፀሎት

ኢየሱስ በፊቱ ወድቆ የጸለየ ወይም የሰገደ መሆኑ ተገልጿል (ማቴ.26፥39)። ይህም ማለት ኢየሱስ በግንባራቸው ተደፍተው መስገዳ ቸውን ያሳያል። ለማነው ተደፍተው የሰገዱት? በዚህ ሁኔታ መስገዳቸው ራሱ ለእግዚአብሔር ራሱን ዝቅ አድርጐና አዋርዶ የሚያስገዛ ሰው መሆናቸውን ያረጋግጣል። ለእግዚአብሔር የሚጸልይና በፊቱ ተደፍቶ እግዚአብሔርን የሚ ያገለግል ሰብዓዊ ፍጡር ተመልሶ በራሱ እግዚአብሔር ሊሆን ፈጽሞ አይች ልም። ቤተክርስቲያን ግን ኢየሱስ ከቶውንም ብለው ወይም ፈልጐት የማያውቁ ቢሆንም ቅሉ ነቢዩን አምላክ የማድረግ ግፊቷን ቀጥላበታለች። በዚህም ቤተክ ርስቲያን ከእውነተኛው የኢየሱስ ትምህርት ጋር ግንኙነት የሌለው አዲስ ሃይ ማኖት ከራሷ ፈጥራ አስገኝታለች። ከዚህ የተነሳም ክርስትና የኢየሱስ ትምሕ ርቶች ተጻራሪ ሃይማኖት ነው።

እስላም ግን ምንጊዜም ቢሆን ነቢዩ ሙሐመድ ያሉት ያደረጉትና ከእግ ዚአብሔር የተላለፈላቸው ትምሕርት ብቻ ነው። በሌላ አገላለጽ እስላም እግዚ አብሔር ለነቢዩ ሙሐመድ በመለኮታዊ ራእይ ያስተላለፈላቸው፣ ሙሐመድ የተናገሩትና የተገበሩት ነባሩ ሃይማኖት ነው።

ይህን ግንዛቤ በመውሰድ የትኛውን ነው የሚመርጡት? የሃይማኖቱ መሥ ራች ነቢይ ያስተማረውንና የተናገረውን የሚጻረር ሃይማኖት? ወይስ ነቢዩ የተናገ ረውንና ያስተማረውን ብቻ የሚከተል ሃይማኖት? ይበልጥ ወጥነት ያለውና ራሱን በራሱ የማይቃረን የትኛው ሃይማኖት ነው? ይበልጥ ቅን ተገዥነትና ይበልጥ መለኮታዊ ተገዥነትን የተላበሰው የትኛው ነው? ከራስ ፈጠራ አዲስ ሃይማኖት መፍጠር ወይስ መስራቹ ነቢይ ባስተላለፉት መሠረት ለእግዚአብሔር ቃል ተገዥ መሆን?

## ቅድመ አያቶቻቸው

ማቴዎስ የኢየሱስን የዘር ሐረግ በአናጺው ዮሴፍና በዳዊት በኩል ከአብርሃም ጋር ያገናኛል። ሉቃስ ደግሞ በወንጌሉ ውስጥ የኢየሱስን የዘር ሐረግ በአናጺው ዮሴፍ፣ በዳዊትና በአዳም በኩል በማሳለፍ ከእግዚአብሔር ጋር ያያይዛል።

ታዲያ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በምትናገረው መሠረት የእግዚአብሔር ልጅ፣ ወንጌሎች በሚናገሩት መሠረት ደግሞ የዮሴፍ ልጅ እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? ቤተክርስቲያን ነች ወንጌልን የምትከተለው? ወይስ ወንጌሉ ነው ቤተክርስቲያኗ የሚከተለው? ማቴዎስና ሉቃስ የሰው ልጅ የዘር ሐረግ ከሰጧቸው ዘንዳ ኢየሱስ እንዴት የእግዜአብሔር ልጅ ይሆናሉ?

እስላም ግን በኢየሱስና በሙሐመድ የዘር ሐረግ ላይ በጣም ግልጽና ቁልጭ ያለ አቋም አለው። ኢየሱስ የማርያም ልጅ ናቸው። በቃ። ሙሐመድ ደግሞ ዐብዱልላህ የሚባል ሰው ልጅ ናቸው። እስላም ለያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ነጠላ ምላሽ ነው የሚሰጠው። ክርስትና እና መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለአንድ ዓይነት ጥያቄ ብዙ ተጻራሪ የሆኑ መልሶች ይሰጣሉ። ወንጌሎች ኢየሱስን የእግዜ አብሔር ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣ የሰው ልጅ እና የማርያም ልጅ በማለት የተለያዩ አባቶች ይሰጣሉ።

የትኛውን ነው የሚመርጡት? ለአንድ ጥያቄ የተለያዩ ተጻራሪ የሆኑ መልሶች የሚሰጠውን ሃይማኖት? ወይስ ለአንድ ጥያቄ አንድ ቋሚ የሆነ መልስ ብቻ የሚሰጠውን ሃይማኖት?

## ኢየሱስና አዳም

ክርስትና አዳም የተከለከለውን ዛፍ በመብላተ ኃጢአት ፈጽሟል፣ ስለዚህም አዳም እስከ አጥንቶቹ መቅኒ ድረስ ኃጢአተኛ ነው፤ የሰው ልጆች

በመላም ከአባታቸው ከአዳም በውርስ በተላለፈባቸው ኃጢአት ምክንያት ኃጢአተኞች ናቸው ይላል። በክርስትና ትምሕርት መሠረት እግዚአብሔር አንድያ ልጁ ኢየሱስን ወደ መስቀያው የላከው የሰውን ልጅ ከዚሀ በውርስ ከተቀበለው ኃጢአት ለማዳን ነው።

በሌላ አገላለጽ አዳም እገዳውን ጥሰው ከዛፉ በሉና ኢየሱስ ከብዙ ሺ ዓመታት በኋላ በአዳም ኃጢአት ተሰቀሉ። አዳም ኃጢአት ፈጸሙ ፤ ኢየሱስ አዳም በፈጸሙት ወንጀል ተቀጡ። ይህ ነው እንግዲህ ክርስቲያናዊ ትረካ።

እስላም የሚለው ደግሞ አዳም ኃጢአት ፈጽሟል ግን በኃጢአቱ ተጸጽቶ እግዚአብሔርን ምሕረት ስለ ለመነ እግዚአብሔር ይቅር ብሎታል ነው። ስለዚህም አዳም ከሠራው ኃጢአት ጋር ኢየሱስን የሚያገናኝ አንዳች ምክንያት የለም። ለዚህ ብለውም አልተሰቀሉም፣ ሊሰቀሉም አይገባም። እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ራሱ ወንጀልና ኃጢአት ራሱ ተጠያቂ ነውና።

የትኛው ትረካ ነው ገርና ቀላል መስሎ የሚታይዎት? ኢየሱስን ለአዳም ኃጢአት ተጠያቂ የሚያደርገው የክርስትና ትረካ? ወይስ እያንዳንዱን ሰው ለሥራው ተጠያቂ የሚያደርገው እስላማዊ ትረካ? ፍርዱን እራስዎ ይስጡ ግን ሐቀኛ ይሁኑ።

## ነቢይ ወይስ አምላክ?

ወንጌሎች ብዙ ቦታ ላይ ኢየሱስን እንደ ነቢይ ያቀርባሉ። ለምሳሌ ያህል (ሉቃ. 7፥16)። የናዝሬቱ ነቢይ (ማቴ.21፥11)። ቤተክርስቲያን ግን ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንንም እንዲሁ በመጻረር በምታራምደው በአንድ አምላክ ያለማመንና በሦስትዮሽ አማልክት ማመንን የመምረጥ ድርጊቷ ኢየሱስን አምላክ አድርጋለች። ስለዚህም ክርስትና መለኮታዊ ሳይሆን ሰው ሠራሽ ሃይማኖት ነው። ኢየሱስ ራሳቸውን አምላክ ነኝ ወይም የአምላክ ልጅ ነኝ ብለው ጠርተው ጭራሽ አያውቁም። ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን የሰው ልጅ እያሉ ይጠቅሱ ነበር (ማቴ.17፥22፤ ማቴ.18፥11) ።

እስላም ግን ሙሉ በሙሉ ከቁርአንና ከነቢዩ ሙሐመድ ቃል ጋር የተጣጣመና የተዋሐደ ነው። ስለዚህም እስላም እግዚአብሔር–ሠራሽ እንጂ ሰው–ሠራሽ ሃይማኖት አይደለም።

ታዲያ የትኛውን ነው የሚመርጡት? በሰዎች የተሠራውን ወይስ ሁሉን በፈጠረው እግዚአብሔር የተፈጠረውን ሃይማኖት? የሚፈልጉትንና ነፍስዎ የምትናፍቀውን ለይተው ይምረጡ።

## አምላክ በሹመት ዕድገት

ወንጌሎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ራሳቸውን የሰው ልጅ ብለው የገለጹ ቢሆንም ክርስትና ግን ኢየሱስን አምላክ ቁጥር 2 ያደርጋቸዋል። የፈጸሟቸው ተአምሮችም በገዛ ራሳቸው ኃይልና ችሎታ ያልተፈጸሙ መሆናቸውንም ኢየሱስ አበክረው ተናግረዋል። በገዛ ራሳቸው ምንም መሥራት የማይችሉ መሆናቸውንም ገልጸዋል (ዮሐ. 5፥30)። ቤተክርስቲያን ግን የኢየሱስን ፍላጐት በመጻረር የገዛ ራሳቸውን ትምሕርቶችም በመቃረንና ከዕውቀታቸው ውጭ ኢየሱስን ከሰው ልጅነት ወደ አምላክነት በማሸጋገር ሾማለች።

እስላም ግን በሁለቱም ማለትም በኢየሱስና በሙሐመድ ላይ ያለው አቋም በጣም ግልጽ ነው። ሁለቱም የእግዚአብሔር ነቢዮች ለመሆን የተመረጡ ሰዎች ናቸው።

የእምነት ብሩህነት የሚሹ ከሆኑ ምርጫዎ ምንድነው? ሰውን አምላክ የሚያደርገውን ክርስትና ወይስ ሰውን ሰው ብቻ በማድረግ ከአንድ ፈጣሪ አምላክ ጋር ባዕድ አማልክት የማያጋራውን እስላም?

## አናጺ ወይስ አምላክ?

ኢየሱስ የአናጺነትን ሙያ ከአናጺው ዮሴፍ ተምረዋል። ከአሥራ ሁለት እስከ አሥራ ስምንት መካከል ባሉት የዕድሜ ዘመናቸው የዮሴፍ ሠልጣኝ ሠራተኛ ነበሩ። አሥራ ስምንት ዓመት ሲሞላቸው ዮሴፍ ሞተና አናጺነትን

ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው የገቢ ማስገኛ መደበኛ ሞያ አድርገው ተያያዙ። ይህን ሥራ መደበኛ የገቢ ማስገኛቸው በማድረግ እስከ ሰላሳ ዓመታቸው ድረስ ቀጠሉበት። ሰላሳ ዓመት ሲሞላቸው ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) ተላለፈላቸውና ለሦስት ዓመታት ያህል የዘለቀውን የእግዚአብሔርን መልዕክት ለቤተ እስራኤል የማድረስ ተልዕኳቸውን ጀመሩ።

ስለዚህም ከአሥራ ሁለት ዓመታቸው ጀምሮ እስከ ሰላሳኛው ዓመታቸው ድረስ ለአሥራ ስምንት ዓመታት አናጺ ነበሩ።

ወንጌሎች ግን ኢየሱስ በዚህ ዘመን (በአሥራ ስምንቱ ዓመት) ስላሳለፉት ሕይወት ምንም ነገር አይተነፍሱም። ስለ ሕይወታቸውና ስለ ልደታቸው ማውራት የሚጀምሩት እስከ አሥራ ሁለተኛ ዓመታቸው ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ ሳይታሰብ በቀጥታ በሰላሳኛው ዓመታቸው ወደ ተጀመረው ተልዕኳቸው ይዘላሉ። ከዕድሜያቸው 12–30 ያሉት ዓመታት በሐዲስ ኪዳን አራቱም ወንጌሎች ሙሉ በሙሉ የተዘናጉ ዓመታት ናቸው። ለምን? ኢቫንጀሊስቶች የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ እየጻፉ ከሆኑ ከሠላሳ ሦስቱ የዕድሜ ዘመናቸው ውስጥ አሥራ ስምንቱን ዓመት ለምን ይዘላሉ? ይህ ራሱ ዋጋ ያለው ጥያቄ አይደለምን? ምናልባት ኢቨንጀሊስቶቹ እነኛን የኢየሱስ የሕይወት ዓመታት አልዘለሉ ይሆናል፤ የጻፉት ነገር ተፈላጊ ያልሆኑ የጽሑፉን ክፍሎች ሆን ብሎ ለመሰረዝና ለማስወጣት ለተካሄደው የማጣመም የማዛባትና የመበረዝ አደጋ ተጋልጦም ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የወንጌል ኦሪጂናል ቅጂዎች ያን ዘመን ከመጀመሪያውም ያላቀፉ ሊሆንም ይችላል።

ለማንኛውም ግን ያ ዘመን፣ አምላካችን ወይም የእግዚአብሔር ልጅ የሚሏቸውን ኢየሱስን አናጺ አድርገው እንዳያሳዩ ስላልፈለጉ ወይ ተዘሏል፤ አለበለዚያም ተሰርዟል። ከኢየሱስ የሕይወት ዘመን ውስጥ እኒያ ዓመታት ተስማሚ ሆነው አልተገኙም ማለት ነው። አናጺው ኢየሱስ ከእግዚአብሔሩ ወይም ከእግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ጋር በጥሩ ሁኔታ አይጣጣምም። ስለዚህም ቤተክርስቲያን አናጺውን ኢየሱስና አሥራ ስምንቱን የአናጺነት ዓመቶቻቸውን አውጥታ ጥላለች። ዳሩ ግና በመታደልም ይሁን አይሁን እውነቶቹን መሰረዝና ማስወጣት አያስወግዳቸውም።

በተቃራኒው ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ በአሥራዎቹና በሃያዎቹ መጀመሪያ የወጣትነት ዘመናቸው እረኛ የነበሩ ሲሆን በኋላ ደግሞ በአርባኛው ዓመታቸው መለኮታዊውን ተልዕኳቸውን ከመጀመራቸው ቀደም ብሎ ነጋዴ ነበሩ። የሙሐመድ የእረኝነትና የነጋዴነት የሕይወት ዘመን በእስላምና በሙስሊሞች ዘንድ የተደበቀ አይደለም። በተጻራሪው ሙስሊሞች በዚህ ኩራትና ክብር ይሰማቸዋል። ነቢያቸው የሥራን ክቡርነት የሚያውቁና ሥራን የሚያከብሩ ጠንካራ ሠራተኛ በመሆናቸው በእጅጉ ይደሰታሉ።

ቀላልና የማያስቸግር ሆኖ የሚታይዎት የትኛው ነው? የነቢዩን ሞያ መደበቅ የሚሞክረው ሃይማኖት? ወይስ አንዳች የሚደብቅ ነገር የሌለው ሃይማኖት?

## ተፈጥሮአቸው

ክርስትና መሥራቹን ማለትም ኢየሱስን አስመልክቶ የተለያዩና ውስብስብ የሆኑ ዘገባዎች ይሰጣል። ሰው ናቸው፣ አምላክ ናቸው፣ ሁለቱም ናቸው ይላል። ሁለት ዓይነት ተፈጥሮ (Nature) ማለትም የሰብዓዊነት ወይም የመለኮታዊነት ባህሪይ አላቸው ይላል። አንድ ፈቃድ ወይም ሁለት ማለትም የሰው ልጅ ፈቃድ ወይም የመለኮታዊነት ፈቃድ አላቸው ይላል።

እስላም ግን ስለራሱ ነቢይ ስለ ሙሐመድ አንድ ግልጽና ወጥ የሆነ ዘገባ ይሰጣል። የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቦች ለማድረስ ነቢይና መልዕክተኛው ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጡ የሰው ልጅ ናቸው። ኢየሱስም እንዲሁ ናቸው ይላል።

ታድያ የማገኛቸው ዘገባ ነው ይበልጥ ሎጂካዊና ይበልጥ ሚዛናዊው? ክርስትና ስለየሱስ የሚሰጠው ዘገባ? ወይስ እስላም ሰለሁለቱም ማለትም ስለ ሙሐመድና ስለኢየሱስ የሚያቀርበው ዘገባ?

## እንቆቅልሽ ወይስ ግልጽ

ክርስትና ኢየሱስ ሥጋ ለብሰው በሰው መልክ የተገለጹ እግዚአብሔር ናቸው ይላቸዋል። በአንድ ጊዜ ሰውም አምላክም ናቸው ይላል።

እስላም ግን ኢየሱስ ሰው እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም። አንድ ሰው ሰውም እግዚአብሔርም መሆን ፈጽሞ አይችልምና። ስለዚህም ኢየሱስ እንደ አብርሃምና እንደ ሙሴ ሁሉ ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ ናቸው።

ይበልጥ ቀላል ይበልጥ ምክንያታዊና ሚዛናዊ አድርገው የሚቀበሉት የትኛውን ነው? ኢየሱስ ሰውም አምላክም ናቸው የሚለውን? ወይስ ኢየሱስ ሰውና የእግዚአብሔር ነቢይ ናቸው የሚለውን? በታማኝነትዎና በሚዛናዊነትዎ እተማመናለሁ።

## ምክንያታዊው ምርጫ

ኢየሱስ አምላክ ነው እንደዚሁም በተመሳሳይ ጊዜ የአምላክ ልጅም ነው ይላል–ክርስትና።

እስላም ግን ኢየሱስ የሰው ልጅና የእግዚአብሔር ነቢይ ናቸው ይላል።

ታዲያ የትኛው አመለካከት ነው የበለጠ ምክንያታዊና ተአማኒ መስሎ የሚታየው? ከውስጣዊ ቅራኔ ነጻ የሆነውስ የትኛው ነው? ኢየሱስ በተመሳሳይ ወቅት አምላክም የአምላክ ልጅም እንዴት ተደርገው ሊሆኑ ይችላሉ? በአንድ ጊዜ አቶ ‹ሀ› እና አቶ ‹ለ› ሊሆኑ እንዴት ይችላሉ? ሎጂካዊና ወጥ ለሆነ አመለካከት የቱን ይመርጣሉ? የክርስትናውን ወይስ የእስላሙን አመለካከት?

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

በ325 ዓመተ ክርስትና ኢየሱስ ሰውና ነቢይ ነው ወይስ ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔር ነው? የሚለውን በድምጽ ብልጫ ለመወሰን የቤተክርስቲያን መሪዎች ስብሰባ አካሂደዋል። በዚህ ስብሰባ ላይም የኢየሱስን ባህሪይ አስመ ልክቶ ክርክርና የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ተከናውኗል። የአብላጫው ድምጽ የኢየሱስን መለኮታዊ ባህሪ አፀደቀና ኢየሱስም በውሳኔው መሠረት በአብላጫ ድምጽ እግዚአብሔር ሆኑ!

እስላም የሚለው ግን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው። ማንም ፍጡር እግዚአብሔር ሊሆን ፈጽሞ አይችልም ነው። የነቢዩ ሙሐመድ ተፈጥሮና ባህሪ ያቸው ለውሳኔ ድምጽ አልቀረበም። በተከታዮቻቸው እምነት ምንጊዜም ቢሆን ሰውና የአላህ ነቢይ ናቸው።

ታድያ የትኛው ነው ከእምነት መሠረቶቹ አኳያ ይበልጥ ግልጽና ብሩሕ? የኢየሱስን ባህሪ ለማስወሰን ለድምጽ የሚያቀርባቸው ክርስትና? ወይስ ምን ጊዜም ቢሆን ሙሐመድን ሰውና የአላህ ነቢይ ብቻ አድርጎ የሚያቀርባቸው እስላም? ለመሆኑ በመለኮታዊ ራእይ ለተላለፈ ሃይማኖት መሠረታዊ የእምነት አስኳል የሆነ ጉዳይ በሰዎች ውሳኔ ድምጽ የሚገዛና የሚወሰን ነውን? የመለ ኮታዊ ሃይማኖት መሠረታዊ የእምነት መርሆዎች፣ ሃይማኖቱ እውነት በመለ ኮታዊ ራእይ የተላለፈ ከሆነ መተላለፍ ያለባቸው በራሱ በእግዚአብሔር ብቻ ነው። እንዲህ ያሉ መሠረታዊ ጉዳዮችን እግዚአብሔር ችላ ብሏቸው ለሰዎች ውሳኔ ድምጽ እንዲተው ሊደረጉ አይችሉም። የሃይማኖቱ መሠረታዊ የእምነት አስኳሎች ከእግዚአብሔር ካልተላለፉ ሌላ ምን ሊተላለፍ ይችላል?! የኢየሱስን ባህሪ ለውሳኔ ድምጽ ማቅረብ የድምጽ አሰጣጡ ውጤት ከመለኮታዊ ራእይ ውጭ መሆኑን ያረጋግጣል።

# አስገራሚ የሹመት ዕድገቶች

ኢየሱስ ፈጽሞ ያልጠበቋቸው ወይም ያልጠየቋቸውንና በጭራሽም የማያውቋቸውን አስገራሚ የሹመት ዝርዝሮች ቤተክርስቲያን ለነቢዩ ሰጥታቸ ዋለች። መጀመሪያ ላይ ራሳቸውም እንደ ተናገሩት የሰው ልጅ ነበሩ። ኋላ ላይ ግን ቤተክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ልጅነት የሹመት ደረጃ አሸጋገራቸው። ትንሽ ቆይታ በማከታተልም እግዚአብሔር ወልድ ወደሚባል የላቀ ሹመት አሸጋገረቻቸው። ቀጥሎም ሦስተኛውን የዕድገት እርከን በመስጠት ጠቅላይ–እግዚአብሔር (Supreme-God) አደረገቻቸው። ይህም በፍርዱ ቀን በሰዎች መካከል የሚፈርድ እሱ ነው በማለት ነው። ኢየሱስ ያገኙትን እንዲህ ያለ ፈጣን የሹመት ዕድገት ማንም አግኝቶ አያውቅም። ከሰው ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት፣ ከዚያም ወደ እግዚአብሔርነት፣ በመጨረሻም ወደ ጠቅላይ እግዚአ ብሔርነት!

ኢየሱስ የሰው ልጅ መሆናቸውን ተናግረዋል። ወንጌሎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ደጋግመው ይህንኑ ተናግረዋል። ፈጽሞ ራሳቸውን እንደ እግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔር ወልድ አቅርበው አያውቁም። ቤተክርስቲያን ግን ከፍላጐታቸው ውጭና ከዕውቀታቸው ውጭ ትምሕርቶቻቸውንም በመጻረር ሾማቸዋለች።

ቤተክርስቲያን ፈጥራ የሠራችው ክርስትናን ብቻ ሳይሆን የራሷን ኢየሱስም ከራሷ ፈጥራለች። የቤተክርስቲያኑ ኢየሱስ ሰው–ነቢይ ከሆነው ከእውነተኛው ኢየሱስ የተለየ ነው። ቤተክርስቲያን የፈጠረችው ኢየሱስ ከእውነተኛው ነባራዊ ኢየሱስ በውል የሚለይ በሃሳብ የተፈጠረ ምናባዊ የፈጠራ ገጸ–ባህሪይ ነው።

በተቃራኒው እስላም ግን ለኢየሱስ የሰው ልጅ የሆኑ የአላህ ነቢይ ናቸው የሚል አንድ ወጥ የሆነ ገጸ–ባሕሪይ ይሰጣል። እስላም የቤተክርስቲያኑን የፈ ጠራ ኢየሱስ ምክንያታዊና ሎጂካዊ በሆነ መሠረት ላይ በመመርኮዝ ውድቅ እያደረገ ስለ እውነተኛው ኢየሱስ እጅግ ከተጋነኑ የሹመት ደረጃዎች በራቀ መልኩ አዘውትሮ ይናገራል።

የትኛውን ነው ይበልጥ እውነታን የተላበሰው አመለካከት አድርገው የሚያስቡት? የክርስትናውን ምናባዊ ኢየሱ ስ? ወይስ እውነተኛውን የእስላም ኢየሱስ?

## ተሰቅለዋል አልተሰቀሉም?

ቤተክርስቲያን ለኢየሱስ ስቅላት አጽንኦት ሰጥታ የሰው ልጆች ዕድል የሚወሰንበትና ጀነት የመግባት ዋስትናቸው የሚመሠረትበት አቢይ የእምነት መርሕ ታደርጋለች።

በዚህ ትረካ ላይ የምሰጠው ምላሽ ቁርአን በጉዳዩ ላይ ከሰጠው ምላሽ ጋር አንድና ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስ አልተሰቀሉም የሚል። ለክርክር ያመች ዘንድ ለመናገር ያህል ግን በመርሕ ደረጃ የስቅላት አስፈላጊነትና ጥቅሙ ጭራሽ አይታየኝም። የኢየሱስ መሰቀል ወይም አለመሰቀል በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ምንም ዓይነት ተጽእና የለውም።ሊኖረውም አይገባም። በታሪክ ውስጥ ብዙ ሰዎች ተሰቅለዋል፣ ታንቀዋል፣ከነሕይወታቸው ወይም ከሞቱ በኋላ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በጥይት ተደብድበው ሞተዋል፣ ተጨፍጭፈዋል። ታድያ ያንድ ሰው በመስቀያ ላይ ተሰቅሎ መሞት ሚቹ የፈለገ ሰውም ቢሆን መሰቀሉ መላውን የሰው ልጅ እንዴት ማዳን ይችላል?

አንድን ሰው የሚያድነው እምነቱና ተግባሩ መሆኑ ግልጽ ነው። ኢየሱስ ራሳቸው ይህንኑ ነው ሚያረጋግጡት። ሐዲስ ኪዳን ያለ ትሩፋት ሥራ እምነት ሞት መሆኑን ያረጋግጣል። የእግዚአብሔር የሽልማትና የቅጣት መርሕ እያንዳንዱ ግለሰብ ለሥራዎቹ ውጤት ተጠያቂነት አለበት በሚለው ላይ የታነጸ ነው። የትኛዋም ነፍስ የሌላዋን ነፍስ ኃጢአት አትሸከምም። የሚሰቀለው የፈለገ ሰው ቢሆን በስቅላትና በመድህን መካከል ምንም ግንኙነት የለም። ይህ ሎጂካዊውና እስላማዊው አመለካከት ነው።

የትኛውን ነው የሚመርጡት? ኢየሱስን መስቀያ ላይ አድርገው በመግደል መድህን ማግኘትዎን ወይስ በገዛ ራስዎ እምነትና በበጐ ተግባርዎ መድህን ማግኘትዎን?

# በፈቃዳቸው ወይስ ከፈቃዳቸው ውጭ?

ክርስትና ኢየሱስ እኛን ለማዳን ሲል ራሱን ለመስቀያ የዳረገው ፈልጕና ሆን ብሎ በገዛ ፈቃዱ ነው ይላል። ወንጌሎቹ ግን ኢየሱስ እንዲሰቅሏቸው ጭራሽ አለመፈለጋቸውን፣ በገዛ ፈቃዳቸው ራሳቸውን ለጠላቶቻቸው አሳል ፈው አለመስጠታቸውን፣ ይልቅም ከፈቃዳቸውና ከፍላጐታቸው ውጭ በግድ ተይዘው መሰቀላቸውን ነው የሚያሳዩት።

ኢየሱስ የሞት ጽዋው ከሳቸው ያልፍ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልየዋል (ማቴ.26፥39)። የሳቸውን በጠላቶቻቸው እጅ መያዝ ለመቋቋም ሐዋርያትን ሰይፍ እንዲያመጡ ወይም እንዲገዙ ጠይቀዋል። መስቀያው ላይ ሆነው ያለ ረድኤት ስለተዋቸው እግዚአብሔርን አማርረዋል። እነዚህ ከወንጌሎች የተ ወሰዱ ማስረጃዎች ኢየሱስ ፈጽሞ በገዛ ፈቃዳቸውና በፍላጐታቸው ራሳቸውን ለሞት አሳልፍው ላለመስጠታቸው በቂ ማረጋገጫ ይሰጣሉ። በተጻራሪው ኢየሱስ ሊይዟቸው ከመጡ ወገኖች እግዚአብሔር ያድናቸው ዘንድ ደጋግሞ ጸልየዋል።

እስላም በዚህ በስቅለት ጉዳይ ላይ ያለው አቋም በጣም ግልጽና ወጥነት ያለው ነው። ኢየሱስ ፈጽሞ አልተሰቀሉም። የሰቀሉት በኢየሱስ የተመሳሰለባቸውን ሌላ ግለሰብ ነበር።

ታዲያ የትኛውን ነው የሚቀበሉት? ኢየሱስ በገዛ ፍላጐታቸው ራሳቸውን ለስቅላት አለመዳረጋቸውን ወንጌሎች ማስረጃ እያቀረቡ የለም ሰውን ለማዳን ሆን ብለው ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል የሚለውን የክርስትና ትረካ? ወይስ ብሩህና ቁርጥ ያለውን ወጥ የእስላም አተራረክ? ከወጥነቱና ከተጣጣ ሚነቱ አኳያ ይፍረዱ። ኢየሱስ ተሰቅለው ለመሞት ራሳቸውን በፈቃደኝነት አሳልፈው ሰጥተዋል ትላለች–ቤተክርስቲያን። የወንጌል ጥቅሶች ግን ይህን አባ ባል የሚጻረር ሁኔታ ይተርካሉ። ይህ ራሱ በቤተክርስቲያኗ የፈጠራ ትረካ ላይ ጥርጣሬ አያሳድርምን?

ኢየሱስ በጠላቶቻቸው እጅ መዋረዳቸውን፣ መረገጣቸውን፣ መደብደባቸውንና ከዚያም ተሰቅለው መገደላቸውን ቤተክርስቲያን ትናገራለች።

እስላም ግን ኢየሱስ ከመያዝ እግዚአብሔር ያዳናቸው መሆኑን፣ አለመገደላቸውንና አለመሰቀላቸውን ያረጋግጣል።

ለኢየሱስ ክብር ይበልጥ ተገቢው የትኛው ነው? የቤተክርስቲያን አተራረክ ወይስ የእስላም አተራረክ? እራስዎ ያስቡበትና ትክክለኛውን ለራስዎ ይምረጡ።

## ተዋረዱ ወይስ ከውርደት ዳኑ?

ኢየሱስ በወታደሮች ተይዘው መደብደባቸውን፣ ምራቅ ተተፍቶባቸው መገረፋቸውን፣ መረገጣቸውን፣ የተፌዘባቸውና መሳቂያ መሳለቂያ መደረጋቸውን፣ በመጨረሻም መስቀያ ላይ ተሰቅለው በመቸንከር መገደላቸውን ቤተክርስቲያን ታስተምራለች።

እስላም የሚለው ግን ኢየሱስ ከውርደት ድነው ክብራቸውን አላህ አስጠብቆላቸዋል፣ ተሰቅሎ ከመሞትም አትርፎአቸዋል ነው።

ኢየሱስ ከዚያ የመያዝ አደጋ ያድናቸው ዘንድ ሌሊቱን ሙሉ እግዚአብሔርን በመለመን ሲጸልዩ ማደራቸውን፣ ያች ጽዋ ታልፋቸው ዘንድ ፈጣሪአቸውን አጥብቀው መማጸናቸውን፣ ሐዋርያት ከርሳቸው ለመከላከል ሰይፍና ጐራዴ እንዲያዘጋጁ መጠየቃቸውንና እግዚአብሔር የመላእክት ሠራዊት እሳቸውን ለመርዳት እንዲልክ መለመን እንደሚችሉ መናገራቸውን ወንጌሎች የዘገቡት መሆኑን እዚህ ላይ ልብ ይበሉ።

ታዲያ ለኢየሱስ ክቡርነት ይበልጥ አግባብ አለው ብለው የትኛውን ይመርጣሉ? ስለ ኢየሱስ መዋረድና ተጐሳቅሎ መሰቀል የሚያወራውን ክርስቲያናዊ ትረካ? ወይስ እግዚአብሔር እየሱስን ከመያዝ፣ ከመዋረድና ከመሰቀል ያዳናቸው መሆኑን የሚናገረውን እስላማዊ ትረካ? ስለ ኢየሱስ መጨረሻ የበለጠና

ተገቢ የሆነ ከበሬታ የሚሰጠው የትኛው ነው? ከራሳቸው ከኢየሱስ ጸሎትና ከምሕላቸው ጋር ይበልጥ የሚጣጣመው የትኛው ነው? ከፉኛ ተደናግጠው የተረበሹትንና ከልብ በማዘን እግዚአብሔርን እንዲረዳቸው ይለምኑ የነበሩትን ኢየሱስ ለማዳን እግዚአብሔር ጣልቃ የገባ መሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለምን?

## ውድቀት ወይስ ስኬት?

በክርስትና አባባል መሠረት የኢየሱስ ፍጻሜ እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ መስቀያ ላይ በመቸንከር ከከፉ ውርደትና ረዳት የለሽነት ጋር መገደል ነበር።

በእስላምና በታሪክም እንደተረጋገጠው የሙሐመድ መጨረሻና ፍጻሜአ ቸው ተልዕኳቸውን በሚገባ አሟልተው የተከታዮቻቸው ስኬታማ መሪ በመ ሆን ነበር የተጠቃለለው።

ከስኬታማነት መመዘኛ አንፃር ማንኛቸውን ነው የሚመርጡት? በተል ዕኮው ውድቀት የገጠመውን፣ ራሱን ከጥቃት መከላከል የተሳነውን ወይም ተከ ታዮቹ ከጥቃት ሊከላከሉለት ያልቻሉትንና ፍጻሜው በአሳፋሪ ሁኔታ መስቀያ ላይ ያበቃውን? ወይስ በተልዕኮው ስኬታማ የነበረውን፣ መንግሥት የመሠ ረተውን፣ የመንግሥቱ መሪ የሆነውንና በመጨረሻም የተለመደው ዓይነት ሞት የሞተውን? ማንኛቸውን ነው የበለጠ የሚያደንቁት? ረዳት የለሽ ሆኖ መስቀል ላይ የተገደለውን? ወይስ ድል አድራጊ ነቢይና ርዕሰ መንግሥት የሆነውን? ወንድሜ የራስዎ ምርጫ ይኖርዎት።

## ኢየሱስና ክርስትና

ኢየሱስ እግዚአብሔር አንድ ነው ያሉ ሲሆን ክርስትና ግን ሦስትም አንድም ያደርገዋል። ኢየሱስ እኔ የሰው ልጅ ነኝ ያሉ ሲሆን ክርስትና ግን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓቸዋል። ኢየሱስ አንድ ሰው የሚድነው

ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ነው ሲሉ ክርስትና ግን መድህን ማግኘትን ከኢየሱስ መስቀል ጋር የተያያዘ አድርጐታል። ኢየሱስ የተላኩት ለሕዝበ እስራኤል ብቻ መሆኑን ሲናገሩ ክርስትና ግን ተልዕኳቸውን ለሕዝቦች ሁሉ አድርጓል። ኢየሱስ የመጡት የሙሴን ሕግ ለመፈጸም መሆኑን የተናገሩ ሲሆን ክርስትና ግን ያን ሕግ ሰርዟል።

ታዲያ ከዚህ ማጠቃለል የምንችለው ምንድነው? መልሱ ግልጽ ነው። ክርስትና ለኢየሱስ ቃል ግድ የለውም የሚል ነው። ክርስትና ቁብ የሚሰጠው ለጳውሎስ ቃል፣ ለጳጳሱ ቃልና የቤተክርስቲያን ሰዎች ለሚወስኑት ነገር ብቻ ነው።

በተቃራኒው ግን ሙስሊም ምሑራንና ተቋሞች አንድ እስላማዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ሲፈልጉ የእስላም ዋነኛ ምንጮች ወደ ሆኑት ቁርአንና የነቢዩ ቃሎች ስብስብ (ሐዲስ) ነው በቀጥታ የሚሄዱት። እስላም የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) በቁርአንና በነቢዩ ቃል ውስጥ አካቶ ይዟል።

ታዲያ የትኛው ነው ለመለኮታዊ ምንጮች ይበልጥ ተገዥ የሆነው? ክርስትና ወይስ እስላም?

# ምዕራፍ 4

# የሁለቱ ሃይማኖቶች የእምነት መሠረቶች

## መሠረታዊ እምነቶች

የክርስትና መሠረታዊ እምነቶች የሚከተሉት ናቸው:-

1. ሥላሴ:- እግዚአብሔር ሦስትም አንድም ነው።
2. በሥጋ መወለድ:- ኢየሱስ ሰውም እግዚአብሔርም ነው።
3. ኬኖሲስ:- ኢየሱስ የአምላክነት ባህሪውን በመተው የአምላክ አገልጋይ ሆኗል።
4. ስቅለት:- የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል እግዚአብሔር ብቸኛ ልጁን ተሰቅሎ እንዲገደል ለመስዋእት አሳልፎ ሰጥቷል።
5. መድህን:- የሰው ልጅ በኢየሱስ በማመኑ ብቻ መድህን ያገኛል።
6. መሠረታዊ የትውልድ ኃጢአት :- የሰው ልጅ ከሥረ-መሠረቱ ኃጢአተኛ ሆኖ በመፈጠሩ ከኃጢአት ነጻ ሆኖ መጽደቅም ሆነ ነፍሱን ማዳን አይችልም።
7. ሥጋ ወደሙን መቀበል:- ዳቦ በመብላት ከኢየሱስ ሥጋ መቀላቀልና ወይን ጠጅ በመጠጣት ከደሙ ጋር መዋሐድ።

እነዚህ አበይት የሆኑ የክርስትና እምነት መሠረቶች ናቸው። አስተዋይና አመዛዛኝ የሆነ ፈጣን አመለካከት ያለው ሰው እነኚህ የእምነት መሠረቶች ሚዛናዊነትና ምክንያታዊነት የሌላቸው፣ስሜት የማይሰጡ ኢ–ሎጂካዊ መሆና ቸውን ከመቅጽበት ይገነዘባል። ይህም ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ፣ ብሉይ ኪዳን የሚናገረውንየሚቃረኑና ወንጌሎቹ ውስጥ በተዘገበው መሠረት ኢየሱስ ራሳቸው ካስተማሩት ጋር የሚጻረሩ ናቸው። እነኚህ ክርስቲያናዊ እምነቶች ተቀምረው የተመሠረቱት በኢየሱስ ሳይሆን በጳሉስና በኋለኞቹ የቤተክርስቲያን መሪዎች አማካይነት ነው።

በተቃራኒው ደግሞ እስላም የሚከተሉትን የእምነት መርሆዎች ያራምዳል:-

1. እግዚአብሔር ጥንትም ዛሬም ምንጊዜም አንድ ብቻ ነው።

2. ኢየሱስ ሰውና የእግዚአብሔር ነቢይ ናቸው። የእግዚአብሔር ልጅ አይደሉም። የማርያም ልጅ ናቸው።

3. ኪኖሲስ አልተከሰተም፣ኢየሱስ የሰብአዊ ፍጡርነት ባህሪይ የሆነ አንድ ተፈጥሮና ባህሪይ ብቻ አላቸውና።

4. ኢየሱስ አልተሰቀሉም። የሰውን ልጅ ለማዳን እግዚአብሔር ኢየሱስን መስቀል አያስፈልገውም። ኢየሱስን ማሰቃየት ሳያስፈልግ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ማዳን ይችላል።

5. ሰው የሚድነው በእግዚአብሔር በማመንና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንጂ ሌላውን ሰው ሰቅሎ በመግደል አይደለም።

6. የሰው ልጅ ኃጢአ ሆኖ አይወለድም። ሰው የተወለደው ከኃጢአት ነጻ ሆኖ ነው። የሰው ልጅ እንደ ምርጫው ኃጢአተኛ ወይም ጻድቅ የመሆን ብቃት አለው። ስለዚህም በትውልድ የተላለፈበት ጥንታዊ ኃጢአት (Orignal sin) የሚባል ነገር የለም።

7. ሥጋ ወደሙ የሚባለው ከቤተክርስቲያን የፈጠራ ሥራዎች አንዱ ነው። ኢየሱስ ይህን ፈጽሞ አላደረጉም፣ አላስተማሩምም። ለመዋሐድ ዳቦና ወይን ጠጅ አስፈላጊ አይደሉም። ጥሩ ሰው ሆኖ እግዚአብሔር ዘንድ ተቀባ ይነት ለማግኘት አስፈላጊው ለእግዚአብሔር በቅንነት መታዘዝ ብቻ ነው።

ይበልጥ ሎጂካዊ ይበልጥ ሚዛናዊና ተጨባጭ ሆኖ የሚያገኙት የትኛውን ነው? የክርስትና እምነት መሠረቶችን ወይስ እስላማዊ የእምነት መርሆዎቹን?

## ልጆችና ውሾች

በመጀመሪያ ላይ ኢየሱስ የከነዓኒቷን ሴትዮ ልጅ መፈወስ እምቢ ብለዋል። ለምን? ምክንያቱም ራሳቸው እንደተናገሩት የተላኩት ለጠፉት የቤተ እስራ ኤል በጐች ብቻ በመሆኑ ነው (ማቴ.15፥22–27)። የሕጻናቱን ዳቦ ወስዶ ለውሾች መስጠት ተገቢ አለመሆኑንም አክለው ገልጸዋል።

ሕጻናቱ እነማን ናቸው? ውሾቹስ እነማን ናቸው? ራስዎ መልሱን ያውቁ ታል ብዬ አምናለሁ። በምንባቡ መሠረት ልጅቷ እስራኤላዊት ባለመሆኗ ምክን ያት ሊፈውሷት እምቢ ካሉ ዘንዳ ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም ሕጻናቱ ሕዝበ እስራኤል ናቸው፣ ውሾቹ ደግሞ አሕዛብ ማለትም እስራኤላዊ ያልሆኑ ሁሉ ሕዝቦች ናቸው ማለት ነው።

ስለዚህም ወንጌል በሚነግረን መሠረት ኢየሱስ ያሉት ነገር እስራኤላዊ ከሆናችሁ ብቻ ከሕጻናቱ ትቆጠራላችሁ ነው። ካልሆናችሁ ግን ከውሾቹ ናችሁ! ማለት ነው።

በተቃራኒው ግን እስላም ሰዎችን ሕጻናትና ውሾች ብሎ በሁለት መደብ አይከፍላቸውም። እስላም ሕዝቦችን ምርጦችና መናኛዎች ብሎ በዘር በጐሳና በብሔር መድልዖ መሠረት ላይ አይከፋፍላቸውም። እስላም ነቢዩ ሙሐመድ እንደተናገሩት ሁሉ ሰዎች እንደ ማበጠሪያ ጥርስ የማይበላለጡና እኩል የሆኑ መሆናቸውን ያስተምራል። በተጨማሪም ነቢዩ ሰው ሁሉ ከአዳም የተፈጠረና አዳም ደግሞ ከአፈር የተፈጠረ በመሆኑ እግዚአብሔርን በመፍራቱ ጽድቅ

ሥራው ብቻ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ከሌላው ሰው በምንም የማይበልጥ መሆኑን ተናግረዋል።

ታዲያ የትኛውን ሃይማኖት ነው የሚመርጡት? ሰዎችን በሕጻናትና በወ ሾች መደብ ለሁለት የሚከፍለውን ሃይማኖት ወይስ የመላውን ሰው ልጅ እኩልነት አበክሮ የሚያስተምረውን ሃይማኖት? የፈለጉትን ይምረጡና ለምርጫዎ ትክክለኛነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለብዎት ያስታውሱ።

## ኢየሱስ ለነማን ተላኩ?

ኢየሱስ የተላኩት ለጠፉ የቤተ እስራኤል በጎች መሆኑን ተናግረዋል (ማቴ.15፥24)።

የእስላም ነቢይ የሆኑት ሙሐመድ ግን የተላኩት በሁሉም ዘመንና ሥፍራ ላሉ ሕዝቦች በሙሉ መሆኑን ተናግረዋል። ቁርአንም ይህንኑ ያረጋግጣል።

የራስዎን ነቢይ መምረጥ ቢኖርብዎት ማንኛቸውን ነው የሚመርጡት? የለም ወደ ቤተ እስራኤል እንጂ ወደ እርስዎ አልተላክሁም የሚለውን? ወይስ ወደ እርስዎ ነው የተላክሁት የሚለውን ነቢይ? ያስቡበት። ግልጽና ቀላል ነውና።

## ከፊሉን እውነት ብቻ ወይስ ሁሉንም?

ክርስትና ኢየሱስ ከፊሉን እውነት ማለትም የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ይዘው መምጣታቸውን ይናገራል። ይህም ኢየሱስ ራሳቸው የተናገሩት ጉዳይ ነው (ዮሐ.14፥26)። ሌላ ሰው እውነታውን በተሟላ መልኩ ይዞ እንደሚ መጣም ተናግረዋል።

ታዲያ ትክክለኛውና የተሟላው የእግዚአብሔር ቃል አድርገው የሚቀ በሉት የትኛውን ነው? ክርስትናን ወይስ እስላምን? ኢየሱስ ራሳቸው

መልዕክታቸው የተሟላ አለመሆኑንና የተሟላውን የእግዚአብሔር መልዕክት ይዞ ሌላ ሰው የሚመጣ መሆኑን ተናግረዋል። የተባለው ያ የተሟላ የማጠቃለያው መለኮታዊ መልዕክት ቁርአን መሆኑን ቁርአን ራሱ ገልጿል። ሁለቱንም ወገኖች ስለራሳ ቸው የተናገሩትን በመቀበል የእግዚአብሔር የተሟላ መልዕክት አድርገው ለመቀበል የሚያዘነብሉት ወደየትኛው ነው? እውነተኞችና እምነት የሚጣ ልባቸው ሁለት ግለሰቦች፣ አንደኛቸው የኔ መልዕክት የተሟላ አይደለ ምና የተሟላውን መልዕክት ወደፊት ሌላ ግለሰብ ያመጠዋል የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ግለሰብ ያ የተባለው የተሟላ መለኮታዊ መልዕክት ይኸውላችሁ የሚል ነው። ለሁለቱም ሰዎች እኩል ተአማኒነትን ከመስጠት ላይ በመንደርደር ለተሟላ መልዕክትነት የትኛቸውን ይመርጣሉ?

## አጠቃላይነት

ኢየሱስ ወንጌል ውስጥ የነቢዩ ሙሐመድን መምጣት የተነበዩ ቢሆንም ቤተክርስቲያን የምታራምደው ክርስትና ግን የሙሐመድን ነቢይነት አውቆ አይቀበልም።

እስላም ግን እንደ አዳም፣ ኖሕ፣ አብርሃም፣ ሉጥ፣ እስማዒል፣ እስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ ኢየሱስና የመጨረሻው የአላህ ነቢይ የሆኑትን ሙሐመድን ለመሳሰሉ የአላህ ነቢያት በሙሉ ዕውቅና ሰጥቶ ይቀበላል።

ከአጠቃላይነቱ መመዘኛ አንፃር የትኛው ሃይማኖት ነው ሌላኛውን ሃይማኖት አጠቃሉ የያዘው? ክርስትና ወይስ እስላም? ዛሬ ባለው መልካቸው ከሁለቱ ሃይማኖቶች ውስጥ ሌላውን ሃይማኖት እውስጡ አካትቶ ያቀፈው የትኛው ነው? እስላም ክርስትናን ያካተተ ከሆንና ክርስትና እስላምን እውስጡ አካትቶ ያላቀፈ ከሆነ፣ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ቢኖርብዎት ከአጠቃላይነቱ አኳያ የትኛውን ሃይማኖት ይምርጣሉ? «ሀ» «ለ»ን አካትቶ ከያዘና «ለ»ግን «ሀ»ን አካትቶ ያልያዘ ከሆነ፣ እርስዎ ከሁለቱ አንደኛውን መምረጥ ቢኖርብዎት የትኛውን መያዙ የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል? «ሀ»ን ወይስ

«ለ»ን? በማቴማቲክስ ሕግ ላይ በመመርኮዝ–ለክርክር ሲባል እንኳ–እስኪ ምርጫዎን ያካሂዱ።

እዚህ ላይ ማለት የፈለግሁት አጠቃላይነት ለነቢዮች ሁሉ ዕውቅና ሰጥቶ የመቀበል አጠቃላይነት ነው።

## በውርስ የሚተላለፍ ኃጢአት

በክርስትና አመለካከት የሰው ልጅ ሲወለድ ኃጢአተኛ ሆኖ ይወለዳል፣ ኃጢአት የሰው ልጅ ተፈጥሮ አካል ነው። እያንዳንዱ ሰው ከልደቱ ጀምሮ በኃጢአት የተሞላ ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ብልሹና ውዳቂ ነው። ሰው ትሩፋት ያለው ወይም ሰናይ ፍጡር ሊሆን አይችልም። የሰው ልጅ የመጀመሪያው ኃጢአተኛ ከነበረው ከአቶ አዳም ኃጢአት የወረሰ ፍጡር ነው። ሰው ክፉና አደገኛ አውሬ ነው።

በእስላም አመለካከት ግን የሰው ልጅ ያለ አንዳች ኃጢአት ንጹሕ ሆኖ ነው የሚወለደው። አዲስ የሚወለድ ሕጻን ከኃጢአት የጠራ ንጹሕ ፍጡር ነው። አንድ ሰው በተግባር ኃጢአት እስካልፈጸመ ድረስ ኃጢአተኛ አይደለም። አንድ ሰው ኃጢአትን ከቅድመ አባቶቹ አይወርስም ወይም ለተወላጆቹ ኃጢአት አያስተላልፍም። የሰው ልጅ በነጻ ፍላጐቱና በገዛ ምርጫው ምግባረ ሰናይ ጻድቅ የመሆንና አጥፊ ኃጢአተኛ የመሆን እኩል የሆነ ብቃትና ተፈጥሮ አለው። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር መመሪያ የሚያስፈልገው ሲሆን የእግዚአብሔርን መመሪያ የመታዘዝ ወይም ያለ መታዘዝ የራሱ የሆነ ነጻ ምርጫና ውሳኔ የማድረግ ብቃት አለው።

ስለ ሰው ልጅ ሎጂካዊ የሆነ ጽንሰ ሐሳብ የትኛውን ነው መምረጥ የሚሹት? የሰው ልጅ በተፈጥሮው ኃጢአተኛ ሆኖ የተወለደ ነው የሚለውን? ወይስ የሰው ልጅ የሚወለደው ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ ነው የሚለውን? በተፈጥሮው ብልሹ ሆኖ የተፈጠረ ሰው ወይስ መሆን የሚፈልገውንና የመረጠውን የመሆን ብቃት ይዞ የተፈጠረ ሰው?

## እባብ ወይስ ሰይጣን?

መጽሐፍ ቅዱስ እባብ ሔዋንን እንዳሳሳተና ሔዋን ደግሞ በተራዋ አዳምን በማሳሳት ከተከለከለው ዛፍ እንዲበላ እንዳደረገች ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ዋነኛው አሳሳች እባብ ሲሆን ሔዋንም አሳሳች ነች።

እባብ እንዴት ሰው ዘንድ ተደማጭነት አግኝቶና ሰብዓዊ ሕሊናን ገፋፍቶ ማሳሳት ይችላል? በተጨማሪም ሔዋንን አሳሳች ፍጡርና የስሕተት መንሥኤ አድርጐ ማቅረቡ ፍትሕ ማጓደል ነው።

ይህን ሁነት አስመልክቶ እስላም ዘንድ ያለው ታሪክ ግን ሁለቱም ማለትም አዳምና ሔዋንም የተሳሳቱት በሰይጣን ጉትጐታ መሆኑን ያስረዳል።

ለሔዋን ፍትሐዊና ይበልጥ ምክንያታዊ የሆነው ትረካ የትኛው ነው? እባብ ሰውን ማሳሳት ችሎ ሔዋን ደግሞ በተራዋ አዳምን አሳሳተች የሚለው? ወይስ የሁለቱም አሳሳች ሰይጣን ነው የሚለው? ሌላው ዋነኛ ጥያቄ እንደ እባብ ያለ እንስሳ ማሰብና ማስተዋል የሚችል አእምሮ ያለውን ሰብዓዊ ፍጡር–ሔዋንን– ማሳሳት ይችላል? የሚለው ነው። የትኛው አተራረክ ነው ይበልጥ የሚታመነው? የመጽሐፉ ቅዱሱ ታሪክ? ወይስ የቁርአኑ ታሪክ?

## ተግባርና ፍርድ

ኢየሱስ እያንዳንዱ ሰው እንደሥራው የሚሸለም መሆኑን ተናግረዋል (ማቴ.16፥27)። ነገሩ እንዲህ ከሆነ ዘንድ ኢየሱስ ለምን ተሰቀሉ? ኢየሱስ ያሉት በሥራችሁ ትድናላችሁ ነው እንጂ መዳን የሚገኘው በሳቸው መሰቀል መሆኑን ፈጽሞ አልጠቀሱም። ይህም በስቅለት መዳንን አስመልክቶ የቤተክርስቲያን ክርስትና ትረካ ከኢየሱስ ትምህርቶች ጋር አንዳች አግባብነት የሌለው ባዶ ፈጠራ መሆኑን በድጋሚ የሚያረጋግጥ ነው።

ቤተክርስቲያን የኢየሱስን ብሩሕ ትምሕርቶች በጭፍኑ ትጻረራለች። የክርስትና መሠረታዊ እምነቶችም የቤተክርስቲያን የፈጠራ ውጤቶች ናቸው። ስለዚህም የዛሬው ክርስትና መለኮታዊ ሃይማኖት አይደለም። የኢየሱስን ስም ብቻ እንደ መሣሪያ እየተጠቀመ በቀጥታ ኢየሱስ ያስተማሩትን የሚቃረን አቋም ያራምዳል።

እስላም ግን ሙሉ በሙሉ ግልጽና ከራሱ ጋር የተጣጣመ ወጥ ሃይማኖት ነው። አንድ ሰው መዳን የሚችለው በእግዚአብሔር በማመንና ትዕዛዞቹን በመፈጸም ብቻ ነው። ሌሎች ስለኛ በኛ ፈንታ በሚሠሩት ነገር መዳን አይቻልም።

ታዲያ ሕሊና ሊቀበለው የሚችል ምክንያታዊነት ያለው አድርገው የሚመርጡት የትኛውን ነው? የቤተክርስቲያኑን የመድህን ፕላን ወይስ የእስላምን የመድህን ዕቅድ?

## መዳን የት አለ?

መላእክት ኃጢአንን ሰብስበው ወደ ገሀነም እቶን እንደሚወረውሯቸው ኢየሱስ ተናግረዋል (ማቴ 13፥41)። ይህ ማለት ደግሞ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን አላዳኗቸውም ማለት ነው። ይህም ኢየሱስ የተሰቀሉት የሰውን ልጅ ከኃጢአት ለማዳን ነው የሚለውን የቤተክርስቲያን የመድህን ንድፈ ሐሳብ ይጻረራል። ኢየሱስም ይህን የቤተክርስቲያን አባባል ይቃረናሉ። በሌላ አገላለጽ ቤተክርስቲያን ግልጽ የሆኑ የኢየሱስ ትምሕርቶችን በመጻረር መዳን የሚገኘው በኢየሱስ ስቅለት ነው የሚል ፈጠራ አቅርባለች። ይህም ክርስትና ዛሬ ባለ መልኩ ከኢየሱስ ትምሕርቶች በጣም የራቀና ተቃራኒው መሆኑን ያረጋግጣል።

እስላም ግን እግዚአብሔር ካስተላለፈው መለኮታዊ ራእይና ነቢዩ ካስተማሩት ትምሕርት ጋር አንድና ተመሳሳይ (Identical) ነው።

መሠረቱ ነው ከሚላቸው ምንጮቹ ጋር ይበልጥ የሚጣጣመው የትኛው ነው? ክርስትና ወይስ እስላም? ክርስትና ከኢየሱስ ትምሕርቶች ጋር የሚቃረን

ሲሆን እስላም ግን ከመለኮታዊ ራእይ ምንጮቹ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣምና በነርሱ ብቻ የሚመራ ነው።

## ጥምቀት

ኢየሱስ በቤተክርስቲያን አባባል ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔር በመሆናቸው ከኃጢአት ነጻና ፍጹም የማይሳሳቱ ናቸው ይላል–ክርስትና።

ወንጌል ግን ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ አማካይነት በጆርዳኖስ ወንዝ መጠመቃቸውን ይናገራል (ማቴት 3፥13–14)። መጠመቃቸው ኃጢአተኛ መሆናቸውን ያሳያል፤ ለምን ቢባል ጥምቀት ከኃጢአት መጽዳት ማለት ነውና።

ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እንደምትለው ከኃጢአት ነጻ፣ ወንጌል እንደሚለው ደግሞ ኃጢአተኛ እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? ይህም ቤተክርቲያን ወንጌል የሚናገረውን የማታዳምጥ መሆኗንና የዛሬው ክርስትና ቤተክርስቲያን–ሠራሽ እንጂ እግዚአብሔር ያስተላለፈው ሃይማኖት አለመሆኑን ያረጋግጣል።

በተቃራኒው ግን የእስላም ሃይማኖት ቁርአን ከተናገረውና ነቢዩ ሙሐመድ ከተናገሩት የተመሠረተ ነው። አንድም እስላማዊ እምነት እግዚአብሔር ቁርአን ውስጥ የተናገረውን ወይም ነቢዩ ሙሐመድ ያስተማሩትን ፈጽሞ አይቃረንም።

ለእምነትነት የትኛውን ነው የሚመርጡት? ሰው ከራሱ ፈጥሮ የሰራውን ሃይማኖት? ወይስ ከእግዚአብሔር የተላለፈውን ሃይማኖት?

## ቤዛነት በተተኪነት

ኢየሱስ መስቀል ላይ ተሰቃይተው ከሞቱ በኋላ የኛን ኃጢአት ለመሸከም ሲባል ለሦስት ቀናት ወደ ገሀነም መሄዳቸውን ክርስትና ያስተምራል። እኛን ከኃጢአት ለማዳን ሲሉ እኛን ወክለውና ስለኛ ሆነው መቀጣታቸውን ይናገራል።

እስላም ግን ማንም ሰው ሌላውን ሰው ተክቶና ስለ እሱ ሆኖ በውክልና አይቀጣም፤ መቀጣትም አይገባም ይላል። ማንም ለማንም ሊሸለምም ሆነ ሊቀ ጣለት አይችልም። እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ራሱ ሥራዎች ተጠያቂና ኃላፊ ነው። እግዚአብሔር ፍርድ አስተካካይና ፍትሐዊ ነውና አንድን ሰው ብሌላኛው ሰው ወንጀል አይቀጣውም። እግዚአብሔር ርህሩኅ ነውና ኢየሱስን የመሰለ ምርጥና ንጹሕ ሰው አይቀጣም። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነውና ሰውን ከኃጢአት ለማዳን ያ የስቅለት ሂደት አስፈላጊው አይደለም። የኢየሱስ ስቅለት አላስፈላጊ ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ርህራሄና ፍትሕ ይጻረራል።

በርስዎ አመለካከት የትኛው ነው ይበልጥ ምክንያታዊና ይበልጥ ሎጂካ ዊው? ክርስትና እንደሚናገረው ለሌሎች ኃጢአት በውክልና መቤዥ? ወይስ እስላም እንደሚያስተምረው እያዳንዱን ሰው ለገዛ ራሱ ሥራዎች ተሸላሚና ተቀጪ የሚያደርገው እምነት? ፍርድ አስተካካይ ሆነው ይምረጡ። አንዱን ለማዳን ብሎ ሌላውን የሚቀጣ ሃይማኖት ይፈልጋሉ? ወይስ እያንዳንዱን ሰው ለሥራው ተጠያቂ የሚያደርገውን ሃይማኖት? ምርጫዎ የቱ ነው?

## የፍርዱ ቀን

የክርስትና መጽሐፍ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን የሚያጠቃልለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ብሉይ ኪዳን መጪውን የፍርድ ቀንም ሆነ የወዲያኛውን ሕይወት የማይቀበል ሲሆን ሐዲስ ኪዳን ግን ሁለቱንም ይቀበላቸዋል።

የእስላም መጽሐፍ ደግሞ ስለየፍርዱ ቀንና ስለ የወዲያኛው ሕይወት አበክሮ የሚያስተምረው ቁርአን ነው።

ይህን ነጥብ በአእምሮዎ በመያዝ ወጥነትና ተጣጣሚነትን ቢፈልጉ የትኛውን ነው የሚመርጡት? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቁርአንን? ሐዲስ ኪዳን የሚያረጋግጠው ሆኖ ብሉይ ኪዳን የፍርዱን ቀን መምጣት እንዴት ያስተባ ብላል? መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ አቢይ የእምነት መሠረት ላይ ወጥነት እንዴት አጣ? ይህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ላለመሆኑ ማረጋገጫ አይደ ለምን? ከወጥነቱና ከመጣጣሙ አኳያ የትኛውን ይመርጣሉ? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቁርአንን? ሚዛናዊ ሆነው ያስቡና ይወስኑ።

## ስቅለት ወይስ ሰናይ ተግባራት?

ክርስትና ኢየሱስ የተሰቀሉት የሰውን ልጅ ለማዳን ነው ይላል። እስላም ደግሞ ማንም ሰው ሌላው ሰው በመሰቀሉ አይድንም ይላል።

የምንድነው በእምነታችንና በሰናይ ተግባራችን ነው። ማንም ሰው የሌላውን ሰው ኃጢአት አይሸከምም። እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ራሱ ሥራዎች ውጤት ተጠያቂ ነው።

የትኛው የመድህን ዕቅድ ነው ይበልጥ ሎጂካዊነት የሚታይበት? የክር ስትና ወይስ የእስላም ኘላን? በሚዛናዊነት ያስቡበትና ምርጫዎን እቀበላለሁ።

## ያለ መጽሐፍ ወይስ ከመጽሐፍ ጋር

ክርስትና ኢየሱስ ለተከታዮቻቸው ምንም ዓይነት መለኮታዊ መጽሐፍ አልሰጡም ይላል።

እስላም ግን እግዚአብሔር ለምእምናን መሪ መጽሐፍ ይሆን ዘንድ ቁርአንን በመለኮታዊ ራእይ አስተላልፏል ይላል።

ከመርሕ አንጻር ይበልጥ አስተማማኝና ይበልጥ ተአማኒነት ያለው የትኛው ሃይማኖት ነው? መለኮታዊ መጽሐፍ የሌለው ወይስ መለኮታዊ የሆነ መጽሐፍ ያለው? ለመመሪያነት የትኛውን ይመርጣሉ?

## ቤተክርስቲያንና ሳይንስ

በአውሮፓ የዘመነ ዳግም ትንሣኤ (Renaissance) ሳይንቲስቶች ፍጥረተ ዓለምን፣ ሃይማኖትንና ሕይወትን አስመልክቶ በምርምር ላይ የተመሠረተ ምክንያታዊ አሳቤ ማራመድ ሲጀምሩ ቤተክርስቲያን አንገታቸው የሚቀነ ጠስበት ሠይፍ አዘጋጅታላቸው ትጠባበቅ ነበር። መሬት ክብ እንጂ ጠፍጣፋ

አይደለችም ወይም የዩኒቨርስ ማዕከል ፀሐይ እንጂ መሬት አይደለችም ስላሉ ብቻ ብዙ ሳይንቲስቶች ታስረዋል፣ ተገድለዋል ወይም ከነሕይወታቸው በእሳት ተቃጥለዋል። ቤተክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ወይም የቤተክ ርስቲያን ትረካዎችን ወይም የጳጳሱን ሥልጣን ከመፈታተን እንዲቆጠብ ሕዝ ቡን አስጠንቅቃለች።

እስላም ደግሞ በተቃራኒው ሰዎች ስለ ዩኒቨርስ፣ ስለ መሬት፣ ስለ ከዋክ ብት ስለ እንስሳት ሕይወት፣ ስለ ዕጽዋት ሕይወት፣ ስለራሳቸው አፈጣጠርና በአጠቃላይም ስለ ሕይወት እንዲመራመሩ ይገፋፉቸዋል። ሙስሊሞች በአዲስ ግኝቶቹ ምክንያት አንድም ሳይንቲስት ገድለው አያውቁም። የቁርአን አንቀጾች የሰው ልጅ ስለ ዩኒቨርስ እውነታዎች እንዲመራመርና እንዲያስስ ግልጽ ባለ ሁኔታ ያበረታታሉ። ሳይንቲስቶች ወይም ሊቃውንት ለእውነታ የተሻለ ቀረ ቤታ ስላላቸው ከሌሎች ይበልጥ እግዚአብሔርን እንደሚያውቁና እንደሚ ፈሩት ቁርአን ይጠቅሳል።

ታዲያ ከሳይንስ ጋር የበለጠ ጐን ለጐን የሚሄደውና የሚጣጣመው የትኛው ነው ይላሉ? ክርስትና ወይስ እስላም? በተለመደውና በስሜታዊነት ላይ በተመ ረኮዘው የወግ ምላሽ ዓይነት ላይ ሳይሆን አዲስ ባገኙት መረጃ ላይ ተመሥርተው ፍርድ ይስጡበት። ፍትሐዊ የሆነ መልስ ለመስጠት በእርግጥ ብዙ ሚዛናዊነት አሉዎት።

## ሥጋ ወደሙ

ክርስትና በቅዱስ ቁርባን ዳቦ ወደ ኢየሱስ ሥጋ፣ ወይን ጠጅ ደግሞ ወደ ደሙ ይለወጣል የሚል እምነት ያራምዳል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ዳቦ ሲበላ አካሉ ከኢየሱስ አካል ጋር ይዋሐዳል። ወይን ጠጅ በሚጠጣበት ጊዜ ከኢየሱስ ደም ጋር ይቀላቀላል።

ይህ እንዴት እንደሚሆን ወይም መሆን እንደሚችል ማንም ሰው አያው ቅም። በእንቆቅልሾች ላይ የተጨመረ ሌላው እንቆቅልሽ ነው። እዚህ ላይ እኛን የሚገደን የወይን ጠጅ መጠጣት የክርስትና አንድ አቢይ ክፍል የተደረገ የመሆኑ

ጉዳይ ነው። ነገሩ የክርስትና የአምልኮ ሥርዓት አካል ነው። በሌላ አገላለጽ ቢያንስ በሥጋ ወደሙ የቁርባን ሥርዓት ላይ አንድ ክርስቲያን ከኢየሱስ ደም ጋር ለመዋሐድ ሲል ወይን ጠጅ መጠጣት ይኖርበታል። ስለዚህ ወይን ጠጅ መጠጣት ክርስትና ውስጥ የአምልኮ ተግባር ሆኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ እስላም የወይን ጠጅ ወይም ማንኛውንም ሌላ ዓይነት አልኮል ነክ መጠጦችን–አንዲት ጠብታ ቢሆን እንኳ–በየትኛውም አጋጣሚ ወይም ሥነሥርዓት መጠጣት ይከለክላል።

ለሰው ልጅ ደህንነትና ለጥቅሙ የትኛው ሃይማኖት ነው የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው? ተከታዮቹ የወይን ጠጅ እንዲጠጡ የሚያዛቸው? ወይስ ፈጽሞ እንዳይጠጡ በማገድ እርም የሚያደርገው? በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የርስዎን ታማኝነትና ሚዛናዊነት አምናለሁ። የትኛው ሃይማኖት ነው የተሻለ ሰብእና የሚቀርጸው? አልኮለኛ ሃይማኖት ወይስ አልኮል–አልባ ሃይማኖት?

# ምዕራፍ 5

# የሥርዓተ አምልኮ አፈጻጸም በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

## ምልጃ

አንድ ሰው እግዚአብሔርን መለመን ከፈለገ ጥያቄው መጀመሪያ ራሱ ውስጥ ባለው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይታያል። ጥያቄውን መንፈስ ቅዱስ ካጸደቀው ወደ ኢየሱስ ያቀርበዋል። ከዚያ በኋላ ነው ኢየሱስ ጥያቄውን ለእግዚአብሔር የሚያስተላልፍለት።

እስላም ግን አንድ ሰው እግዚአብሔርን መለመን ከፈለገ ያላንዳች አማላጅ እና ያላንዳች አገናኝ በቀጥታ እሱን መጠየቅ ይችላል ይላል። እግዚአብሔር ፈጣሪ አምላካችን ነውና በኛና በርሱ መካከል አማላጅ አያስፈልገንም።

ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥታ ግንኙነት ቢፈልጉ የትኛውን ይመርጣሉ? የክርስትናን መንገድ ወይስ የእስላምን መንገድ? ጸሐፊዎችና ረዳቶች ያሉት አምላክ ይሻሉ? ወይስ ወዲያውና በቀጥታ ሊገናኙት የሚችሉትን አምላክ ይፍልጋሉ? አስበው አንዱን ይምረጡ።

## ንስሐ መግባት

በኃጢአት ተጸጽቶ ንስሐ መግባት የፈለገ ሰው ይህን ማድረግ ያለበት ቄስ ዘንድ ቀርቦ ሲሆን ቄሱ ደግሞ በተራው ንስሐውን ለእግዚአብሔር ወልድ ወይም ለእግዚአብሔር አብ ወይም ለሁለቱም ያቀርብለታል ይላል–ክርስትና።

እስላም የሚለው ግን አንድ ሰው በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ እውነተኛ ንስሐ (ተውበት) ማድረግ ከፈለገ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ምንም አገናኝ ወይም

አማላጅ ጉዳይ አስፈጻሚ ሳያስፈልገው በቀጥታ ጸጸቱን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ እንዲማለሰው መጠየቅ ይችላል ነው። ንስሐ መደረግ ያለበት በቀጥታ በሠሩት ሥራ ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር በመማጸን እንጂ በሌላ ሰው አማካይነት መሆን የለበትም። ንስሐ በሰውና በፈጣሪ አምላኩ መካከል የሚደረግ እንጂ ማንም ሰው ጣልቃ የሚገባበት ጉዳይ አይደለም።

የበለጠ ልባዊ ፍጹምነትን፣ የበለጠ ምስጢራዊነትንና የበለጠ መንፈሳዊነትን ያካተተው የትኛው መንገድ ነው? የክርስትና የንስሐ አፈጻጸም መንገድ? ወይስ እስላማዊ የንስሐ (የተውበት) መንገድ? ነጻ ሆነው ይምረጡ።

## ምሕረትና ይቅርታ ልመና ለምን?

ክርስቲያኖች ወደ ቤተክርቲያን በመሄድ እግዚአብሔር አብ ሳይሆን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ይቅር እንዲላቸውና ምሕረት እንዲያደርግላቸው ይለምናሉ። ኢየሱስ እነሱን ከኃጢአት ለማዳን ተሰቅሎ ከሆነ ለምን ይቅርታና ምሕረት መለመኑን ይቀጥሉበታል? ስቅለቱ አድኗቸው ከሆነ ይቅር ይ ላቸው ዘንድ ኢየሱስን ለምን ይማጸናሉ? በስቅለት በመዳንና መድህንና ምሕረት በመለመን መካከል ተቃርኖ አለ።

ሙስሊሞች እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸውና ምሕረት እንዲያደርግላቸው ይጸልያሉ። ምሕረቱን በፍጹም ከሙሐመድ አይለምኑም። አንድ ሰው በፍጹም ልቦና ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰና ምሕረቱን ከለመነው ምሕረት ያገኛል ብለውም ያምናሉ።

የበለጠ ሎጂካዊና የበለጠ ጽድቅ ነው ብለው የሚያስቡት የትኛውን ነው? ምሕረት ከኢየሱስ መለመን ወይስ ከኢየሱስና ከዓለማት ፈጣሪ አምላክ ከእግዚአብሔር መለመን? ከውስጣዊ ቅራኔ ነጻ ሆኖ ይበልጥ እርስ–በርስ የተጣጣመው የትኛው ነው? መድህንን በስቅለት የሚያበረክተውና ምሕረትን ከኢየሱስ መለመኑንም የማይተወው ክርስትና? ወይስ መድህን የሚገኘው በእምነት፣ በመልካም ሥራዎችና ልባዊ በሆነ ንስሐ ወይም ተጸጽቶ መመለስ ነው የሚለው እስላም?

## ለእግዚአብሔር መታዘዝ

አንድ ሰው ጌታን በመጥራት ብቻ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ እንደማይችልና እርሱን መታዘዝ እንዳለበት ኢየሱስ ተናግረዋል (ማቴ 7፥21)። በኔ ስቅለት ስለ አመናችሁ ወደ ገነት ትሄዳላችሁ አላሉም። ኢየሱስ ያሉት በእግዚአብሔር ማመን ብቻ በቂ አይደለም፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መፈጸም አለባችሁ ነው።

ቤተክርስቲያንና ክርስትና ግን ኢየሱስ ከተናገሩት የተለየ ነገር ነው የሚናገሩት፣ ኢየሱስን አዳኝ ነው ብላችሁ እመኑ ትድናላችሁ ይላሉ። ይህም ቤተክርስቲያን ለኢየሱስ ቃልም ሆነ ለእግዚአብሔር ቃል ግድ የላትም ማለት ነው። ኢየሱስ የሚናገሩት እግዚአብሔር እንዲናገሩ ያዘዛቸውን ነውና።

እስላም የሚለው ኢየሱስ በዚህ ነጥብ እሉ ተብሎ የተዘገበውን ራሱን እን ዳለ ነው። በእግዚአብሔር እመኑ እግዚአብሔርን ታዘዙ፣ የሚያድናችሁ ይህ ብቻ ነው ይላል።

ቤተክርቲያን ግን የኢየሱስንም ሆነ የእግዚአብሔርን ቃል አትፈልግም። የምትፈልገው የራሷን የፈጠራ ተረት ነው። ኢየሱስ የተሰቀለው እኛን ለማዳን ነውና በዚህ ካመናችሁ ያሻችሁን ብትሠሩም ድናችኋል ትላለች።

ምን ይመርጣሉ? የቤተክርስቲያን ቃል ወይስ የእግዚአብሔር ቃል? በስ ቅለት መዳን ወይስ በእምነትና በሰናይ ተግባራት መዳን?

## ማንበብ የማይፈቀድላቸው

ቤተክርስቲያን ለተራ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ ለመፍ ቀድ ከመገደዷ በፊት ምዕተ ዓመታት አልፈው ምዕተ ዓመታት ተተክተዋል። ስለ እውነት ይህ ራሱ በጣም አስገራሚ አይደለምን? ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ አይፈቀድላቸውም ነበር። ማንበብ የሚፈቀደው ለካህናቱ

ብቻ ነበር። በተመሳሳይ መልኩም ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች እንዲተረጎም አትፈቅድም ነበር። በአጭሩ መጽሐፍ ቅዱስ በይፋና በብዙኃኑ ሕዝብ እንዲነበብ አይፈለግም ነበር። ለምን?

አንድ ሰው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ነው የምትለውን መጽሐፍ ቅዱስን ሕዝቡ እንዲያነበው ማበረታታት አለባት ብሎ ይጠብቃል። ታዲያ ቤተክርስቲያን ለዚህ ምን ማብራሪያ መስጠት ትችላለች? እስፔሺያሊስቶች ብቻ ናቸው መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት የሚችሉት ትል ይሆናል። ይሁን እንጂ እውነተኛው ምክንያት ሕዝቡ የመጽሐፍ ቅዱስን የርስ–በርስ ውስጣዊ ቅራኔ ዎች እንዳያይና የቤተክርስቲያን ዶክትሪኖች ሁሌም ከመጽሐፍ ቅዱስ ዶክት ሪኖች ጋር እንዴት እንደሚለዩ እንዳያውቅ ቤተክርስቲያን ስጋት ስላላት ነው። ሕዝቡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ስለ ቤተክርስቲያኗ ሐቁን እንዲያውቅ አልፈለገችም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይነበብና እንዳይተረጐም የከለከለችውም በዚህ ምክንያት ነው።

በተቃራኒው ግን እስላም ቁርአንን ማንበብ ታላቅ ምንዳ የሚያስገኝ የአምልኮት ተግባር ያደርጋል። ሙስሊሞች ዘወትር በየዕለቱ በየወሩና በየዓመቱም ቁርአንን ደግሞ ደጋግሞ እንዲያነቡ እስላም ግፊት በማድረግ ያበረታታል።

ይበልጥ ትርጉም የሚሰጠው የትኛው ነው? ሊከተሉት የሚገባ ቅዱስ መጽሐፋቸውን እንዳያነቡ ክርስቲያኖችን የምትከለክለው ቤተክርስቲያን? ወይስ መከተል ያለባቸውን ቅዱስ መጽሐቸውን እንዲያነቡ በሙስሊሞች ላይ ግፊት የሚያደርገው እስላም?

# ምዕራፍ 6

# ሥነ ምግባር በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

## እጅ መስጠት ወይስ አጸፋ መመለስ?

ኢየሱስ አንድ ሰው ቀኝ ጉንጫችሁን በጥፊ ከመታ የግራውን ጉንጭ አዙሩለት ይላል።

እርግጥ ከዚህ የሚወሰደው ትምሕርት ወይም የግብረገብነት ምሳሌ ግልጽ ነው።ትዕግሥት መቻቻልና ለሌሎች ይቅር የማለት ምሳሌ ነው። ቁም ነገሩ ግን ቀኝ ጉንጩን በጥፊ ካጮሉት በኋላ ለመደገም የግራ ጉንጩን የሚያዞር ማነው? ! የሚለው ነው።

በተቃራኒው ደግሞ እስላም፣በሕገ–ወጥ ሰው ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ብትመታ አጸፋውን የመመለስ ሙሉ መብት አለህ፣ ይሁን እንጂ ይቅር ማለት ከቻልክ በእውነት ጥሩ ሰው ትሆናለህ ይላል። በዚህም እስላም አጸፋውን የመመለስ ወይም ይቅርታ የማድረግ ምርጫ ይሰጠሃል። ኢየሱስ ግን አማራጭ አልሰጡህም። ያሉት ወደድክም ጠላህ ይቅርታ ማድረግ አለብህ ነው። እስላም ግን ራስህን የመከላከልና አጸፋ የመመለስ ተፈጥሯዊ መብት ይሰጠሃል። ኢየሱስ ያዘዙህ ይቅርታ እንድታደርግ ብቻ ሳይሆን ሌላኛውን ጉንጭህን ለተጨማሪ ጥፊ በማዞር እጅ እንድትሰጥ ነው!

የትኛውን ነው ይበልጥ ተግባራዊ፣ ይበልጥ ለሰው ልጅ ተፈጥሮ የቀረበና ይበልጥ ፍትሐዊ ሆኖ የሚያገኙት? አስገዳጅ ይቅርባይነት ወይስ አማራጭ ያለው ይቅርባይነት? ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ይበልጥ የሚጣጣመው የትኛው ነው? እንደ በግ እጅ መስጠት ወይስ ከፈለጉ ራስዎን መከላከልና ካሻዎትም ይቅርታ ማድረግ?

## ክፉውን መቃወም

ኢየሱስ ክፉውን መቃወም ከልክለዋል (ማቴ 5፥39)።

ቁርአን ግን ሰዎች ክፉ ሥራንና ክፉ ሠሪዎችንም እንዲቃወሙ ይገፋፋል። እያያንዳዱ ሙስሊምም ክፉውን ባለው አቅምና ዘዴ ሁሉ መቃወም አለበት።

ይበልጥ ማሕበራዊና ይበልጥ የተሟላ ከመሆኑ አኳያ የትኛውን ነው የሚመርጡት? ክፉውን አለ መቃወምን ወይስ ክፉውን ሥራና ሠሪዎቹንም መቃወምን? የትኛው ነው ይበልጥ መንፈሳዊና ይበልጥ ጽድቅ የሚመስለው? ሰዎችን ለማስተማር ቢሹ የትኛውን ነው የሚመክሯቸው? ክፉውን ሥራ በዝምታ ማየት ወይስ መቃወሙን?

## አሥርቱ ትዕዛዛት

ክርስትና ለአሥርቱ የሙሴ የኢየሱስና የሁሉም ነቢያት ትዕዛዛት አጽንኦት ይሰጣል። እስላምም ተመሳሳይ ትዕዛዞች ያሉት ሲሆን በተጨማሪ ግን ትዕዛዛቱን በሚጥሱ አጥፊዎች ላይ የተደነገጉ መቀጫዎች አሉት።

ክርስትና አትግደል ብሎ ያዛል፤ ዳሩ ግን በነፍስ ገዳይ ላይ መቀጫ ሳይጥል ነው። ዝሙት አትፈጽም ብሎ ያዛል፤ ነገር ግን በዝሙተኞች ላይ ቅጣት አይወስንም። አትስረቅ ብሎ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ በሌቦችና በዘራፊዎች ላይ ግን መቀጫ አይወስንም።

እስላም ግን ግልጽ፣ ፍትሐዊ፣ ጥብቅና አጋጅ የሆነ መቀጫ አበይት በሆኑ የወንጀል ዓይነቶች ላይ ይደነግጋል። እንዲህ ያሉ ወንጀሎች ቁርአን ውስጥ ተለይተው ተጠቅሰዋል።

ታዲያ ለሕብረተሰቡ የሚስማማውና ይበልጥ ሠላምና መረጋጋት የሚሰጠው የትኛው ነው? ትዕዛዝ መስጠትና መምከር ብቻ? ወይስ ትዕዛዝ

ማስተላለፍ፣ መምከርና አጥፊዎችን እንዲታረሙ መቅጣት? የበለጠ ውጤታማው የቱ ነው? የበለጠ የአጋጅነትና የእርምት ብቃት ያለው የትኛው ነው? ወንጀልን ቀንሶ የበለጠ ሠላምና ጸጥታ የሚያሰፍነው የትኛው ነው? ማሕበራዊ ሕይወት በቃል በሚሰጡ የምክር ቁርጥራጮች ብቻ እንዲሁ በቀላሉ በተረጋጋ መልኩ መጓዝ ይችላል? በአጥፊዎችና በሕግ ተላላፊዎች ላይ በሚወሰዱ የቅጣት እርምጃዎች ካልተደገፉ የባዶ ትዕዛዛት ጠቀሜታ ምንድነው?

## አርአያነት

ክርስትና ኢየሱስ እግዚአብሔር ወልድ ነው ይላል። እስላምን ግን ሙሐመድ ሰውና የእግዚአብሔር ነቢይ ናቸው ይላል። በአርአያነቱ የሚከተሉትና በምሳሌነቱ የሚመሩበትን የሚሹ ከሆኑ ለሰው ልጆች የተሻለና የበለጠ አብነት መሆን የሚችለው ማንኛቸው ነው? እግዚአብሔር ወልድ የተባሉት ኢየሱስ? ወይስ ሰው የሆኑት ሙሐመድ? ለሰው ልጅ ጥሩ የሥነ ምግባር ምሳሌ ለመሆን አግባብነት ያለው ማነው? ለሰው ልጆች አርአያ ሆኖ የተሻለ ማገልገል የሚችለው ማንኛቸው ነው? በክርስትና እምነት መሠረት አምላክ የተባሉትና የእግዚአብሔር ባሀሪይ እንዲላበሱ የተደረጉት ኢየሱስ? ወይስ የሰብዓዊ ፍጡር በሀሪይ ብቻ የተላበሱት ሙሐመድ? እንደ ሰው ልጅ መጠን ምሳሌና አርአያውን መከተል እችላለሁ ብለው የሚያስቡት የትኛቸውን ነው? አምላክ ነው የተባለውን ሰው? ወይስ ሰው የሆነውን ሰው ነው?

## ባህታዊነትና ምናኔ

መጽሐፍ ቅዱስ «..ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፣ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤» ይላል (ማቴ 6፥25)። ስለዚህች ዓለማዊ ሕይወት እና ስለ ሥጋዊ ፍላጐቶቿ አታስቡ ይላል።

ቁርአን ግን ስለ ወዲያኛው ሕይወት ማሰብና መጨነቅ አለባችሁ ነገር ግን ደግሞ የዚህን ዓለም ሕይወት ፍላጐቶችም ችላ ማለት የለባችሁም ይላል። ሁለቱም ሕይወቶች አስፈላጊ ናቸው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሳትጥስ ለዚህኛውም ዓለም ሕይወት ትኩረት ስጥ ይላል።

ከተግባራዊነት ብቃቱ አንጻር የትኛውን የበለጠ ይመርጣሉ? ወንጌሎች እንደሚያስተምሩት የዚህን ዓለም ሕይወት ፍላጐቶች ችላ ማለት ወይስ ቁርአን እንደሚያስተምረው ለሁለቱም ሕይወቶች ትኩረት መስጠት?

## ባለጸጋ

ፍጹም መሆን የሚፈልግ ሰው ያለውን ንብረት ሁሉ ሸጦ ካካፈለ በኋላ መጥቶ እንዲከተላቸውና ባለ ጸጋ ሰው ገነት የመግባት ዕድሉ በእጅጉ የመነመነ መሆኑን ኢየሱስ ተናግረዋል (ማቴ 19፥18-24)።

ያለዎትን ንብረት በሙሉ ቤትዎን፣ መሬትዎን፣ መኪናዎንና የቤት ዕቃዎን ሁሉ ይሸጡና ከዚያ በኋላ ነው ሊከተሏቸው የሚችሉት። ይህ እንግዲህ ኢየሱስ ያሉት ነገር ነው። ሀብታም ሰው በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም።

በተቃራኒው ግን ሕዝቡ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ ሀብትና ንብረት እንዲያፈራ እስላም ግፊት ያደርጋል። እስላም በሕጋዊ መንገድ የተገኘውን ሀብት ያከብራል፣ ሰዎች ሀብታቸውን በሕጋዊ መንገድ እንዲያወጡና ለአላህ ብለው እንዲለግሱትም ይገፋፋል። ሀብትህን ለትክክለኛውና ለተገቢው ነገር ካዋልክ ራስህንና ሌሎች ሰዎችንም ብዙ ትጠቅማለህ ብሎ ያስተምራል-እስላም። ድሆችን፣ ችግረኞችን፣ ወላጅ የሌላቸው የሙት ልጆችንና በዕዳ የተያዙ ሰዎችን መርዳት ትችላለህ ይላል። እስላም ሃብታም ሰዎችን በንቀት ዐይን አይመለከትም። ያጡ የነጡ ድሆች እንዲሆኑም አይገፋፋቸውም። አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ ብልህ ሀብታም ከሆነ ያፈራው ሀብት ለራሱና ለሌሎች ሰዎችም ጸጋና በረከት ይሆናል። በእስላም ውስጥ ዋነኛው መለኪያ ሀብትን በሕጋዊ መንግድ ማፍራትና በሕጋዊ መንገድ ማውጣት ነው።

የትኛውን ነው የሚመርጡት «ሀብትህን ሸጥና ተከተለኝ» የሚለውን? ወይስ «በሕጋዊ መንገድ ገንዘብህን አልማና በሕጋዊ መንገድ ተጠቀምበት» የሚለውን?

## የዋስትናው ውጤት

ኢየሱስ እኛን ለማዳን ነው የተሰቀለው ብላችሁ ካመናችሁ ትድናላችሁ፤ ገነትም በወዲያኛው ሕይወት የናንተ ትሆናለች ትላለች–ቤተክርስቲያን።

እስላም ደግሞ ስቅለት አልተፈጸመም፣ ተፈጽሟል ተብሎ ቢወሰድ እንኳ በአንዱ መሰቀልና በሌላው መድህን ማግኘት መካከል ግንኙነት የሌለ በመሆኑ ለማንም ሰው የመዳን ዋስትና ሊሰጥ አይችልም። በተጨማሪም ሰዎች በኢየሱስ ስቅለት ድነናል ብለው በጭፍኑ እንዲያምኑ ከተደረጉ የዚህ ውጤት የሥነ ምግባር ሥርዓቱ እንዲፈርስና የሞራል ሕግጋት ውድቅ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ሰዎች ቀድሞውኑ መዳንን ያገኙ ከሆኑ በጐ ተግባር ለመሥራትም ሆነ ከኃጢአት ለመወገድ እንዴት ግድ ይኖራቸዋል? ያሻህን ብትሠራ አንዴ በመሰቀሉ ካመንክ ድነሃል ከተባለ ግብረገብነት ምን ያደርግለታል።

በስቅለት መድህን የማግኘት እምነት የፈለግነውን ብንሠራ በስቅለቱ መዳንን አግኝተናል የሚል እምነት ስለሚያሳድርባቸው የኃጢአተኞችን ቁጥር ያሳድጋል። ጽድቅ ሠራንና ንጽሕናን አላስፈላጊና ትርጉም የለሽ ያደርጋል። በስቅለት በማመን ብቻ ገነት የመግባት ዋስትና ከተሰጠ ከዚያ በኋላ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ምንም ያህል አስፈላጊ አይደለም።

የእስላም አመለካከት ግን አንድ ሰው መዳን የሚችለው በእምነቱና በበጐ ተግባራቱ እንጂ ኢየሱስ እሱን በመወከል መስቀል ላይ ተቸንክሮ ሥቃይ የተቀበለለት መሆኑን በማመን አይደለም። በእስላም እምነት እያንዳንዱ ሰው በዚህች ዓለምም ሆነ በወዲያኛው እግዚአብሔር ፊት ለገዛ ሥራው ኃላፊና ተጠያቂ ነው።

ታዲያ የርስዎ ምርጫ የትኛው ነው? በኢየሱስ መስቀል በማመን መዳን ወይስ በእግዚአብሔር በማመንና መልካም ሥራ በመሥራት መዳን? የማህ በራዊ ተሐድሶ መሪ ቢሆኑ ሕዝቡን ቀደም ብሎ የማግኘት ዋስትና በተሰጠው መድህን እንዲያምንና ያሻውን እንዲሠራ ይመክራሉ? ወይስ እያንዳንዱ ግለሰብ በሚሠራው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ፊት ኃላፊነት ያለበት ተጠያቂ በመሆኑ ለዚህ ትኩረት እንዲሰጥ ይመክራሉ? የትኛው እምነት ነው የተሻሉ ተከታ ዮችንና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሆኑ ምግባረ ሰናይ ግለሰቦችን የሚያፈራው?

## የሰበካ አቢይ ርዕስ

ሰባኪዎች በየቤተክርስቲያኑና በየፀሎት ቤቱ አጽንኦት ሰጥተው የሚያተኩሩበትን አቢይ የሰበካ ርዕስ ብናስተውል የሚሰጡት ትምህርት በአብዛ ኛው በኢየሱስ ግለሰብ፣ በተአምሮቻቸው፣ በስቅለትና ከነኚህ በሚመነጨው መዳን ዙሪያ የሚሽከረከር ሆኖ እናገኛለን። ሰባኪያኑ ለሕዝቡ ምን ማድረግና ምን መተው እንዳለበት የሚነግሩት በጣም አልፎ አልፎ ነው።

ይህን ክስተት ጥቂት ጠለቅ ብለን ብንገመግም፣ የኢየሱስ ተአምሮች ዛሬ ያለፈ ታሪክ ብቻ በመሆናቸው ውጤታቸው በጣም አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን። ቁም ነገሩ ኢየሱስ በወቅቱ የፈጸሟቸው ተአምሮች ሳይሆን ኢየሱስ ትተዋቸው ያለፉ ትምሕርቶች ናቸው። ሰዎች በዕለታዊ ሕይወታቸው ውስጥ የሚመሩ ባቸው መመሪያዎች የኢየሱስ ተአምሮች አይደሉምና። የአንድ ነቢይ ተከታ ዮች ተጠቃሚ የሚሆኑት በነቢዩ ቃሎችና በመሪ ትምሕርቶቹ እንጂ በአንድ ወቅት ፈጽሟቸው በነበሩ ተአምሮቹ አይደለም።

ኢየሱስ የተናገሯቸው ነገሮች በጣም ውስን[1] ቢሆኑም ቅሉ ጽድቅን ለሚሻ ሰው በእርግጥ ዋጋ አላቸው። ኢየሱስ ትተዋቸው ያለፉት እኒያ ጥቂት ነገሮች

1 በቅርቡ (JESUS SUMIT) በተሰኘ ታላቅ ኮንፈረንስ ላይ በቀረበው አንድ ጥናት ላይ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በእየሱስ የተነገረው 18% ብቻ መሆኑ (April 8, 1996) የወጡት (TIME እና NEWS WEEK) መጽሔቶች ላይ የቀረቡት ዘገባዎች ያመለክታሉ–ተርጓሚው

እንኳ በክርስቲያን ሰባኪዎች ሆን ተብለው ይታለፋሉ። ለምን? ምክንያቱ ክርስቲያኖች ጽድቅ መሥራት ስለማያስፈልጋቸው ነው። ለምን? ምክንያቱ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተቸንክረው ስለሞቱና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ከኃጢአት ስለ አዳኗቸው ነው! ይህ ነው እንግዲህ ቤተክርስቲያን ነጋ ጠባ ዘወትር የምትነግራቸው።

ክርስቲያኖች ጽድቅ ሥራ እንዲሠሩ የሚሰጣቸው ትምህርት በጣም ትንሽ ከሆነ፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በተሰቀለ ሰው ሞት ከኃጢአት የዳኑ መሆናቸው የሚነገራቸው ከሆነ፣ በምዕራቡ ዓለም በሚገኙ ዓለማዊ ትምሕርት ቤቶች ውስጥ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ትምሕርት የማይሰጣቸው ከሆነ፣ ከሕዝበ ክርስቲያኑ ውስጥ በጣም ትንሽ መቶኛው ብቻ ወደ ቤተክርስቲያን የመሄድ ቁብ ያለው ከሆነ፣ ቤተክርስቲያን አጽንኦት ሰጥታ የምታስተምረው ስለ ኢየሱስ ተአምሮች እንጂ ስለ ኢየሱስ ትምሕርቶች ካልሆነና እራሳቸው ኢየሱስ ወንጌሎች ውስጥ እንደተናገሩት ትምሕርቶቻቸው የተሟሉ ያልሆኑ ከሆነ ክርስቲያኖች ጥሩ ለመሆንና ትሩፋት ለመሥራት እንዴት ሊበረታቱ ይችላሉ?

የሰው ልጅ በፈለግነው ዓይነትና ባቀድነው መሠረት መቅቀረጽ የሚችል ፍጡር ነው። ሰይጣናዊ እንዲሆን ከቀረጽነው ሰይጣናዊ ሊሆን ይችላል። በሁሉም ቦታ በክፉ ነገርና በኃጢአት ብቻ እንዲከበብ ካደረግነው ኃጢአተኛ ሰው ይሆናል። መልአካዊ እንዲሆን ከቀረጽነውም መልአካዊ ዓይነት ባህርይ ያለው ፍጡር ይሆናል። በትሩፋት ሥራዎችና በጽድቅ ተግባራት እንዲከበብ ካደረግነው ጻድቅና ምግባረ ሰናይ ሰው ይሆናል።

እኔ ራሴ በምዕራቡ ዓለም ለሚኖረው ሕዝብ አዝንለታለሁ። ለሆኑት ነገር እነሱን አልወቅስም። የነሱ መገናኛ–ብዙኃን፣ ትምሕርት፣ ትምሕርት ቤቶች፣ ጐዳናዎችና አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤአቸው ኢ–አማኝና ሃይማኖት–የለሽ ነውና። በኢ–አማኝ ሥልጣኔ ውስጥ አብዛኞቹ ሰዎች ኢ–አማኞች ናቸው። በኃጢአት ምድር አብዛኞቹ ሰዎች በኃጢአት ውስጥ ስለሚበቅሉ ኃጢአን ይሆናሉ። በጆሮአችን የምንሰማው ኃጢአት፣ በዓይናችን የምንመለከተው ኃጢአት፣ በሁሉም ቦታ የምናሽተው ኃጢአት ከሆነ በአብላጫ ግምት ወደድንም ጠላን በኃጢአት ውስጥ መዘፈቃችን የማይቀር ነው።

በተቃራኒው ግን መስጊድ ውስጥ የሚሰጠው እስላማዊ ትምሕርት፣ እስላማዊ መገናኛ–ብዙኃንና እስላማዊ ትመሕርት ቤቶች አጽንኦት የሚሰጡት ለትክክለኛው የሰው ልጅ ሥነ ምግባር ነው። የሚፈቀደውና የማይፈቀው ምን እንደሆነ፣ አንድ ሰው ምን መሥራት እንዳለበትና ምን መተው እንዳለበት አበክረው ያስገነዝባሉ። የእስላም ዋነኛው ተአምር እስላም ራሱ ነው። የእስላም ነቢይ የሆኑት ሙሐመድ ለሕዝቡ ያቀረቡት አንድ ብቸኛ ተአምር ቅዱስ ቁርአን ነው። የሳቸው ተአምር በመለኮታዊ ራዕይ የተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የኢየሱስ ተአምራት ከኢየሱስ ጋር አልፈዋል። የሌሎች ነቢያት ተአምራትም እንደዚሁ። የነሱ ተአምራት ከነሱ ሕልፈት ጋር አልፈዋል። በዚህ ረገድ ከሌሎች ነቢያት ልዩ የሆኑት ነቢዩ ሙሐመድ ብቻ ሲሆኑ የሳቸው ተአምር የሆነው ቅዱስ ቁርአን ዛሬም እንደነበረ ከኛ ጋር ነው። ወደፊትም ለዘለዓለም ከሰው እጆች ጋር ይኖራል። የሌሎች ነቢያት ተአምሮች ከነቢያቱ ጋር የሞቱ በመሆን ከስመዋል። ብቸኛው የተሟላውና የጠራው የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የሙሐመድ ተአምር ቅዱስ ቁርአን ግን የማያልፍ ዘላለማዊ ተአምር ነው። ውድ ወንድማችን! ቁርአንን ያንብቡትና የተናገርነው እውነት መሆኑን ራስዎ ይረዳሉ። ያንብቡት የእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ጥንካሬ እንዳለው ለራስዎ ማየት ይችላሉና። ቁርአን ኦሪጂናል ቋንቋው ዐረብኛ ሲሆን ፍቺዎቹ ወደተለያዩ የዓለም ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ትርጉም የኦሪጁናል ቋንቋውን የአቀራረብ ስልት ውበትና መስህብነቱን የሚቀንስና የሚደብቅ ቢሆንም እንኳ የተተረጎመው ቁርአን ራሱ ኃያል ፍቺውን እንደያዘ ይቆያል።

ታዲያ ሰዎች በዕለታዊ ኑሯቸው ውስጥ ይበልጥ የሚያስፈልጋቸው የትኛው ነው? የአንድ ነቢይ ያለፉና የከሰሙ ተአምሮች ወይስ መለኮታዊ ተግባራዊ ትምሕርቶቹ?

## ካህናትና ጀሌ ማይማን

ክርስትና ሕዝቡን ካህናትና ጀሌ ማይሞች በተባሉ ሁለት መደቦች ይመድባል። እያንዳንዱ መደብም የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎች አሉት። አንድ ሰው የቤተክህነቱ መደብ አባል ከሆነ ቤተክርስቲያን ያዘወትራል፣ አያ ገባም፣ የፀሎት ሥነ ሥርዓት ይመራል፣ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ያካሂዳል ወዘተ. ከተራው ማይም መደብ ከሆነ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውጭ ይሆናል፣ ማግባት ይችላል፣ የጸሎት ሥነ ሥርዓት መምራትም ሆነ ቤተክርስቲያን ማገል ገል ግን አይችልም። የካህናት የሥልጣን ተዋረድ እንደ ጦር ሠራዊት ወታደራዊ የሥልጣን ተዋረድ ፒራሚድ መሰል ሲሆን፣ ከላይ ቁንጮው ላይ ጳጳስ–ፓትር ያርኮች–አቡኖች–ሰባኪዎች ቀሳውስት..እያለ ከመንበረ ጳጳሱ በታች በተዋረድ የሚሰለፉበት እየሰፋ ወደታች የሚወርድ መዋቅር ነው።

በእስላም ውስጥ ግን እንዲህ ያለ የሕዝብ የመደብ ክፍፍል የለም። የካህናት መደብ ወይም የሃይማኖት መሪዎች ልዩ የሥልጣን ማዕረግ የለም። የሚያውቅ ከሆነ ማንኛውም ሙስሊም ሃይማኖታዊ ትምህርት መስጠት ይችላል። የተለየና በእስላም ውስጥ ያለውን ደረጃ የሚያመለክት ልዩ ልብስ እንዲለብስ ማንም ሙስሊም አይጠየቅም። በእስላም ምሑራን መካከልም አንዳች የሥልጣን ተዋ ረድ የለም። እስላም የካህናት መደብ የተባለ መደብ የሌለው በመሆኑ አፈጻ ጸሙን ካወቀ ማንም ሙስሊም የጸሎት (የሶላት) ሥነ ሥርዓት መምራት ይች ላል። ማንም ሙስሊም የቀብር ሥነ ሥርዓት መምራት ይችላል። እርግጥ ነው እስላም ውስጥ ሃይማኖቱን በደንብ ያጠኑ የሃይማኖት ምሑራን አሉ፤ ይሁን እንጂ ካህናት አይደሉም።

የትኛው ነው ይበልጥ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ የሚታየው? ካህናት–ጀሌ ሞዴሉ? ወይስ እስላማዊው ሞዴል?

# አጠቃላይነትና ሁለገብነት

አንድን እምነት ወይም ሃይማኖት የሚከተል ሰው፣ ፍጹም የሆነ ምሉዕ ሃይማኖት ለሰው ልጅ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ፣ ለሰው ልጅ አበይት ችግሮች መፍትሔ የሚያቀርብና ለሰው ልጅ የሥነ ምግባር መመሪያ የሚሰጥ ዓይነት መሆን አለበት ብሎ ይጠብቃል።

ክርስትና ግን በጣም የተናጋ ዶክትሪንና አንዳንድ የሥነ ምግባር መመሪያዎችን ወይ እጅግ በጣም መንፈሳዊ ወይ ደግሞ ያልተሟላ በሆነ ሁኔታ ያቀርባል። ይሁን እንጂ በሐዲስ ኪዳን በተገለጸው መሠረት የተቀናበረና መደ በኛ የሆነ የአምልኮ ተግባራት ክንዋኔ የለውም። የሰውን የለትበለት ክንውኖች የሚገዛ ሕግም የለውም።

በተጻራሪው ደግሞ እስላም የተሟሉ አጠቃላይና ሁለገብ የሆኑ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ የንዑሳን ሥርዓቶች ቅምር አሉት። እነሱም:-

1– ጽናት ያለው ሎጂካዊና ምክንያታዊ የሆነ የእምነት መርሆ፣

2– ግሩም ድንቅ የሆኑ የሥርዓተ–ጸሎትና የአምልኮ ክንዋኔ ትዕዛዛት ስብስቦች፣

3– ምሉዕ የሥነ ምግባር ሕግና የሞራል ትምሕርቶችና

4– የሰውን ልጅ ዕለታዊ የኑሮ ክንዋኔዎችን የሚያደራጅና በዋነኛ የሕግ መተላለፍ ድርጊቶች ላይ ቅጣት የሚደነግግ ዝርዝር ሕግ ናቸው። እስላም ዶክትሪን ሲደመር አምልኮት ሲደመር ሥነ ምግባር ሲደመር ሕግና ድንጋጌ ነው።

የተሟላ ሁለገብና አጠቃላይ ከመሆኑ አንጻር የትኛውን ይመርጣሉ? ክርስትና ወይስ እስላም?

## ዛፍና ፍሬዎቹ

ኢየሱስ «መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ይሰጣል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ይሰጣል» ብለዋል (ማቴ 7፥16–17)። በዚህ አባባል ሙሉ በሙሉ እንስማማለን።

እስኪ የክርስቲያንን ዛፍ እናስተውልና ከእስላም ዛፍ ጋር እናወዳድር።

የዛሬው ዓለም ዋነኛ ዓለም አቀፍ ችግሮች ምንድን ናቸው? ብዙ ሰዎች:- ኢምፔሪያሊዝም ነው፣ የዘር መድልዖ ነው፣ ኢ–አማኝነት ነው፣ ወንጀል ነው፣ አደንዛዥ እጽ ነው፣ ልቅ ወሲባዊ ነጻነት ነው፣ የቤተሰብ መበተን ነው፣ የጠፈር–ጦርነት ስጋት ነው፣ የአቶሚክ ቦምብ ስጋት ነው፣ በባዮሎጂካል ጦር መሣሪያ የሚደረግ ጦርነት ስጋት ነው፣ የኬሚካል ጦር መሣሪያ ጦርነት ስጋት ነው፣ የአልኮል ሱሰኝነት ነው፣ የኤድስ በሽታ ነው ወዘተ. ይላሉ።

እነኚህ ችግሮች የትና በነማን ተጀመሩ? ባለፉት ቅርብ ምዕተ ዓመታት ውስጥ ክርስቲያን የሆኑ የምዕራብ አገሮች አፍሪካና ኤስያን በመውረር የሁለቱን አሕጉራት አገሮች በቅኝ ግዛትነት ለመግዛት የመረጡት ባህላቸውን ለማስፋፋትና ሥልጣኔአቸውን ለማስራጨት ሳይሆን ደማቸውንና ሀብታቸውን ለመምጠጥ ዓላማ ነበር። የምዕራባውያን ስልትና ታክቲካቸው ሊለወጥ ይችል ይሆናል፣ውስጣዊ ምኞታቸው፣ ዓላማቸውና እውነተኛ ፍላጐታቸው ግን አይለወጥም።

የዘር መድልዎ የተጀመረው አሜሪካና ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በነጭ ክርስቲያኖች አማካይነት በጥቁሮች ላይ ነው።ኢ–አማኝነትና በሃይማኖት ማፌዝ የተጀመረው በአውሮፓ ነው። ሃይማኖትን ከመደበኛው አኗኗር መለየት የተጀመረው አውሮፓ ውስጥ ነው። ከሙኒዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝምና እስታሊኒዝም የተጀመሩት በክርስቲያኒቷ አውሮፓ ውስጥ ነው። ናዚዝም፣ ፋሺዝምና ሾፊኒዝምም እንደዚሁ።

የመካከለኛው ዘመን አውሮፓ ቤተክርስቲያን በእምነታቸው ምክንያት ብቻ ብዙ ሚሊዮን ሰዎች ጨፍጭፋለች። ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ከሷ የተለየ አቋም በነበራቸው ተቀናቃኞቿ ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽማለች። እስታ ሊንም በፀረ–ኮሙኒስቶች ላይ ይህንኑ ፈጽሟል።

የገነት ማስገቢያ ትኬቶች ሽያጭና ገነት ውስጥ መቀመጫዎችን ለሰዎች መያዝ የተጀመረው አውሮፓ ውስጥ ነው። ኢጣሊያ ውስጥ ቤተክርስቲያን በመ ካከለኛው ዘመን ከእግዚአብሔር ምሕረት የሚያስገኙ ቻርተሮች ስትሸጥ ያደረገችው ይህንኑ ነበር።

ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነትና የወሲብ ነጻነት የተጀመረው በክርስቲያኖቹ ምዕራብ አውሮፓና በአሜሪካ ነው። በዝሙት ተግባር ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የለም። በዘማዊነት ላይ ምንም መቀጫ የለም። ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከጋብቻ በፊት ወሲብ ይፈጽማሉ። ግብረ ሰዶም ፈጻሚዎች የራሳቸው የሆኑ ክለቦችና የሚከላከሉላቸው ተሟጋቾች አሏቸው። ሴቶች የትም ሥፍራ እርቃን ገላቸውን ይታያሉ። የእርቃን ገላዎች ክበቦች አሉ። ሁሉም ዓይነት ከተለምዶ ውጭ የሆኑ የወሲብ አፈጻጸም ሁኔታዎች የተፈቀዱ ናቸው። ሽርሙጥና ወደ ሕጋዊነት እየተለወጠ ነው። ጸያፍና ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ የወሲብ እብ ደት! እነኚህና ሌሎችም ከቤተክርስቲያን አንድ የተቃውሞ ቃል ሳይሰነ ዘርባቸው በአደባባይ ይፈጸማሉ!!

የቤተሰብ መፍረስና መበታተን የተጀመረውም በክርስቲያኑ ምዕራብ ነው። ባል በሚስቱ ላይ ምንም ቁጥጥር የለውም። ወላጅ በልጁ ላይ የተቆጣጣሪነት ሥልጣን የለውም።ወላጅ ከገዛ ልጁ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽም ይችላል።ትዳራዊ ሕይወትን ከፍጻሜ የሚያደርስ ፍቺ ዘወትር ይከሰታል። ዝሙት በፍጥነት እየተስፋፋ ነው።

በክርስቲያኑ የምዕራብ ዓለም የወንጀል ድርጊት በከፍተኛ መጠን እያደገ ነው። ሁሉም የወንጀል ዓይነቶች:- ሕጻናትን አግቶ መያዝ፣ ጠለፋ፣ በሕጻናት ላይ ወሲባዊ ግፍ መዋል፣ ሕጻናትን እንደ ቁሳቁስ መሸጥ፣ የቢሮ ጸሐፊዎችን ለሕገ–ወጥ ወሲብ መጠቀም፣ የማስፈራሪያ መልዕክቶች በመላክ ማስፈ ራራት፣ የግዳጅ ወሲብ፣ በቅርብ የሥጋ ዘመዳሞች መካከል የሚፈጸም የወሲብ

ጋጠወጥነትና የነፍስ ግድያ በማንኛውም ሥፍራና በማንኛውም ጊዜ ይፈጸማሉ። የወንጀሎቹ ብዛትና መጠን በእጅጉ የሚያስበረግጉ ናቸው። የወንጀሎች መዘርዝር ለማመን የሚያዳግት ነው።

አደንዛዥ እጾች በክርስቲያን አገሮች ውስጥ የስጋት ምንጭ ናቸው። የትምህርት ቤቶች ታዳጊ ወጣቶች የአደንዛዥ እጽ ምርጥ ደንበኞች ናቸው። አደንዛዥ ዕጾች በአብዛኛው የሚቀመሙት በክርስቲያን አገሮች ውስጥ ነው። የአልኮል መጠጦች የክርስቲያኖች ምርጥና የደራ ንግድ ሲሆኑ ያመርታሉ፣ ይሸጣሉ፣ ይጠጣሉ በአስከፊ ውጤቶቻቸውም ይረካሉ።

ከሃያ አምስት ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በ1914 እና በ1939 ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች የጀመሩት የክርስቲያን አገሮች ናቸው። በነዚህ ጦርነቶች ከሰባ ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎችን ገድለዋል። በክርስቲያን አገሮች መካከል ቀዝቃዛው ጦርነት ጋብ ብሎ አያውቅም። ሁልጊዜም እዚህና እዚያ አነስተኛ ጦርነቶች ያካሂዳሉ፣ ወይም ጦርነት ይጭራሉ፣ አለበለዚያም አንዱን ደግፈው ይነሳሉ።

የዩ.ኤስ. አሜሪካና የአውሮፓ ክርስቲያን አገሮች የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች በሠላም እንዲኖሩ የሚተውዋቸው በጣም አልፎ አልፎ ነው። በየጊዜው እዚህና እዚያ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት አንድ ዓይነት ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጫና ያደርጋሉ፤ ሴራ ይጠነስሳሉ፤ ወይም ወታደራዊ ኩዴታ፣ ግድያ ወይም የሲቪል ጦርነት ወይም የድንበር ግጭት እንዲፈጠር ዕቅድ ጠንስሰው ያስፈጽማሉ። ትላልቆቹ ክርስቲያን አገሮች በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥ የጥፋትና የውድመት እሳት ሲንቀለቀል በማየት ይረካሉ።

ዩ.ኤስ.ኤ ክርስቲያኗ አገር ሁለት የጃፓን ከተሞችን በሁለት የአቶሚክ ቦንቦች በመምታት እንቅልፍ ላይ የነበሩ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎችን ገድላ ከተሞቹን ወደ ዶግ አመድ መለወጥ መርጣለች።

ክርስቲያን አገሮች ሲቪሎች ሊያመልጧቸው የማይችሉ አስበርጋጊ የውድመት መሣሪያዎችን ፈልስፈዋል። ኬሚካላዊና ባዮሎጂካዊ የጦር

መማሪያዎችን ፈልስፈው በመሥራት ተገልግለውባቸዋል። ዓላማህን ለማሳካት ማንኛውንም ነገር አድርግ የሚል ርኅራኄ–የለሽ ሥልጣኔ ነው።

ክርስቲያን አገሮች በመላው ሕዝብ ላይ ሴራ ይሸርባሉ። ይሁዶች ፍልስጥኤምን እንዲይዙና የፍልስጥኤምን ሕዝብ ወደ ስደተኝነት እንዲለውጡ ረድተዋል። ድርጊቱ ከመላው ሕዝብ በጠራራ ጸሐይ መሬቱንና መብቶቹን የመንጠቅ ልዩ ዘረፋ ነበር።

እነኚህ እንግዲህ የክርስቲያን ዛፍ ፍሬዎች አንዳንድ ምሳሌዎች ናቸው። ምንኛ ብሩክ ዛፍ ነው! ፍሬዎቹስ!! እንዲህ የከፋ ዛፍና የመረሩ ፍሬዎች ለምን ሆነ? ምክንያቱ ያ ዛፍ በእግዚአብሔር ያልተተከለና በእግዚአብሔር የመመሪያ ውሃ እንዲጠጣ ያልተደረገ ዛፍ በመሆኑ ነው። ክርስትና ከኢየሱስ ጋር ምንም ትስስር የለውም። ሌላው ቀርቶ ከኢየሱስ ትምሕርቶች ጋርም ይጻረራል። ክርስትና ሰው–ሠራሽ ነው። ክርስትና ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጻረር ነው። አውሮፓ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሞ ተከትላ አታውቅም። በዚህ ምክንያት ነው ዛፏ እንዲህ መጥፎ፣ ፍሬዎቿ እንዲህ መራራ የሆኑት።

የእስላምን ዛፍ ደግሞ ይመልከቱ። ሙስሊሞች መልአኮች ናቸው የምል ሰው አይደለሁም። ይሁን እንጂ ለክርስቲያኖች የተጠቀምናቸውን ተመሳሳይ መስፈርት እንጠቀምና ሙስሊሞች ለዛሬው ዘመን ኢምፔሪያሊዝም ተጠያቂዎች አይደሉም። የኢምፔርያሊዝም ሰለባዎች እንጂ። ሙስሊሞች የቀለም ልዩነትና የዘር መድልዎ ጀማሪዎች አይደሉም፣ ሁሉም ቀለሞችና ዘሮች በእስላማዊ አገሮች ውስጥ በእኩልነት ይኖራሉና።

ሙስሊሞች የምዕራባውያን ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት ይጸየፋሉ። በአሜሪካና በአውሮፓ ካለው የወንጀል ብዛትና መጠን ጋር ሲነጻጸር በሙስሊም አገሮች ውስጥ ያለው ወንጀል በጣም አነስተኛ ነው። እስላማዊ አገሮች የክርስቲያን አገሮች በሚጠቁበት ደረጃ በአደንዛዥ እጽና በአልኮል መጠጦች አይጠቁም።

እስላማዊ ቤተሰብ ጠንካራና እርስ በርስ በጽኑ የተሳሳረ ነው። የፍቺ ቁጥር ብዛት በጣም አነስተኛ ነው። ዘማዊነትም በጣም ጥቂት ነው። የወላጅ ሥልጣን አሁንም በጣም ጠንካራ ነው።

ዘመናዊው ኤቲይዝምና ኮሙኒዝም በእስላማዊ አገሮች ውስጥ ተወልደው አላደጉም። እስላማዊ አገሮች ያለፉትን ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች አልጀመሩም።

እናም ግልጽ ቀጥተኞችና ምክንያታዊ እንሁንና የዛሬው ዓለማችን አበይት ችግሮች የተፈጠሩት በክርስቲያን አፈር ውስጥ ነው። በጣም አስፈሪና አስበርጋጊውን ዋነኛ የዓለማችን ራስምታት–በክርስቲያን ምድር የበቀለ በጣም አዲሱን የክርስቲያን ዛፍ ፍሬ ኤድስንም መዘንጋት የለብንም። አንድ ዛፍ በጣም አስከፊና አስፈሪ የሆኑ ፍሬዎችን የሚያፈራ ከሆነ ዛፉ አንድ ዓይነት ችግር አለበት ማለት ነው። ወይ ደግሞ እንደ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ልክ አይደለም።

መምረጥ ቢፈልጉ የትኛውን ዛፍ ይመርጣሉ? የክርስቲያኑን ዛፍ? ወይስ እስላማዊውን ዛፍ? ሐቀኛ ሰው ይሁኑ።

# ምዕራፍ 7

# ሕግ በሁለቱም ሃይማኖቶች ዘንድ

## ውኃ ወይስ የወይን ጠጅ?

ኢየሱስ በአንድ የሠርግ ድግሥ ላይ ውኃ ወደ ወይን ጠጅ መለወጣቸውንና በድግሡ ላይ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ያን ወይን ጠጅ መጠጣታቸውን የክርስትናው ሐዲስ ኪዳን ዘግቧል (የሐንስ ወንጌል)።

በተቃራኒው ደግሞ፣ እስላም (ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ቃል) ሁሉንም ዓይነት የአልኮል መጠጦችን እርም አድርጐ ይከለክላል። ይህም ብቻ ሳይሆን እስላም አስካሪ መጠጥ መሸጥ፣ ማጓጓዝ፣ ማስተናገድና ማምረትን ጭምር ያግዳል።

የአልኮል መጠጦች በግለሰብና በሕብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን አፍራሽ ውጤቶች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ለአንድ ሃይማኖት የተሻለው አማራጭ የትኛው ነው ብለው ያስባሉ? ውኃን ወደ ወይን ጠጅነት የሚለውጥ? ወይስ የአልኮል መጠጦችን ማምረትና መጠጣት የሚከለክል? የትኛው ሃይማኖት ነው በይበልጥ መንፈሳዊነት የሚታይበትና ለሕዝብ ደህንነት የተሻለው?

## ውርስ

የሞተ ሰው ንብረት ለወራሾች እንዴት መከፋፈል እንዳለበት ክርስትና ምንም አይነግረንም። እንዲህ ያለው አከፋፈል የሚወሰነው በክርስትና ሕግ ሳይሆን በሰው ሠራሽ ሕግ ነው።

በተቃራኒው ግን፣ ቁርአን–የእስላም መለኮታዊ መጽሐፍ–ውርስ እንዴት መከፋፈል እንዳለበት ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል። እስላም የያንዳንዱን ወራሽ

ማለትም የአባት፣ የናት፣ የሚስት፣ የወንድ ልጅ፣ የሴት ልጅና የሌሎች ዘመዶችን ድርሻ ይወስናል።

እንደ ሃይማኖትና እንደ እግዚአብሔር ቃል የትኛው ነው በይበልጥ የተሟላው? ውርስ እንዴት መከፋፈል እንዳለበት ምላሽ የማይሰጥ ሃይማኖት? ወይስ ለእንዲህ ያለ አስፈላጊ ጉዳይ ዝርዝር ምላሽ የሚሰጥ ሃይማኖት?

## ኢየሱስና የአሳማ ሥጋ

ኢየሱስን የምታፈቅረው ቤተክርስቲያን ትከዳቸዋለች! ኢየሱስ የ‹ ·ሴን ሕግ ላጠፋ አልመጣሁም ብለዋል። ይህ ሕግ ደግሞ የአሣማ ሥጋ መብላትን እርም ያደርጋል። ስለዚህም ኢየሱስ ሕጉን የሚከተሉ በመሆናቸው የአሳማን ሥጋ የተመለከቱት እርም አድርገው ነው።

ኢየሱስን በባዶ ቃላት ሌትተቀን የምታወድሰው ቤተክርስቲያን ግን የኢየሱስን ቃል ወይም ተግባር አታከብርም። ቤተክርሲቲያን የአሣማ ሥጋ መብላትን ትፈቅዳለች! ለምን? የአውሮፓ አሕዛብ (Gentile) የአሳማ ሥጋ በጣም የሚ ወዱ በመሆናቸው ምክንያት። የኢየሱስ ቃል ቤተክርስቲያኗን አያሳስባትም። የሚያሳስባት ሕዝብን ማስደሰትና ያሻችሁን አድርጉ፣ የፈለጋችሁትን ነገር ብሉ፣ ያሰኛችሁን ነገር ጠጡ፣ በማለት ወዳስፈለጋቸው በቀላሉ የሚነዱትን ሃይ ማኖት ለሕዝቡ መስጠት ነው። በትክክልም ቤተክርሲቲያንኢየሱስን ሰርዛለች፣ ሕጉንም ውድቅ አድርጋለች።

ቤተክርሲቲያን አዲስ ሕግ አላትና ሕጉ ሕግ አይደለም። ሕጉ ጳጳሱ የተና ገረው እንጂ ኢየሱስ የተናገሩት አይደለም፣ ሙሴ የተናገረውም አይደለም፣ እግዚአብሔር የተናገረውም አይደለም።

በተቃራኒው ደግሞ እስላም መቼውም ቢሆን እግዚአብሔር የከለከለውን ወይም ነቢዩ ሙሐመድ ያገዱትን ነገር ፈጽሞ አይፈቅድም። እስላም በፍጹ ማዊነት ለእግዚአብሔር መግገዛት ነውና።

እንደ ቅዱስ ሃይማኖት የትኛውን ይመርጣሉ? የራሱን ነቢይ ትምህርቶች የሚሰርዝ፣ የኢየሱስን ቃል የሚያፈርስ ሃይማኖት? ወይስ የእግዚአብሔርንና የነቢዩን ትምህርቶች አጥብቆ የሚይዝ ሃይማኖት?

## ብዙ ማግባት

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሚስት ማግባትን አይከለክልም። ነቢዩ ሰለሞን ሰባት መቶ ሚስቶች ማግባታቸውንና ሦስት መቶ እቁባቶች እንደነበሯቸው ይዘግባል (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 12፥3)። አብዛኞቹ የአይሁድ ነገሥታት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚዘግበው በብዙ ሁኔታዎች እስከ አሥራ ዘጠኝ የሚደርሱ ብዙ ሚስቶች ነበሯቸው።

ሐዲስ ኪዳንም ለአንድ ሰው በሚፈቀዱት የሚስቶች ቁጥር ላይ በጭራሽ ገደብ አላደረገም። ኢየሱስም ብዙ ማግባትን ፈጽሞ አልከለከሉም። ጳውሎስም በመልዕክቶቹ ውስጥ አላገደም። መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይና በሐዲስ ኪዳኖቹ በሚስቶች ቁጥር ላይ አንዳች ገደብ ሳያኖር ብዙ ማግባትን ፈቅዷል። አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለው የክርስቲያን ባህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን በቤተክርስቲያን የተጀመረ ይትባሃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማግባትን ፈጽሞ አላወገዘም፤ አልከለከለም፤ ድጋፍ አልነሳውም፤ አልገደበውም፤ ምንም ዓይነት ደንብና ገደቦችም አልጣለበትም።

በተጻራሪው ግን እስላም በቁርአን ውስጥ ብዙ በማግባት ላይ ገደቦች ጥሏል። የሚስቶቹ ቁጥር ከአራት መብለጥ የሌለበት ሲሆን ባል ሁሉንም በእኩልነት ማስተዳደር ይኖርበታል። ብዙ ማግባት ብዙ መሠረታዊ የሆኑ ማህበራዊ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል የዝሙት በር መዝጋቱ፣ የአንድ ሚስት ግን ብዙ ወዳጆችን ከስተት መዋጋቱና የሴቶችን በቁጥር ከወንዶች የመብለጥ ችግር[1] መፍትሔ መስጠቱ የሚጠቀሱ ናቸው።

1 በቅርቡ ሰኔ 1988 መጀመሪያ ላይ ውጤቱ ይፋ በሆነው የ 1987 የአዲስ አበባ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መሠረት የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት 2,254,562 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሴቶች 1,162,561 ሲሆኑ ወንዶች 1,092,301 ናቸው። ይህ የሚያሳየው በአዲስ አባባ ከተማ ውስጥ ብቻ የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ቁጥር በ70,260 የሚበልጥ መሆኑን ነው— ተርጓሚው

ታዲያ በይበልጥ ተግባራዊ ብቃትና ተቀባይነት ያለው የትኛው ነው? የመጽሐፍ ቅዱሱ ገደብ–የለሽ ልቅ ብዙ ማግባት? ወይስ ቁርአናዊው በገደብ የታጠረ ብዙ ማግባት? እርግጥ ነው በምዕራቡ ዓለም አንድ ወንድ አንዲት ሚስት ብቻ አለችው፤ ዳሩ ግና ብዙውን ጊዜ አቶ ባል ቁጥራቸው ከበዛ ቅምጥ ወዳጆች ጋር ወሲባዊ ትስስር አለው። ታዲያ የትኛው ነው የበለጠ ንጽሕናና ጥራት ያለው? አንድ ሚስትና ብዙ ምስጢራዊ ወዳጆች? ወይስ አንድ ሚስትና አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች ተጨማሪ ሚስቶች ግን ያላንዳች ምስጢራዊ ወዳጆች የሚለው እስላማዊ አመለካከት?

## የመቅጫ ሕግ የለም

ዝሙት የፈጸመች ሴት እንዲቀጡ ኢየሱስ በተጠየቁ ጊዜ መቅጣቱን እምቢ ብለው እያንዳንዱ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ ወደ ሴትዮዋ ድንጋይ መወርወር የሚችል አንድም ሰው አለመኖሩን መናገራቸው ሐዲስ ኪዳን ውስጥ በዮሐንስ ወንጌል ተዘግቧል። ያ ትረካ ባለበት ሁኔታ ለዝሙትና ለዘማዊነት አረንጓዴ መብራት ማሳየት ተደርጐ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይችላል። ለምን ቢባል በዝሙተ ኛይቱ ሴት ላይ ምንም ዓይነት ቅጣት አልተላለፈምና። ታሪኩ እንደሚያስረዳው ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ ክሱን ለመመርመር እንኳ ግድ አልነበራቸውም። እንዲያው ሴቲቱን መቅጣት እምቢ በማለትና መልካሙን ተመኝተውላት ነው ወደ ቤቷ የሸኟት።

ቁርአን የዝሙተኛን ቅጣት ለይቶ የወሰነ ሲሆን ነቢዩ ሙሐመድም በሕይ ወት ዘመናቸው ውስጥ ቅጣቱን ተግባራዊ አድርገውታል።

ለርስዎ ይበልጥ ስሜት የሚሰጥዎ የትኛው ነው? እንደተባለው ኢየሱስ ሊተገብሩት የመጡትን የሙሴ ሕግ ራሳቸው እምቢ ማለታቸው? ወይስ ሙሐመድ የእግዚአብሔርን ሕግ መተግባራቸው? ለመጪዎቹ ዳኞች የተሻለው ጥሩ ምሳሌ የትኞቹ ነው? ሕግን በማስከበሩና በመጠበቁ ረገድ የበ ለጠ ውጤታማው የትኛው ነው? ዝሙትን ከማውገዝና ከመኮነን አኳያ ይበልጥ ትርጉም ያለው የትኛው ነው።

## ምንኩስና ወይስ ጋብቻ?

ማግባት አንድን ሰው ከእግዚአብሔር አምልኮ ስለሚያውከው ሐዲስ ኪዳን በጳውሎስ መልዕክቶች ውስጥ ሰዎች እንዳያገቡ ይገፋፋል። በቤተክርስቲያን እምነት መሠረት ሴት ሰይጣናዊነት ስለማያጣት ከሴት ርቆ መኖሩ የተሻለ ነው። ጽድቅና ንጽሕና የፈለገ ሰውም በድንግልናና በምንኩስና ይኑር።

የእስላም አቋም ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ወንዶችና ሴቶች ጣጣውን ከቻሉ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲያገቡ ነው እስላም የሚገፋፋው። ምክንያቱም ጋብቻ አንድን ሰው ከኃጢአትና ከዝሙት ስለሚጠብቀው ነው። እስላም ሰዎችን ከምንኩስናና ከምናኔ በማስጠንቀቅ ትዳር እንዲመሠርቱ ያበረታታቸዋል።

ለግለሰብና ለማህበረሰቡም የትኛው ነው ይበልጥ ንጹሕና በላጩ? ምንኩስና ወይስ ጋብቻ? የማሕበራዊ ተሐድሶ አራማጅ ቢሆኑ ሰውን የሚመክሩት በድንግልና እንዲቆይ ነው ወይስ በተቻለ መጠን ቶሎ ጋብቻ እንዲመሠርት ነው? አስበውበት ይወስኑ። የትኛው ነው ሕብረተሰቡን ከወሲብ–ነክ ወንጀሎች የሚጠብቅ ወይም ቢያንስ ወንጀሎቹን የሚቀንስ? ምንኩስና ወይስ ጋብቻ? ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች የሚፈልጉት የትኛውን ነው? ምንኩስና ወይስ ጋብቻ? እርስዎ የትኛውን ይመርጣሉ? ለምንኩስና ጥሪ የሚያደርገውን የክርስትና አቋም ወይስ ለጋብቻ ጥሪ የሚያደርገውን እስላማዊ አቋም?

## የሴት ልጅ ሚና

አዳም ከተከለከለው ዛፍ እንዲበላ ስላሳሳተችው ቤተክርስቲያን ሴትን እንደ ተረገመ ፍጡር ትመለከታለች።

እስላም ግን ለሴት እንዲህ ዓይነት አመለካከት የለውም። ነቢዩ ሙሐመድ ሴቶች የወንድ እህቶች መሆናቸውን ተናግረዋል። እስላም ለሴቶች

በኃላፊነታቸው መጠን መብቶችን የሚሰጥ ሲሆን እንደ እናት፣ ሚስት፣ ልጅና እህት ለሴቶች ታላቅ ክበሬታ ይሰጣል። የተከለከለውን ዛፍ ጉዳይ በተመለከተ ቁርአን ሁለቱንም አዳምና ሔዋንን ለተፈጸመው ስህተት እኩል ተጠያቂዎች አድርጎ ይስላቸዋል።

ለሴት ልጅ ፍትሐዊ አመለካከት አለው ብለው የሚወስዱት ትረካ የትኛው ነው? ከፍተኛውን ወቀሳ በሔዋን ላይ የሚጭነውን? ወይስ አዳምና ሔዋን ሁለቱንም እኩል ተጠያቂዎች አድርጎ የሚወስደውን ትረካ?

## የሕልም ኃይል

ቤተክርስቲያን የአሳማ ሥጋ እንዲበላ እንዴት ፈቀደች? ለዚህ የሆነ ትረካ ወይም ማመካኛ አስፈለጋት። ጴጥሮስ ርቦት ነበርና ተኛ። አንቀላፍቶ ሕልም አየ። እንስሳት ሁሉ ሥጋቸውን መብላት ይፈቀዳል የሚል ድምጽ ከሰማይ ሰማ! ሙሴ የሞተው የአሳማ ሥጋ እርም ነው መብላት አይፈቀድም የሚለው ሕግ እንደነበረ ሳይሻር ነበር። ኢየሱስም እንዲሁ ሕጉ እንደነበረ እያለ ነው ያለፉት። ታዲያ ምን ማድረግ ይበጃል? ራእይ መምጣት ነበረበትና ሕልመኛ ሰው አስፈለገ! ሕልመኛውም ጴጥሮስ ነበር። መፍትሔው ተገኘ። ተኛናም እነሆ ሕልም ታየው! የእንስሳት ሁሉ ሥጋ መብላት በሕልም ተፈቀደ።

አንዱ የጴጥሮስ ሕልም ብቻ የሙሴን ሕግና የኢየሱስን ቃል ወዲያውኑ ሻረ! ጴጥሮስ የሁለቱንም ማለትም የሙሴንና የኢየሱስን ቃል የመሻርና ውድቅ የማድረግ ሥልጣን ነበረው!! በተጨማሪ ሕልሞችም ሁሉም ነገር ተሻረና ቤተክርስቲያን ሁሉንም ነገር ፈቀደች!! ሕልም ሃይማኖት ማስገኘት ይችላል? ቤተክርስቲያን ሃይማኖት የማስገኘት ሥልጣን ካላት እግዚአብሔር ለምን ነቢያት ላከ?!

በተጻራሪው ግን እስላም ለሕዝቡ ሕግ በሕልም እንዲደነገግለት አይፈቅድም። እስላም ጴጥሮሳዊ ሕልሞች የሉትም። እስላማዊ ሕግ እግዚአብሔር በቁርአን ያስተላለፈውና ወደ ነቢዩ ሙሐመድ ያስተላለፈው መለኮታዊ ራእይ

(ወሕይ) ነው። እስላም እግዚአብሔር የተናገረውን ወይም ነቢዩ ሙሐመድ የተናገሩትን ፈጽሞ ውድቅ አድርጎ ሰርዞ አያውቅም። የእግዚአብሔርንና የነቢዩን ትምህርቶች የመሰረዝ መብትና ሥልጣን ማንም ሰው የለውም። እግዚአብሔር አንድን ነገር ከፈቀደ ያን ነገር ማንም ሰው መከልከል አይችልም። እግዚአብሔር አንድን ነገር ከከለከለም በሕልሙም ይሁን በዕውኑ ማንም ቢሆን ያን ነገር መፍቀድ አይችልም።

*ታዲያ ምርጫዎ የትኛው ነው? የጴጥሮስ ሕልሞች? ወይስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ራእይ?*

## የሙሴ ሕግ

ኢየሱስ የመጣሁት ሕግን ለመፈጸም እንጂ ለመሻገር አይደለም ብለዋል (ማቴ 5፥17–18)። ይህ ማለት ክርስትና የሙሴን ሕግ ተግባራዊ ማድረግ የራሱ እምነት አካል አድርጎ መውሰድ አለበት ማለት ነው።

ጳውሎስ ግን በመልዕክቶቹ ውስጥ የሙሴን ሕግ ሽሯል። በዚህ አድራጎቱም የኢየሱስን ቃልም ሽሯል። ታዲያ ቤተክርስቲያን የምትከተለው ማንን ነው? አዳኙ በመሆኑ ኢየሱስን ትከተላለች ብሎ ነው አንድ ሰው የሚጠብቀው። ግና አይደለም። ጳውሎስን ነው የምትከተለው። የምትመራውም በሱ ነው። ጳውሎስ ኢየሱስ የተናገሩትን፣ ሙሴ ያደረጉትንና የተናገሩትን፣ እግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ሕግ ይሆን ዘንድ ያቀደውን የመሻር ሥልጣን ነበረው።

ከዚያ አሳዛኝ ጊዜ ጀምሮ ክርስትና፣ አየር ላይ ከሚንሳፈፍ ባዶ ቁርጥራጭ የቀላጤ ምክር ውጭ ምንም ሕግ የሌለው ሃይማኖት ሆነ። ከኃጢአት ወይም ከወንጀል የሚከላከልለት ተጨባጭ መከላከያ የሌለው ሃይማኖት ሆነ። የሙሴ ሕግ ብዙ ገደቦችና መቀጫዎች ያሉት በመሆኑ ምክንያት ጳውሎስ ሕጉን አልወደደውም። የጳውሎስ ፍላጎት፣ ሌላ ሰው በመስቀል ላይ ስለተገደለልህ መዳህን አግኝተሃል! ያሻህን ነገር ሥራ፣ የፈለግከውን ነገር ብላ፣ ጠጣ፣ የሚል ቀላልና ልል የሆነ ሃይማኖት ስለነበረ የሙሴን ሕግ አልወደደውም።

ክርስትና ነኝ ብሎ የፈለገውን ነገር ማለት ይችላል። የእግዚአብሔር መንገድ ነኝ ማለት ግን አይችልም። ለምን ቢባል ኢየሱስ ግልፕልፕ አድርገው እንደተናገሩት ሊፈጽሙት እንጂ ሊሽሩት ያልመጡትን የሙሴ ሕግ በመሻር እግዚአብሔር የደነገገውን ሕግ ሰርዟልና።

እስላም ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አንድ ነው። ምንም አይጨምርም። ምንም አይቀንስም።

የትኛውን ነው ሚመርጡት? መሥራቹ የተቀበለውን የሚሽር ሃይማኖት? ወይስ በእግዚአብሔር ቃል ወይም ሕግ ሙሉ በሙሉ የሚገዛውን ሃይማኖት? መለኮታዊ ሕግ የሌለውን ወይስ መለኮታዊ ሕግ ያለውን? የእምነት መርሕ ብቻ ያለውን ወይስ የእምነት መርሕና ሕግም ያለውን?

## ተለዋዋጭነት ያለው ሃይማኖት

ክርስትና ውስጥ ብዙ ነገሮች ይለዋወጣሉ። ምንጮቹ መለኮታዊ ስላልሆኑ ክርስትና ወጥና ቋሚ አይደለም። ለምሣሌ ያህል የአሳማ ሥጋ በኢየሱስ ዘመን አይፈቀድም ነበር። በኋላ ግን የተፈቀደ ሆነ። በኢየሱስ ዘመን መገረዝ ግዴታ ነበር፣ በኋላ ግን አልነበረም። በኢየሱስ ዘመን የሙሴ ሕግ ተግባራዊ ይደረግ ነበር፣ በኋላ ግን አልነበረም። በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ፍቺ አይፈቀድም ነበር፣ በኋላ ግን ያላንዳች ገደብ የተፈቀደ ሆነ። በመጀመሪያው ዘመን እግዚአብሔር ራሱ አንድ ነበር። በኋላ ላይ ግን ሦስትም አንድም ሆነ። መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ የተላኩት ለሕዝበ እስራኤል ብቻ ነበር። በኋላ ግን ተልዕኳቸው ወደ ሁሉም ሕዝቦች ተደረገ።

ክርስትና እግዜር–ሰራሽ ሳይሆን ቤተክርስቲያን–ሰራሽ ከመሆኑ አንጻር ተለዋዋጭነቱ ጊዜው በጠየቀ ሁኔታ ቀጣይ ነው። አዲስ ነገሮች በተፈጠሩ ቁጥር ክርስቲያናዊ ለውጦችም በዚያው መጠን ይቀጥላሉ። ክርስትና ከኢየሱስ ጋር ትስስር የሌለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም በማያቋርጥ ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው። ሁሌም እንደተሻሻለና እንደተሠራ ነው።

በተቃራኒው በኩል ግን እስላም ሁሌም ያው ነው። ከአሥራ አራት ምዕተ ዓመታት በፊት የተፈቀደው ነገር ዛሬም እንደተፈቀደ ነው ያለው። ያኔ የታገደ ውና የተከለከለው ዛሬም እንደታገደና እንደተከለከለ ነው ያለው። ለምን? እስላም የእግዚአብሔር መንገድ በመሆኑ ምክንያት። እንግዚአብሔር ምን ዓይነት ሕግ እንደሚሰጥ ያውቃል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሕጎች ለውጥና ማሻሻያ አያስፈልጋቸውም።

ለመለኮታዊ እምነትነት ምን ይመርጣሉ? ተለዋዋጭ የሆነ ሃይማኖት? ወይስ የማይለወጥና ቋሚ የሆነውን?

## ተለዋዋጭ ሕጎች

ክርስትና ሲጀመር ኢየሱስ ወንጌሎቹ ውስጥ እንዳሉት ሁሉ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ፍቺን ይከለክል ነበር። ይህ ሕግ ግን ቢያንስ በፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች ዘንድ ተሽሮ ፍቺ ያለ ምንም ገደብ ይፈቀዳል።

እስላም ግን ቋሚ ሕጎች አሉት። በእስላም ዘንድ ፍቺ ከተፈቀዱ ነገሮች ሁሉ በጣም የተጠላው ተፈቃጅ ከመሆኑ ጋር ይፈቀድ ነበረ፣ ዛሬም ወደፊትም እንዳተፈቀደ ይኖራል። እስላማዊ ሕጎች ከመጀመሪያው አንሥቶ ትክክለኛ ናቸው። ለዚህም ነው የማይለዋወጡት፣ መለዋወጥና መቀያየር አያሻቸውምና። እንደ እግዚአብሔር ቃል የትኛውን ይመርጣሉ? በአበይት የሕይወት ጉዳዮች ላይ ጥርት ያለ አቋም የሌለውና በሰው ልጆችና በሕግጋትም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሌ ሙከራ የሚያካሂድ ሃይማኖት? ወይስ ጥርት ያሉ ትክክለኛና ቋሚ የሆኑ ሕግጋት ያሉት ሃይማኖት? የእግዚአብሔርን ሕግጋት በሰብዓዊ ፍጡራን ሕግ መለወጥ የሚያመለክተው ተለዋጩ ሕግ የእግዚአ ብሔር ሕግ አለመሆኑን ነው። ሰዎች እንዴት የእግዚአብሔርን ሕግ ያሻሽሉ ታል? አንድ ሕግ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ከሆነ የእግዚአብሔር ሕግ ሊሆን አይችልም፣ ወይም ደግሞ ቢያንስ የእግዚአብሔር የመጨረሻውና የማጠቃለያው ሕግ ሊሆን አይችልም።

## ያልተሟላ መመሪያ

ክርስትና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በመሳሰሉ በመቶዎች በሚቆጠሩ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ትምሕርት የማያስተላልፍ በመሆኑ የተሟላ መመሪያ ነኝ ብሎ ማለት አይችልም። ከእነኚህም ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ:-

1. እንስሳት እንዴት መታረድ እንዳለባቸው
2. ለመብላት የማይፈቀዱ እንስሳት የትኞቹ እንደሆኑ
3. ሳይታረድ የሞተ ሥጋ አለመብላት
4. ስለ ሞግዚት
5. የእንስሳት አደንን ስለሚገዙ ሕጎች
6. የአልኮል መጠጦች
7. አደንዛዥ ዕጽ
8. ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶች መልበስ እንደማይፈቀድላቸው
9. ሴቶች ምን ዓይነት ልብሶች መልበስ እንደማይፈቀድላቸው
10. የአንዲት ሴት አኳኋን ምን መሆን እንዳለበት
11. ከወርቅ የተሰሩ የመመገቢያ እቃዎችና ቁሳቁሶችን ስለመጠቀም
12. ከወንድ አካል መሸፈን ስላለባቸው ክፍሎች
13. ከሴት አካል መሸፈን ስላለባቸው ክፍሎች
14. የባል መብትና ግዴታ
15. የሚስት መብትና ግዴታ

16. የወላጆች መብትና ግዴታ

17. የሕጻናት መብትና ግዴታ

18. ሐውልትና ቅርጻቅርጽ

19. የማይፈቀዱ ሥራዎች

10. የዋነኛ ወንጀሎች ቅጣት

21. የወንድ–ሴት ግንኙነቶች

22. የተከለከሉ ጋብቻዎች

23. ብዙ ማግባት ላይ የሚጣል ገደብ

24. ውርጃ

25. የጋብቻ ሁኔታዎች

26. ጉድፈቻ

27. ውርስ

28. ጥንቆላ

29. የዘር የጐሣ የቀለም ወዘተ መድልዖ

30. አራጣ

31. የሥርቆት ወይም የዘረፋ ቅጣት

32. የንግድ ሽርክና

33. ቁማር

34. ጉቦ

በተጻራሪው ግን እስላም ከላይ ስለተመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ ግልፀል፣ አድርጐ በማስተማር ምን እንደሚፈቀድ ምን እንደሚከለከል በዝርዝር ያብራራል። የቁርአን አንቀጾችና የነቢዩ ሙሐሙድ ቃሎች የሰውን ልጅ በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ በሚያጋጥሙት በብዙ መቶዎች በሚቆጠሩ አበይት ርዕሶች ላይ ዝርዝር መመሪያ ይሰጣሉ። እስላም የተሟላና ፍጹም የሆነ የአኗኗር መንገድ ነውና።

የተሟላና ፍጹም የሆነ መመሪያ ፈላጊ ቢሆኑ የትኛውን ይመርጣሉ? ክርስትና ወይስ እስላም?

يهدى ولا يباع

اللغة الأمهرية

# الإسلام والمسيحية

تأليف
الدكتور / محمد علي الخولي

اللغة الأمهرية

طبع على نفقة عبدالله الفقير إلى عفو ربه ورضاه
غفر الله له ولوالديه ولذريته ولجميع المسلمين

وقف لله تعالى لا يجوز بيعه

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر وأم الحمام